

«አገራዊ ምክክር በራሱ ኢትዮጵያን የሚፈውስ ነው»

የአገራዊ ምክክር ኮሚሽን አባል ኮሚሽነር አምባሳደር መሐሙድ ዲሪር

ገጽ 6

"አይቻልምን" የሰበረው የስራ ፈጣሪዋ መንታ ስኬት



ገጽ 13


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

82ኛ ዓመት ቁጥር 273 ሰኔ 3 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10:00

ቅዳሜ

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!




# "የዘንድሮን የአረንጓዴ ዐሻራ ተከላ ስናገባድድ ኢትዮጵያ በ31 ቢሊዮን ችግኞች ትለብሳለች"

- ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)

ሳሙኤል ወንደሰን

አዲስ አበባ፡- የዘንድሮን የአረንጓዴ ዐሻራ ተከላ ስናገባድድ ኢትዮጵያ በ31 ቢሊዮን ችግኞች እንደምትለብስ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ አስታወቁ።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ በትናንትው እለት ከቀዳማዊት እመቤት ዝናሽ ታያቸው እና ከጠቅላይ ሚኒስትር ጽህፈት ቤት ሰራተኞች ጋር በጋራ በመሆን በየካ ተራራ ላይ የአፕል ችግኝ ተክለዋል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ በወቅቱ እንደተናገሩት፤ በዚህ ክረምት በቦታው ላይ ያለውን ባህር ዛፍ በማንሳት 100 ሺህ የአፕል ችግኞችን ለመትከል እቅድ ተይዟል። በባህር ዛፍ የተሸፈነውን ቦታ በአፕል ስንሸፍን

"የዘንድሮን የአረንጓዴ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## ሚኒስቴሩ ከኢፕድ ሥልጠና ውጤታማ የሚያደርገውን አስተምህሮ እንደሚያገኝ አስታወቀ

- ኢፕድ ለልማት ባንክ አመራሮችና ባለሙያዎችም ሥልጠና እየሰጠ ይገኛል

ቃልኪዳን አሳዬ

አዲስ አበባ፡- ተቋማቸው የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ከሚያቀርበው ሥልጠና ውጤታማ የሚሆንበትን አስተምህሮ እንደሚያገኝ የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስትር ዶክተር በለጠ ሞላ ገለጹ፡፡ የኢፕድ የሥልጠና ማዕከል ለልማት ባንክ የሚዲያና ኮሙኒኬሽን አመራሮችና

ሚኒስቴሩ ከኢፕድ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## ከ 6 ነጥብ 25 ሚሊዮን ኩንታል በላይ የአፈር ማዳበሪያ አገር ውስጥ ገብቷል

. ሶስት ሚሊዮን ኩንታል የአፈር ማዳበሪያ በቅርቡ ጅቡቲ ወደብ ይደርሳል

ልጅዓለም ፍቅሬ

አዲስ አበባ፡- እስከ ግንቦት 30 ቀን 2015 ዓ.ም ድረስ ከስድስት ነጥብ 25 ሚሊዮን ኩንታል በላይ የአፈር ማዳበሪያ ወደ አገር ውስጥ መግባቱን የግብርና ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡ በሚቀጥሉት ሶስት ሳምንታት ሶስት ሚሊዮን ኩንታል የአፈር ማዳበሪያ ጂቡቲ ወደብ እንደሚደርስ ተገልጿል።

በግብርና ሚኒስቴር የግብርና ኢንቨስትመንትና ግብዓት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ ዶክተር ሶፊያ ካሳ የአፈር ማዳበሪያ አቅርቦትና ስርጭትን በተመለከተ ትናንትና በሰጡት

ከ 6 ነጥብ 25 ሚሊዮን ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ዶክተር ሶፊያ ካሳ















## ከኤሌክትሪክ ኃይል ሽያጭ ከ83 ሚሊዮን ዶላር በላይ ገቢ ተገኝቷል

ገጽ 4








# በመጀመሪያው ምዕራፍ የአረንጓዴ አሻራ መርሐ ግብር የተገኙ አመርቂ ውጤቶችን ለመድገም በቁርጠኝነት እንደሚሰሩ ርዕሳነ መስተዳድሮች ገለጹ

በጋዜጣው ሪፖርተር



አዲስ አበባ፡- በመጀመሪያው ምዕራፍ የአረንጓዴ አሻራ መርሐ ግብር የተገኙ አመርቂ ውጤቶችን በሁለተኛው ምዕራፍ ለመድገም በተለይ በጥምር ግብርና ላይ በቁርጠኝነት እንደሚሰሩ የክልል ርዕሳነ መስተዳድሮች ተናገሩ።

በሁለተኛው ምዕራፍ የአረንጓዴ አሻራ መርሐ ግብር ማስጀመሪያ መርሃ-ግብር ላይ ተገኝተው አሻራቸውን ያሳረፉ የክልል ርዕሳነ መስተዳድሮች በሰጡት አስተያየት ለዘንድሮው የአረንጓዴ አሻራ መርሐ-ግብር በየክልሎቹ ዝግጅት ተደርጓል ብለዋል።

የኦሮሚያ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቶ ሽመልስ አብዲሳ በመጀመሪያው ምዕራፍ የተገኙ ስኬቶችን ለመድገም በቂ ዝግጅት መደረጉን ነው የጠቀሱት።

በዘንድሮው የአረንጓዴ አሻራ መርሐ ግብር ክልሉ የደን፣ የቡና እና የፍራፍሬ ወይም ጥምር ግብርና ሥርዓትን በመከተል እንደሚያለማ ገልጸዋል።

በክልሉ ከሚተከሉ አጠቃላይ ችግኞች መካከል 1 ነጥብ 3 ቢሊዮን የቡና፣ 50 ሚሊዮን ደግሞ የፍራፍሬ ዝርያዎች ተከላ ቀደም ብሎ መጀመሩን አረጋግጠዋል።

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቶ አሻድሊ ሀሰን በበኩላቸው ከዕቅድ በላይ ማሳካት በተቻለበት በመጀመሪያው ምዕራፍ አረንጓዴ አሻራ መርሐ ግብር ዘርፈ ብዙ ትሩፋቶች አምጥቷል ብለዋል።

ክልሉ የአየር ንብረት መዛባት ተጽዕኖን የሚቋቋሙ ብቻ ሳይሆን የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ችግኞችን ለመትከል ቅድመ ዝግጅት ማጠናቀቁን ነው የተናገሩት።

በተያዘው የክረምት ወቅት ከሚተከሉ ችግኞች ባሻገር ለቀጣይ ዓመት የሚሆኑ ችግኞችን የማፍላት ስራዎች እንደሚከናወኑም ርዕሳነ መስተዳድሩ ገልጸዋል።

በአረንጓዴ አሻራ መርሐ ግብር የህብረተሰቡ ችግኝ የመትከልና የመንከባከብ ባህል መዳበሩን ጠቅሰው፤ በቀጣይ በተለይም ጥምር ደንን ታሳቢ ያደረጉ የአረንጓዴ ልማት ስራዎች ተጠናክረው እንደሚቀጥሉ ተናግረዋል።

የትግራይ ክልል ጊዜያዊ አስተዳደር ርዕሰ መስተዳድር አቶ ጌታቸው ረዳ በበኩላቸው፤ ትግራይ ክልል በአካባቢ ጥበቃ ስራዎች አርዓያነት እንደነበረው አስታውሰው፣ ሆኖም በጦርነቱ የተፈጥሮ ሀብት ስራው መስተጓጎሉን አንስተዋል።

በዚህም የተስተጓጎለውን የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ስራ ለማካካስ በሁለተኛው ምዕራፍ አረንጓዴ አሻራ መርሐ ግብር በስፋት ለማከናወን ቅድመ ዝግጅት መደረጉን ተናግረዋል።

በተመሳሳይ የሀረሪ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቶ ኦርዲን በድሪ፤ ለምግብነት በሚውሉ ችግኞች ላይ በማተኮር በቁርጠኝነት እንደሚሰራ አረጋግጠዋል።

ርዕሳነ መስተዳድሮቹ ሁለተኛው ምዕራፍ በይፋ በተጀመረበት አፋር ክልል የተመለከቱት እምርታ ያመጣ የፍራፍሬ ልማት፤ ኢትዮጵያ ያላትን ዕምቅ አቅም የሚያሳይ እንደሆነ ተናግረዋል።

በተለይም በቆላማ አካባቢዎች ላይ የአመራር ቁርጠኝነት ከተጨመረበት የአየር ንብረት መዛባት ተጽዕኖን መቀነስ ብቻ ሳይሆን የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ እንደሚቻል ጉልህ ማሳያ መሆኑን ጠቅሰዋል።

# አውደ ርዕዩ በአዲስ አበባ ያለውን የትምህርት አሰጣጥ ዕድገት የሚያሳይ ነው

ማህሌት ብዙነህ

አዲስ አበባ፡- የሳይንስና ቴክኖሎጂ ፈጠራ ስራ አውደ ርዕይ በአዲስ አበባ ከተማ ያለውን የትምህርት አሰጣጥ ሁለንተናዊ ዕድገትና ሂደት አጉልቶ የሚያሳይ መሆኑን የአዲስ አበባ ከተማ ትምህርት ቢሮ ገለጸ፡፡

“በሳይንስና ቴክኖሎጂ ፈጠራ የዳበረ ትውልድ ለአገር ብልጽግና!" በሚል መሪ ሃሳብ ለ8ኛ ጊዜ የሚካሄደው ከተማ አቀፍ የተማሪዎች እና የመምህራን የሳይንስና ቴክኖሎጂ ፈጠራ ስራ አውደ ርዕይ ትናንት በወዳጅነት ፓርክ ተከፍቷል፡፡

የአዲስ አበባ ትምህርት ቢሮ ኃላፊ ዶክተር ዘላለም ሙላቱ በመክፈቻ ሥነ ሥርዓቱ ላይ እንደገለጹት፤ ዓውደ ርዕዩ በከተማዋ ያለውን የትምህርት አሰጣጥ ከማሳየት ባለፈ ጤናማ የሆነ የውድድር መንፈስ ለመፍጠር፣ የተማሪዎችንና የመምህራንን የፈጠራ ችሎታና የምርምር አድማስ ልህቀት ለማሳደግ ያግዛል፡፡ የሳይንስና የቴክኖሎጂ የፈጠራ ውጤቶችንም ለከተማዋ ነዋሪዎች ለማሳየትና የተሞክሮ ልውውጥ ለማድረግ ያስችላል፡፡

የከተማ አስተዳደሩ ትምህርት ቢሮ ለሳይንስና ቴክኖሎጂ ትምህርቶች ትኩረት በመስጠት ተማሪዎች በንድፈ ሃሳብ የተማሩትን ትምህርት ወደ ተግባር በመቀየር እንዲመራመሩ የሚያደርጉ ስራዎችን እየሰራ እንደሚገኝ ጠቁመው፤ እነዚህ የፈጠራ ስራዎችም በማህበረሰቡ ዘንድ የሚስተዋሉ ችግሮችን መፍታት እንዲችሉ ቢሮው አስፈላጊ የሆኑ ግብዓቶችን በማሟላት ላይ ይገኛል ብለዋል፡፡

አውደ ርዕዩ የፈጠራ ዝንባሌ ያላቸው ተማሪዎች እና መምህራን የፈጠራ ስራዎቻቸውን የሚያቀርቡበት፤ የሚወዳደሩበት፣ ከባለድርሻ አካላት የሚተዋወቁበት፣ የተወዳዳሪነት ስሜት የሚጎለብትበት እና እውቅና የሚያገኙበት ሁኔታ የሚፈጥር መሆኑንም ጠቅሰዋል፡፡

ተማሪዎችን ዘመኑ ከደረሰበት የሳይንስና የቴክኖሎጂ ማስተዋወቅ የሚጀምረው በትንሿ ቤተ ሙከራና በትምህርት ማበልጸጊያ ማዕከላት መሆኑን አመልክተው፤ በትምህርት ቤቶች የሚገኙ ቤተሙከራዎችና የትምህርት ማበልጸጊያ ማዕከላት ተማሪዎቻቸውን ተግባራዊ ምርምር የሚያደርጉበት፣ በክህሎት የሚያበለጽጉበት ማድረግ ያስፈልጋል። ለዚህም አዲሱ ሥርዓተ ትምህርትም ለሳይንስ እና ቴክኖሎጂ ትምህርቶች ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቷል ብለዋል፡፡

ዶክተር ዘላለም ተማሪዎች በአገሪቱ የሚስተዋሉ ችግሮች ለመፍታት በሳይንስና ቴክኖሎጂ ፈጠራ ስራ ተግተው እንዲሰሩና የሳይንስ ዝንባሌ እንዲያድርባቸው ወላጆችም በየእለቱ ክትትልና ድጋፍ እንዲያደርጉ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል፡፡

ትምህርት ቤቶች ተማሪዎቻቸውን በሳይንስና ቴክኖሎጂ ላይ የተሻለና ተወዳዳሪ የሆነ ክህሎት ይዘው ወደ ሌላው የትምህርት ምዕራፍ እንዲሸጋገሩ ተገቢውን ድጋፍና ክትትል ማድረግ ይኖርባቸዋል ነው ያሉት፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት ዋና አፈ ጉባኤ ወይዘሮ ቡዜና አልቃድር በበኩላቸው፤ አውደ ርዕዩ በትምህርት መስክ የልምድና ተሞክሮ ልውውጥ የሚካሄድበት ነው። የተለያዩ አካላትን ያሳተፈ በመሆኑ የትምህርቱን አሰጣጥ የሚመዘንበትና የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሽግግር የሚካሄድበት ነው ሲሉ ተናግረዋል፡፡



አውደርዕዩ ሲጎበኝ

በአገሪቱ የመጣው ለውጥም በትምህርት መስክ ፍትሃዊ የትምህርት ስርጭት ለማስፈንና የትምህርት ጥራት ለማረጋገጥ እየተሰራ ያለው ስራ ተስፋ ሰጪ ነው። ይህ ትምህርታዊ አውደ ርዕይም ትልቅ ማሳያ ነው ብለዋል፡፡

# የአቅም ማሻሻያው ትምህርት ፈተና ከሰኔ 26 ጀምሮ ይሰጣል

ማህሌት ብዙነህ

አዲስ አበባ ፡- የአቅም ማሻሻያ (ሪሚዲያል ) የትምህርት መርሃ ግብር ፈተና ከሰኔ 26 እስከ ሰኔ 30 ቀን 2015 ዓ.ም ድረስ እንደሚሰጥ የትምህርት ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

በትምህርት ሚኒስቴር የአካዳሚክ ጉዳዮች መሪ ስራ አስፈጻሚ ዶክተር ኤባ ሚጀና ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት ፤ በ2014 ዓ.ም የ12ኛ ክፍል አገር አቀፍ ፈተና ወስደው ከ50 በመቶ በታች ውጤት ላመጡ ተማሪዎች ለመጀመሪያ ጊዜ ለአራት ወራት ያክል ሲሰጥ የነበረው የሪሚዲያል የትምህርት መርሃ ግብርን በማጠናቀቅ ከሰኔ 26 እስከ ሰኔ 30 ቀን 2015ዓ.ም ፈተናው ይሰጣል፡፡

ተፈታኞቹ ከሚማሩበት ዩኒቨርሲቲ ከ30 በመቶ ፈተና የወሰዱ መሆናቸውን አውስተው፤ ቀሪው 70 በመቶ ፈተና ሰኔ 26 ቀን ጀምሮ እስከ ሰኔ 30 ቀን 2015 ዓ.ም በማዕከል የሚሰጥ መሆኑን ተናግረዋል፡፡


የተፈጥሮ ሳይንስ ተማሪዎች ፊዚክስ፣ ሂሳብ፣ ኬሚስትሪ፣ እንግሊዝኛ ፣ ባዮሎጂ የትምህርት አይነቶችን በተከታታይ ከሰኞ እስከ አርብ የሚፈተኑ ሲሆን የማህበራዊ ሳይንስ ተማሪዎች ታሪክ፣ ሂሳብ፣ ጂኦግራፊና እንግሊዝኛ ፈተናዎችን በተከታታይ ከሰኞ እስከ ሀሙስ እንደሚፈተኑ ገልጸዋል፡፡

ዶክተር ኤባ በአቅም ማሻሻያ ፕሮግራሙ 105 ሺህ የመንግሥት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተፈታኞች እንዲሁም 107 ሺህ የግል የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተፈታኞች በድምሩ 212ሺህ ተማሪዎች የትምህርት መርሃ ግብሩ ተጠቃሚ መሆናቸውን ጠቅሰዋል፡፡ ፈተናውም በተመሳሳይ ቀን፣ ሰአትና እኩል የመፈተኛ ጊዜ ይሰጣል ብለዋል፡፡

ተፈታኞች ይህ ዳግመኛ የማይገኝ እድል መሆኑን በመረዳት በትኩረት መስራትና መዘጋጀት ብሎም የዩኒቨርሲቲ ተማሪ ለመሆን መትጋት ይኖርባቸዋል ነው ያሉት፡፡ ለማለፍም በአጠቃላይ ከ50 በመቶ እና ከዛ በላይ ማምጣት እንደሚጠበቅባቸው አሳስበዋል፡፡

በጂንካ ዩኒቨርሲቲ የአቅም ማሻሻያ ትምህርት በመከታተል ላይ የሚገኙት ተማሪ መሰረት ወርቁ እና መቅደስ አለማየሁ እንደገለጹት፤ የተፈጥሮ ሳይንስ ትምህርት የሆኑ አምስት የትምህርት አይነቶችን እየተማሩ ሲሆን በመምህራን የሚቀርቡ የተለያዩ ሞጁሎችን ከማንበብ በተጨማሪ አጋዥ መጽሀፍትን በማጥናት ጭምር ዝግጅት እያደረጉ ነው፡፡


ሌላው በአምቦ ዩኒቨርሲቲ አቅም ማሻሻያ ትምህርቱን እየተከታተለ የሚገኘው ተማሪ ሰመረ አባተ በበኩሉ የተሰጣቸው የትምህርት እድል መልሶ የማይገኝ በመሆኑ ከመቼውም ጊዜ በላይ በትኩረት ትምህርቱን እየተከታተለ እንዳለ ገልጾ፤ ትምህርታቸውን ለማማር በሚያመች መልኩ በዩኒቨርሲቲ ውስጥ መከታተላቸው ጊዜያቸውን በአግባቡ ለመጠቀም ምቹ ሁኔታ መፍጠሩን ተናግሯል። ጥሩ ውጤት ለማምጣትና ወደ ቀጣይ ትምህርት ደረጃ ለመሸጋገርም የተሰጠውን እድል በአግባቡ እየተጠቀመበት እንደሆነ ነግሮናል፡፡




ዶክተር ኤባ ሚጀና

# በደብረ ኤሊያስ በተወሰደው ርምጃ ሰላም በመስፈኑ የግብርና ስራቸውን እያከናወኑ መሆኑን አርሶ አደሮች ገለጹ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**







ባህርዳር፡- በምስራቅ ጎጃም ዞን ደብረ ኤሊያስ ወረዳ መንግሥት በወሰደው የሕግ ማስከበር ርምጃ በአሁኑ ወቅት የአካባቢው ሰላም ተመልሶ የግብርና ስራቸውን እያከናወኑ መሆኑን የአካባቢው አርሶ አደሮች ገለጹ።

በደብረ ኤሊያስ ወረዳ በገዳም ውስጥ የመሸጉ ሽፍቶች በአካባቢው ማህበረሰብ ላይ የፀጥታ ችግር በመፍጠር ሕዝቡ በሰላም እንዳይኖር አድርገውት እንደነበርም ተናግረዋል።

የጸጥታና ደህንነት የጋራ ግብረ ኃይል በቅርቡ በምስራቅ ጎጃም ዞን ደብረ ኤልያስ ወረዳ ሥላሴ ገዳም መሽገው መንግሥትን በትጥቅ ትግል ለመጣል ሲንቀሳቀሱ የነበሩ አካላት ላይ ርምጃ መወሰዱን ገልጾ ነበር።

በወቅቱም በገዳሙ ውስጥ ለውጊያ ሲውል የነበረው ምሽግ መሰበሩንና በ200 ታጣቂዎችም ላይ ርምጃ መወሰዱን የጸጥታና ደህንነት የጋራ ግብረ ኃይሉ አስታውቆ ነበር።

ከጠቅላይ ቤተክህነት፣ ከምስራቅ ጎጃም አገረ ስብከት፣ ከወረዳው ቤተ ክህነት፣ ከዞንንና ከወረዳ የተውጣጡ የስራ ኃላፊዎች 'ብሔረ ብፁን አፄ መልክአ ስላሴ አንድነት ገዳምን ጎብኝተዋል።

በዚሁ ወቅት ኢዜአ ያነጋገራቸው የደብረ ኤልያስ ወረዳ የመቤሽ ቀበሌ ነዋሪ ቄስ መሠረት ሰውነት ለኢዜአ እንደገለፁት በገዳሙ ውስጥ የመሸጉ ሽፍቶች በአካባቢው ማህበረሰብ ላይ የፀጥታ ችግር ፈጥረው ነበር።

ሽፍቶቹ ነፍሰ ጡር እናቶችን ሳይቀር "እንፈጃችኋለን" በማለት በህብረተሰቡ ላይ ስጋት መፍጠራቸውን ጠቁመው የጸጥታ አካላት እርምጃ ከወሰዱ በኋላ የአካባቢው ሰላም መመለሱን ተናግረዋል።

"አሁን ላይ አካባቢው ሰላም በመስፈኑ ወደ እርሻ ስራችን ተመልሰን ለመጪው መኸር ዝግጅት እያደረግን እንገኛለን" ብለዋል።

በወረዳው የጓይ ቀበሌ ነዋሪ አርሶ አደር ሞኝሆድ ጫኔ በበኩላቸው በገዳሙ የነበሩት ሽፍቶች ሰውም ሆነ ከብት ገዳሙ አካባቢው ወደ ሚገኘው በረሃ እንዳይንቀሳቀስ በማድረግ ችግር ፈጥረው ነበር ብለዋል።

"ከአባቶቻችን ጀምሮ የሚታወቀው በገዳም ውስጥ ፀሎት ይደረግበታል፣ ደካማ ይጦርበታል፣ የተጣላ ይታረቅበታል እንጅ በሽፍቶች አስነዋሪ ድርጊት ይፈጸምበታል ተብሎ ታስቦ አያውቅም" ነው ያሉት።

ከአካባቢው ማህበረሰብ መካከል አንድ ሰው የሚፈጽሙት ድርጊት ትክክል አለመሆኑን ከተናገረ ተከታትለው በመግደል መልሰው በገዳሙ ውስጥ ይደበቁ እንደነበረም ተናግረዋል።

ጸረ ሰላም ሃይሎቹ ህዝቡን በጭንቀትና በፍርሃት ውስጥ ከተው የአካባቢው ህብረተሰብ ለከፋ ችግር ተዳርጎ ቆይቷል ብለዋል።

ሽፍቶቹ ወጣቱን ቀርቶ ነፍሰ ጡር ሴቶችን ሳይቀር ለመጨፍጨፍ ቀጠሮ ይዘው ነበረ የሚሉት አርሶ አደሩ ቢሆንም በተወሰደው ርምጃ በአሁኑ ወቅት የአካባቢው ሰላም ተመልሶ የግብርና ስራቸውን በትኩረት እያከናወኑ መሆኑን አስረድተዋል።

ሌላኛው አርሶ አደር አያናው መለሰ በበኩላቸው "ከብቶቻችንን ይዘን ወደ በረሃው ስንወርድ ከብት ጠባቂው እረኛ ሳይቀር ይደበደብ ነበር" የአካባቢው ሰላም ወደ ነበረበት በመመለሱ ከስጋት ነፃ እንደሆኑ ተናግረዋል።

የደብረ ኤልያስ ወረዳ ዋና አስተዳዳሪ አቶ መልካሙ አዲስ በበኩላቸው የስላሴ አንድነት ገዳም በደብረ ኤልያስ ወረዳ ህዝብ በ1992 ዓ.ም ተገንብቶ መንፈሳዊ አገልግሎት ሲሰጥ የቆየ ገዳም መሆኑን አስታውሰዋል።

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በተለያየ ምክንያት የሰው ነፍስ የገደሉ ግለሰቦች ሁሉ ወደ ገዳሙ ገብተው በመደበቅ ወታደራዊ ሥልጠና ሳይቀር ይወስዱ እንደነበር በተለያየ ወቅት በሚደርስ ማስረጃ እንዳረጋገጡ ገልጸዋል።

ከክልሉም ብሎም ከምስራቅ ጎጃም ዞን ችግሩን ለመፍታት ሽማግሌዎችን በመላክ ጭምር ጥረት ቢያደርግም ችግሩ ሳይፈታ ቆይቷል ነው ያሉት።

በተወሰደው ርምጃም የአካባቢው ሰላም በአሁኑ ወቅት ወደ ነበረበት በመመለሱ ህብረተሰቡ ያለ ስጋት የልማት፣ የእርሻና የዘር ስራውን በአግባቡ እንዲያከናውን አስችሎታል ብለዋል ሲል የዘገበው ኢዜአ ነው።

# በመዲናዋ የንግድ ሥርዓቱን ለማስተካከል ርምጃዎች እየተወሰዱ ነው

. በሕገወጥ ጫኝና አውራጆች ላይ ርምጃ ተወስዷል

**አመለወርቅ ከበደ**



ፎቶ ኤዮብ ተፈሪ

አዲስ አበባ፡- በመዲናዋ የሸራ ቤት ንግድ ከፈረሰባቸው መካከል አካል ጉዳተኞችና የኢኮኖሚ ችግር ያለባቸውን በጥናት በመለየት በተለያዩ የንግድ ስራዎች ለማሳተፍና የንግድ ሥርዓቱን ለማስተካከል የተለያዩ ርምጃዎች እየተወሰዱ መሆኑን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስታወቀ፡፡ በከተማዋ ኢ-መደበኛ በሆነ መልኩ ተደራጅተው ሲሰሩ የነበሩ ጫኝና አውራጆች ላይ ርምጃ መወሰዱ ተገልጿል።

የአዲስ አበባ ምክትል ከንቲባ እና የሥራ፣ ኢንተርፕራይዝና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ ኃላፊ አቶ ጃንጥራር አባይ ከሰላምና ጸጥታ እንዲሁም ከንግድ ቢሮ የስራ ኃላፊዎች ጋር በመሆን በከተማ አስተዳደሩ እየተከናወኑ የሚገኙ ስራዎችን በተመለከተ ጋዜጣዊ መግለጫ ሰጥተዋል። አቶ ጃንጥራር አባይ በዚሁ ወቅት እንደገለጹት፤ በከተማዋ ከሸራ ንግድ ቤቶች መፍረስ ጋር ተያይዞ አካል ጉዳተኞችና የተለያየ የኢኮኖሚ ችግር ያለባቸውን በጥናት በመለየት በተለያዩ የንግድ ስራዎች እንዲሰማሩ ይደረጋል።

ምክትል ከንቲባው እንዳስታወቁት ፤ የኢኮኖሚ አቅማቸው ያደጉ ኢንተርፕራይዞችና ግለሰቦች ቀድሞ የያዟቸውን ቦታዎች እንዲለቁ ተደርጓል። የከተማ አስተዳደሩ አዳዲስና የተለቀቁ መስሪያ ቦታዎችን አቅም ላነሳቸውና፣ ስራ ለሌላቸው እንዲሁም ለአካል ጉዳተኞች እንዲተላለፉ ያደርጋል።

በከተማው የስራ አጥነት ችግርን ለመቅረፍ በርካታ ስራዎች እየተሰሩ ቢሆንም፤ የስራ አጥነት ችግር ሊቀረፍ አልቻለም ያሉት አቶ ጃንጥራር፤ በሌላ በኩል ከተማዋ የዓለም ሶስተኛዋ የዲፕሎማሲ መዳረሻ እና የአፍሪካ መዲና እንደመሆኗ ሞዴል እንድትሆን ታቅዶ እየተሰራ ይገኛል ብለዋል፡፡

አቶ ጃንጥራር እንዳሉት፤ እነዚህን ሁለት ተቃራኒ ሃሳቦች አስታርቆ መሄድ ይጠይቃል፡፡ በአንድ በኩል የከተማዋን ውበት መጠበቅ እና በሌላ በኩል ሕጋዊ የሆነ የስራ ስምሪት ውስጥ ሰፋፊ ስራዎችን በመስራት መደበኛ ያልሆኑትን በመደበኛ ስራ በማሰማራት የህብረተሰቡን ጥያቄ መመለስ ይገባል፡፡

በመደበኛው የንግድ አሰራር ለመሰማራት ከፍተኛ መሰረተ ልማት የሚጠይቅ በመሆኑና ይህን ማድረግ ባለመቻሉ በርካታ አካላት መገበኛ ባልሆነ ሁኔታ እየሰሩ ቆይተዋል ያሉት አቶ ጃንጥራር፤ በመሆኑም እነዚህ ኢ-መደበኛ በሆነ መንገድ እየሰሩ እውነተኛ እና ተጨባጭ ችግር ያሉባቸውን አካላት ወደ ሕጋዊነት ለማምጣት በርካታ ስራዎች ሲሰሩ መቆየታቸውን አስረድተዋል፡፡

ኢ-መደበኛ በሆነ መንገድ መስራት የአዲስ አበባ ከተማ ገጽታን ማበላሸት ብቻ ሳይሆን እንደዚህ አይነት ንግዶች እየተስፋፉ የሚመጡ ከሆነ በፖለቲካ፣ ኢኮኖሚ እና ማህበራዊ ጉዳይ ላይ የሚያመጡት ቀዉስ ቀላል አይደለም። በመሆኑም ይህን ችግር ለመቅረፍ የከተማ አስተዳደሩ ጥናቶችን በማድረግ እነዚህን አካላት ወደመደበኛ እና ዘላቂ በሆነ ሥርዓት እንዲገቡ ይደረጋል ብለዋል፡፡

በዚህም ስራ አጦችን ለመርዳት በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለከተማ አንድ ትልቅ ክላስተር ተቀርጾ እየተገነባ ነው። ይህ ክላስተር በአነስተኛ ደረጃ ያሉትን ወደመካከለኛ ለማሸጋገር እድል ይፈጥራል ሲሉ ገልጸዋል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሰላምና ጸጥታ ቢሮ ኃላፊ ወይዘሮ ሊዲያ ግርማ እንደገለጹት፤ በከተማዋ በሕገወጥ መንገድ ተደራጅተው፤ በኢ-መደበኛ አደረጃጀት ታቅፈው ህብረተሰቡን ለእንግልት ሲዳርጉ የነበሩ ጫኝና አውራጆች በሕግ እንዲጠየቁ ተደርጓል፡፡

ከከተማዋ ማህበረሰቦች ለከተማ አስተዳደሩ ከሚደርሱ ቅሬታዎች አንዱ በሕገ ወጥ መንገድ በመደራጀት ከመናኸሪያ እስከ መኖሪያ ሰፈሮች ድረስ ህብረተሰቡን ለእንግለት ሲዳርጉት የነበሩ ጫኝና አውራጆች ጉዳይ እንደነበር ተናግረዋል፡፡

ይህንንም የከተማ አስተዳደሩ በተደጋጋሚ በሚደርሱት ቅሬታዎች እና ባደረገው ጥናት ሊደርስበት ችሏል፡፡ የከተማ አስተዳደሩ ይህን ችግር ለመቅረፍ ከክፍለ ከተማ እስከ ወረዳ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በጋራ ሲሰራ ቢቆይም፤ ችግሩ ሊቀረፍ ባለመቻሉ ህብረተሰቡ ለእንግልት ተዳርጓል ብለዋል፡፡

ሃላፊዋ እንደተናገሩት የሰላምና ጸጥታ ቢሮ ይህንን ችግር ለመቅረፍ ህገወጥ ማህበራትን በማገድ በማህበሩ የሚሰሩ ግለሰቦችን በሕግ ተጠያቂ እንዲሆኑ አድርጓል፡፡

# ከ19 ቢሊዮን ብር በላይ ካፒታል ያስመዘገቡ ባለሀብቶች ወደ ፓርኩ ገብተዋል

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- ከ19 ቢሊዮን ብር በላይ ካፒታል ያስመዘገቡ ባለሀብቶች ወደቡልቡላ የተቀናጀ አግሮ ኢንዱስትሪ ፓርክ መግባታቸውን የኦሮሚያ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን አስታወቀ፡፡

የኦሮሚያ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን ዋና ሥራ አስፈጻሚ ሰናይት መብሬ ከአምስት ባለሀብቶች ጋር በፓርኩ ገብተው ማልማት የሚያስችል ስምምነት በተደረገበት ወቅት እንደገለጹት፤ በቡልቡላ የተቀናጀ አግሮ ኢንዱስትሪ ፓርክ ገብተው ለማልማት ስምምነት ያደረጉ ባለሀብቶችን ጨምሮ ከ40 ሄክታር በላይ መሬት ከ19 ቢሊዮን ብር በላይ ካፒታል ላስመዘገቡ ባለሀብቶች ተላልፏል፡፡

በፓርኩ ውስጥ ገብተው ለማልማት የሚያስችል ፍቃድ ካገኙት ባለሀብቶች መካከል የተወሰኑት የሙከራ ምርት ማምረት ጀምረዋል ያሉት ዋና ሥራ አስፈጻሚዋ፤ ከባለሀብቶች ጋር በተደረገው ስምምነት መሰረትም በቡልቡላ አግሮ ኢንዱስትሪ ፓርክ ከ21 ሄክታር በላይ መሬት ከ9 ቢሊዮን ብር በላይ ላስመዘገቡ አምስት ባለሀብቶች ማስተላለፍ የሚያስችል ነው ብለዋል።

ሁሉም ፕሮጀክቶች ወደ ትግበራ ሲገቡ 10ሺ ለሚጠጉ ዜጎች የሥራ እድል እንደሚፈጥር ጠቁመው፤ በፓርኩ ፓስታ፣ መካሮኒ፣ የምግብ ዘይት፣ የህጻናት አልሚ ምግቦች፣ የእንስሳት መኖ፣ የወተት ውጤቶችን ማቀነባበርን ጨምሮ 12 ዓይነት ምርቶች የሚመረቱበትና የሚቀነባበሩበት መሆኑን ገልጸዋል፤ እነዚህ ሥራዎች ግብርናን በማዘመንና ወደ ኢንዱስትሪ የሚደረገውን ሽግግር በማፋጠን በኩል ትልቅ ሚና እንደሚጫወቱም አመላክተዋል፡፡

በተጨማሪም ከውጭ የሚገቡን ለማተካት በአገር ውስጥ ተኪ ምርቶችን በማምረት፣ የውጭ ምንዛሪ በማስገኘትና ሰፊ የሥራ እድል በመፍጠር በኩልም ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንደሚኖራቸው ጨምረው ገልጸዋል፡፡

የኦሮሚያ ኢንቨስትመንትና ኢንዱስትሪ ቢሮ ኃላፊ አቶ አህመድ ኢድሪስ በበኩላቸው፤ ክልሉ በግብርናው ዘርፍ ያለውን ሀብት በአግባቡ ትቅም ላይ ለማዋል የቡልቡላ የተቀናጀ አግሮ ኢንዱስትሪ ፓርክን ገንብቶ አጠናቆ ወደ ሥራ አስገብቷል፡፡ በነቀምቴም ተመሣሣይ ሥራ በመከናወን ላይ ይገኛል ብለዋል፡፡

ክልሉ ወደ ሥራ ለሚገቡ ባለሀብቶች ብድር በማመቻቸት፣ የሰለጠነ የሰው ሀብትና ጥሬ እቃዎችን እንዲያገኙ ማድረግን ጨምሮ አስፈላጊውን እገዛ እንደሚያደርግ ጠቁመው፤ ራሳቸው ጥሬ እቃዎችን ማምረት ለሚፈልጉ ባለሀብቶችም የኢንቨስትመንት መሬት ለመስጠት ዝግጅት ተደርጓል ነው ያሉት፡፡

የቡልቡላ የተቀናጀ አግሮ ኢንዱስትሪ ፓርክን መንግሥት አስፈላጊ መሠረተ ልማቶችን ማሟላትን ጨምሮ 50 መቶ ኢንቨስት ያደረገበት መሆኑን ጠቅሰው፤ ወደ ፓርኩ የገቡ ባለሀብቶችም በቶሎ ወደ ምርት ገብተው ለሌሎች ባለሀብቶች አርአያ እንዲሆኑ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

ስምምነት የተፈራረሙት ባለሀብቶችም የተረከቡትን ቦታ በአግባቡ በማልማት ወደ ምርት ለመግባትና የሥራ እድል ለመፍጠር ያላቸውን ቁርጠኝነት ገልጸዋል፡፡

ዜና

# በሥነምግባር የታነፁ ተማሪዎችን ለማፍራት ባለድርሻ አካላት ሚናቸውን ሊወጡ ይገባል

**በኃይሉ አበራ**

አዲስ አበባ፡- በመማር ማስተማር ሂደቱ በሥነምግባር የታነፁ ተማሪዎችን ለማፍራት ባለድርሻ አካላት ሚናቸውን ሊወጡ እንደሚገባ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ አስታወቀ።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ የተዘጋጀ ስምንተኛ ከተማ አቀፍ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ፈጠራ ጥናትና ምርምር ጉባዔ ተካሂዷል።

በጉባዔው መክፈቻ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ኃላፊ ዶክተር ዘላለም ሙላቱ እንደገለጹት፤ በሥነምግባር የጎለበተና ሃሳብን በሃሳብ የሚሞግት ትውልድ በመፍጠር ረገድም መምህሩ ተማሪው፣ ወላጅ የትምህርት አመራሩና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ይበልጥ መስራት አለባቸው።

በሥነ-ምግባር የያነጸ ትውልድ ለአገርም ለእራሱም የሚጠቅም ስራ ማከናወን ይችላል ያሉት አቶ ዘላለም፤ አስፈላጊውን ቁጥጥርና ክትትል በማድረግ የተማሪዎች ሥነምግባር እንዲሻሻል መስራት የሁሉም ዜጋ ሃላፊነት ነው ሲሉ ተናግረዋል።

ትውልዱ በዕውቀቱና በክህሎቱ የዳበረ እነዲሆን የሚደረገው ጥረት ተጠናክሮ እንደሚቀጥል የተናገሩት ኃላፊው፤ ተማሪዎች የመማር ማስተማር ሂደቱን በማያውክ ሁኔታ ትምህርታቸውን ተከታትለው ለማጠናቀቅ የሚያስችል ዝግጁነት ሊኖራቸው እንደሚገባ ተናግረዋል።

የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሶስተኛ ዲግሪ የታሪክ ተማሪው ዮሀንስ ተስፋዬ ባቀረቡት የጥናት ጽሁፍ፤ ተማሪ ተኮር የማስተማር ሥነ ዘዴን መከተል ተማሪዎች ሃሳባቸውን በነጻነት እንዲያቀርቡ ከማስቻሉም ባሻገር ምክንያታዊ የሆነ የውይይት ባህልን እንዲያዳብሩ እንደሚረዳ አመላክተዋል።

ወላጆች ለተማሪዎች አነስተኛ ክትትል ማድረጋቸው፣ ትምህርት ቤቱ ያወጣውን ሕግ በመተግበር ረገድ ክፍተት መኖሩ፣ የአዲስ አበባ ትምህርት ቢሮ የተማሪዎች መተዳደሪያ ደንብ ከወቅቱ ጋር የተገናዘበ አለመሆኑ፣ ተማሪዎች ኩረጃ ላይ ማተኮራቸው የተማሪዎችን የሥነምግባር ሁኔታውን እንዳበላሸው ጠቁመዋል።

ለመፍትሄው የተማሪዎችን ሥነምግባር ለማሻሻል የትምህርት አመራሩ ቅጣት ላይ ብቻ አለማተኮር፣ መምህራንና ወላጆች ከተማሪዎች ጋር በበቂ ሁኔታ መወያየትና የትምህርት ቤት ግብዓቶችን ማሻሻል፣ እንደሚገባቸው አስረድተዋል።

በመድረኩ የተማሪዎችን ሥነምግባር ለማሻሻል የሚረዱ ምክረሃሳቦች የቀረቡ ሲሆን፤ ተማሪዎችም ለትምህርት ቤታቸው ሕግና ደንብ ተገዢ እንዲሆኑ ይበልጥ መስራት እንደሚገባ ተገልጿል።



ዶክተር ዘላለም ሙላቱ

# ከኤሌክትሪክ ኃይል ሽያጭ ከ83 ሚሊዮን ዶላር በላይ ገቢ ተገኝቷል

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- ባለፉት አስር ወራት ወደ ጎረቤት አገራት ከተላከ የኤሌክትሪክ ኃይል ሽያጭ ከ83 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር በላይ ገቢ መገኘቱን የኢትዮጵያ ኤሌክትክ ኃይል አስታወቀ፡፡

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል የኮሙኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ ሞገስ መኮንን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ባለፉት አስር ወራት ወደ ጎረቤት አገራት ከተላከ የኤሌክትሪክ ኃይል ሽያጭ 83 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር በላይ ገቢ ተገኝቷል፡፡ አፈጻጸሙ የአስር ወራቱን እቅድ 82 በመቶ የሚሸፍን ነው፡፡

አሁን ላይ ኢትዮጵያ የኤሌክትሪክ ኃይል እየላከች የምትገኘው ወደ ሦስት አገራት መሆኑን ያስታወሱት አቶ ሞገስ፤ በዚህም ወደ ጂቡቲ ከተላከው ኃይል 34 ነጥብ 66 ሚሊዮን ዶላር፣ ወደ ሱዳን ከተላከው 28 ነጥ 73 ሚሊዮን ዶላር የተገኘ ሲሆን፣ ወደ ኬንያ ከተላከ የኤሌክትሪክ ኃይል ደግሞ 19 ነጥብ 6 ሚሊዮን ዶላር የውጭ ምንዛሪ መገኘቱን ጠቅሰዋል፡፡

እንደ ዳይሬክተሩ ገለጻ፤ ወደ ኬኒያ የሚላከው ኃይል በአንዳንድ ምክንያቶች መዘግየቱና ህዳር ላይ ሥራው ከተጀመረ በኋም የሁለት ወራት የሙከራ ጊዜ ስለነበር በታቀደው ልክ ገቢ እንዳይገኝ አድርጓል፡፡ አሁን ላይ ግድቦች የተሻለ ውሃ ስለያዙና የተሻለ ኃይልም ማመንጨት የሚቻልበት ሁኔታ ስላለና የሙከራ ሥራው ተጠናቆ ወደ ሙሉ ሽያጭ የተገባበት ጊዜ ስለሆነ በቀጣይነት የተሻለ ገቢ ለማግኘት ያስችላል፡፡

በርካታ አገራት ከኢትዮጵያ የኤሌክትሪክ ኃይል ለመግዛት ፍላጎት እያሳዩ መሆኑን ጠቅው፤ ከእነዚህ አገራት ጋር ንግግሮችና በባለሙያዎች ደረጃ መሠራት ያለባቸው የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች መጀመራቸውን ገልጸዋል፡፡

ኬኒያን ጨምሮ ከኢትዮጵያ በስተደቡብ ያሉ ሌሎች አገራት የኤሌክትሪክ ኃይል ለማድረስ የሚያስችል መሠረተ ልማት በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ መሠራቱን አስታውሰው፤ የኢትዮ-ኬኒያ የ500 ኪሎ ቮልት ማስተላለፊያ መስመር እስከ ሁለት ሺህ ሜጋ ዋት ድረስ ኃይል ማስተላለፍ የሚችል ነው፡፡ ከኬኒያ ጋር አሁን ያለው ስምምነት ደግሞ እስከ 400 ሜጋ ዋት ኃይል ድረስ ማስተላለፍ የሚያስችል ነው ብለዋል።፡

በመሆኑም ይህ መሠረተ ልማት ብዙ ሥራ ሊሠራበት የሚችል በመሆኑ ግንኙነት ከተጀመረባቸው በታችኛው አገራት ጋር ያሉ ውይይቶችና የሚኖሩን ስምምነት ታሳቢ አድርጎ ይህን መስመር ወደ ሌሎች አገራት ኃይል ለማስተላለፍ መጠቀም ይቻላል ብለዋል፡፡

ከደቡብ ሱዳን ጋር ኃይል ማስተላለፍ የሚያስችል ውይይት መጀመሩን ጠቁመው፤ ውይይቱ እንደተጠናቀቀና የባለሙያዎች ቡድን የሚያመጣው ምክረ ሃሳብ በኃላፊዎች ደረጃ ተገምግሞ ከጸደቀ በኋላ ተግባራዊ ሥራ ይጀመራል። በተመሳሳይ ወደ ሶማሌ ላንድም ኃይል ለመላክ እቅድ አለ ሲሉ ተናግረዋል፡፡

ይሁን እንጂ ንግግርና በባለሙያዎች ደረጃ መሠራት ያለባቸው የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች ቢቀጥሉም እስካሁን ድረስ ወደ ደቡብ ሱዳንም ሆነ ወደ ሶማሌ ላንድ የተጀመረ ተግባራዊ ሥራ እንደሌለ አቶ ሞገስ ጨምረው ገልጸዋል፡፡

# ሚኒስቴሩ ከኢፕድ...

**ከ1ኛው ገፅ የዞረ**

ባለሙያዎችም ሥልጠና እየሰጠ ይገኛል፡፡

"ትጋት፣ ዕውቀት፣ ፈጠራና ትብብር ለውጤት" በሚል መሪ ሃሳብ በኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የሥልጠና ማዕከል ለኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር አመራሮች ሥልጠና መስጠት ተጀምሯል።

የሥልጠና መርሀ ግብሩን በንግግር የከፈቱት የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስትሩ ዶክተር በለጠ ሞላ እንደተናገሩት፤ ተቋሙ ከመንግሥት የሚሰጠውን ሃላፊነት በመወጣት ውጤት በማምጣት የራሱን መገለጫ መገንባት የሚያስችል ሥልጠና ያስፈልገዋል፡፡

ኢፕድ ከሚሰጠው ሥልጠና እኛን የሚያንፅና ተቋማችንን ውጤታማ ሊያደርግ የሚችል አስተምርሆት እናገኛለን፤ ከተቋም ስራ ውጪም ቢሆን እንደ ሰው እንዴት መኖርና መስራት እንዳለብን የሚረዳ ዕውቀት እናገኛለን ብለዋል፡፡

አገር የሚያድገው ሰዎች ከውስጣቸው ያለውን ችሎታ አውጥተው መጠቀም ሲችሉ ነው ያሉት ዶክተር በለጠ፤ ዕውቀትና ጥበብን ከተሻሉት በመማር ሰራተኛውም ሆነ ተቋሙ የተሰጣቸውን ተልዕኮ በላቀ ውጤት እንዲፈጽሙ የሚኖረው ሚና ከፍተኛ ነው ሲሉ ተናግረዋል።

እንደ ሚኒስትሩ ገለጻ፤ ተቋም ከተሰጠው ተልዕኮ አንጻር ለማህበረሰቡና ለአገር የላቀ አገልግሎት ማድረግ እንዲችል ሰራተኛው ተገቢ ዕውቀት መያዝ ይኖርበታል።

ትጋት ያለው፣ የነቃ፣ ለመለወጥ፣ በጎ ነገር ለማድረግ የተዘጋጀና ዕውቀትና ክህሎትን በአንድ ላይ ያነገበ ሰራተኛ ሲገኝ በተቋሙና በአካባቢው አዎንታዊ ሚና መወጣት ይችላል፤ በዚህ ረገድ የኢፕድ ሥልጠና አቅምንና ክህሎትን በማሳደግ ውጤታማ እንደሚያደርግ ይጠበቃል ብለዋል።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈፃሚ አቶ ጌትነት ታደሰ በበኩላቸው፤ ድርጅቱ የሥልጠና ማዕከል ከፍቶ መስራት ከጀመረ አጭር ጊዜ ቢሆንም ለተለያዩ ተቋማት ትልልቅ የሚባሉ ሥልጠናዎችን መስጠት እንደተቻለ ተናግረዋል።

ድርጅቱ አገራዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ በፌዴራልና በክልል ደረጃ ያሉ ተቋማትን ጭምር በማስተባበር ሥልጠናዎችን በመስጠት ላይ እንደሚገኝ ገልጸው፤ ከምርመራ ጋዜጠኝነት ጋር በተያያዘ ለፌዴራልና ለክልል የሚዲያና ኮሙኒኬሽን አመራሮችና ባለሙያዎች ሥልጠና መስጠቱን በአብነት አንስተዋል።

ተቋሙ የተለያዩ የሪፎርም ስራዎችን በመስራት በሚዲያና ኮሙኒኬሽን ዘርፍ እየታዩ ያሉ ክፍተቶችን ለመሙላት ጥረት እያደረገ ይገኛል ያሉት አቶ ጌትነት፤ በተለያዩ ጊዜያት ከ70 በላይ ለፌዴራልና ለክልል ተቋማት ሥልጠናዎችን መስጠት እንደተቻለ አመላክተዋል።

ሥልጠናው ተጠናክሮ እንደሚቀጥል የተናገሩት ዋና ስራ አስፈጻሚው፤ የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ከሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ጋር ያለውን ሁሉን አቀፍ ትብብር በማጠናከር በቀጣይ ሌሎች ስራዎችንም በጋራ እንደሚሰራ ጠቁመዋል። ትናንትና የተጀመረው ሥልጠና ለስድስት ተከታታይ ቀናት እንደሚቆይ ተገልጿል።

በተያያዘም የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የሥልጠና ማእከል ለልማት ባንክ የሚዲያና ኮሙኒኬሽን አመራሮችና ባለሙያዎች ሥልጠና እየሰጠ ይገኛል። ሥልጠናው በሚዲያና ኮሚኒኬሽን ዘርፍ ያለውን ክፍተት የሚሞላ መሆኑ ሰልጣኞቹ ገልጸዋል፡፡

ሥልጠናው በካሜራ አጠቃቀም ፣ በፎቶና ቪዲዮ ኤዲቲንግ፣ በግራፊክስ ዲዛይንና በሌይአውት እርእሶች እየተሰጠ ይገኛል።

በሥልጠናው ተሳታፊ የሆኑት በኢትዮጵያ ልማት ባንክ የሚዲያና ኮሚኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ የአብስራ ከበደ እንደገለጹት ሥልጠናው በዘርፉ የሚኖሩ ክፍተቶችን የሚሞላ ነው፡፡

የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ለደንበኞቹ መረጃን ለማድረስ የህትመትና የምስል ስራዎች ጥራታቸው ተጠብቆ እንዲደርስ በዘርፉ የሚሰሩ ባለሙያዎች ክህሎታቸው ከፍ ያለ ሊሆን እንደሚገባ ጠቅሰው ሥልጠናውም በዚህ ዙሪያ ያሉ ክፍተቶችን ለመሙላት የሚያግዝ ይሆናል ብለዋል፡፡

ሌላኛው በኢትዮጵያ ልማት ባንክ የሚዲያና ኮሙኒኬሽን ባለሙያ አቶ ተመስገን መንግሥቴ ሥልጠናው ባለሙያው በሚዲያው ከዚህ በፊት ያሉ እውቀቶችን ለማስታወስና የበለጠ ለማዳበር የሚረዳ በመሆኑ ለባለሙዎች ትልቅ ጠቀሜታ የሚኖረው ነው ብለዋል፡፡

የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ከሚዲያና ኮሙኒኬሽን ዘርፍ ከህዝብ ግንኙነት ስራ በተጨማሪ ሳምንታዊ የቴሌቪዥን ፕሮግራም፣ የሬድዮ ፕሮግራም እንዲሁም በሶሻል ሚዲያ የተለያዩ ስራዎችን የሚሰራ ዘርፍ በመሆኑ ሥልጠናው የበለጠ ብቁ እንዲሆኑና አቅማቸውን የሚሳድግላቸው መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡

# "የዘንድሮን የአረንጓዴ...

**ከ1ኛው ገፅ የዞረ**

አንደኛ አርንጓዴነቱን አይለቅ፤ ሁለተኛ አካባቢው ምግብ የሚፈራበት ቦታ ይሆናል። በሌላ በኩል ደግሞ የሥራ እድል ለመፍጠር ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል ብለዋል።

በሌሎች ቦታዎች ደግሞ ብርቱካን፣ መንደሪን እና ሌሎች ፍራፍሬዎች የሚተከሉ ከሆነ ከሶስትና አምስት ዓመታት በኋላ በምግብ ዋስትና ዙሪያ ለሚነሱ ጉዳዮች መፍትሄ ለመስጠት ምቹ ሁኔታዎች ይፈጠራሉ። ከዚህም ባለፈ ቦታው ለገቢ ምንጭነት ያገለግላል ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ በዘንድሮ የአረንጓዴ ዐሻራ ተከላ ኢትዮጵያ በ31 ቢሊዮን ችግኞች እንደምትለብስ ተናግረዋል።

በሚቀጥሉት አራት ክረምቶች 50 ቢሊዮን ችግኞችን መትከል ይቻላል። ከዚህ ውስጥ ሶስት ቢሊዮኑ የሚበላ ከሆነ እንደአገር የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ በሚሰራው ሥራ ከፍተኛ ውጤት ማስመዝገብ እንደሚቻል ገልጸው፤ ከዚህ በፊት ሰው ማስተባበር፣ ችግኝ ማዘጋጀት እና ቆፍሮ መትከል ችግር ነበር። አሁን ግን ብዙ ሰው በየቤቱ ችግኝ መትከል በመጀመሩ የአረንጓዴ ዐሻራ መርሃ ግብሩን በእውቀት ማድረግ ያስፈልጋል ብለዋል።

እንደ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ገለፃ፤ በእውቀት ሲባል አንደኛ የሚተከለው ችግኝ የሚበቅል፣ አካባቢ የማይጎዳ፣ ከሶስት ዓመት በኋላ የሚበላ መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል። የሚተከለው ችግኝ አካባቢን የሚጠብቅና የሚያስውብ ብቻ ሳይሆን ሥራ የሚያሲዝ እና ምግብ የሚሆን መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል።

አሁን ላይ በአቡካዶ ምርት ኢትዮጵያ ከአፍሪካ ሁለተኛ ሆናለች። በቀጣይ በአርንጓዴነት፣ በፍራፍሬና በምግብ ራስን በመቻል ጉዳዮች ሁለተኛና ሶስተኛ የሚባለውን መቀልበስ አለብን። ምክንያቱም ኢትዮጵያ ይህንን ለማድረግ ከበቂ በላይ ሀብት ያላት አገር ነች። ስለዚህ ጨክኖ በመሥራት መለወጥ ያስፈልጋል ብለዋል።

በዚህ ጉዳይ የፖለቲካ ልዩነት፣ ወቅታዊ አጀንዳዎች፣ የሀብት ጉዳይ ሁሉ ትርጉም የለውም። ይህን የሚሰራ ለነገ ትውልድ የሚሰራ በመሆኑ ለትውልድ መሰረት ለመትከል መንግሥት ስለማይመቸን ነው የሚል አስተሳሰብ ትክክል አይደለም፤ ሊታረም ይገባል። ዛሬን በመቀየም የነገ ትውልድን ማስቀየም አይገባም። አሁን ያለውን ጉዳይ በመግባባት፣ በእርቅና በካሳ መፍታት እንጂ ለቀጣዩ ትውልድ ችግርን ማስተላለፍ አይገባም ነው ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ።

የቀድሞ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ችግር ዛሬን እንድንቸገር አድርጎናል። እኛም በተመሳሳይ መንገድ ለትውልድ ችግር እንዳናወርስ ጥንቃቄ ማድረግ አለብን ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ አሁን የምንሰራው ሥራ ለሀገርና ለትውልድ የሚጠቅም መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል። በዚህ እሳቤ የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብርን ማስቀጠል ይገባል ብለዋል፡፡

# ከ 6 ነጥብ 25 ሚሊዮን...

**ከ1ኛው ገፅ የዞረ**

መግለጫ፤ ከስድስት ነጥብ 25 ሚሊዮን ኩንታል በላይ የአፈር ማዳበሪያ ወደ አገር ቤት መግባቱን አስታውቀዋል።

የአርሶ አደሩን የአፈር ማዳበሪያ ፍላጎት ለማርካት ከጅቡቲ ወደብ ወደ አገር ቤት ከገባው በተጨማሪ በቀጣዮቹ ሶስት ሳምንታት ከሶስት ሚሊዮን ኩንታል የአፈር ማዳበሪያ የጫኑ አምስት መርከቦች ጅቡቲ ወደብ እንደሚደርሱ አመላክተዋል፡፡

ወደአገር ውስጥ ከገባው ባለፈ ካለፈው በጀት ዓመት የተረፈ ሁለት ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ኩንታል ማዳበሪያ ጋር በድምሩ ስምንት ነጥብ አራት ሚሊዮን ኩንታል ማዳበሪያ መቅረቡን ተናግረዋል።

ወደአገር ከገባው ማዳበሪያ ሰባት ነጥብ አምስት ሚሊዮን ኩንታሉ ከማዕከላዊ መጋዘን ወደ መሰረታዊ ህብረት ስራ ማህበራት ተጓጉዞ ከ5 ነጥብ 7 ሚሊዮን ኩንታል በላይ የሚሆነው ማዳበሪያ ለአርሶ አደሩ መሰራጨቱን ጠቁመዋል።

ሁለት ነጥብ ሰባት ሚሊዮን ኩንታል ማዳበሪያ ደግሞ በተለያዩ የህብረት ስራ ማህበራት መጋዘን እንደሚገኝ አስታውቀዋል።

በበጀት ዓመቱ አጠቃላይ ግዢ የተፈጸመበት 12 ነጥብ 8 ሚሊዮን ኩንታል ማዳበሪያ እስከ ሰኔ 30 ቀን 2015 ዓ.ም ወደአገር ውስጥ እንደሚገባ አመላክተዋል።

ግዢ ከተፈጸመለት 12 ነጥብ 8 ሚሊዮን ኩንታል ውስጥ አምስት ሚሊዮን ኩንታሉ ዩሪያ ማዳበሪያ መሆኑን ጠቁመው፤ ቀሪው ዳፕ የተሰኘው ማዳበሪያ መሆኑን አስረድተዋል።

በሚቀጥሉት 3 ሳምንታት ከ3 ሚሊዮን ኩንታል በላይ የአፈር ማዳበሪያ የጫኑ አምስት መርከቦች ጅቡቲ ወደብ እንደሚደርሱ ገልጸዋል።

የአፈር ማዳበሪያ ከአርሶ አደሩ ቀድሞ ወደ ነጋዴው እጅ እንዳይገባ ከፍተኛ ቁጥጥር እየተደረገ ይገኛል ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ ክልሎች በመጋዘን ያለውን የአፈር ማዳበሪያ ለአርሶ አደሩ በፍጥነት እንዲያሰራጩ አሳስበዋል።

ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የአርሶ አደሩን የአፈር ማዳበሪያ ክፍተት ለመሙላት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በትኩረት እየሰራ ነው ሲሉ ዶክተር ሶፊያ ተናግረዋል።

ሚኒስትር ዴኤታዋ እንደገለጹት፤ የመንገድ ችግርና የህብረት ስራ ማህበራት የስርጭት ጉድለት የማዳበሪያ እጥረት እንዲከሰት በማድረጉ አፋጣኝ መፍትሄ መስጠት ያስፈልጋል።

# አገልግል

## የቅዳሜ መጽሔት



**‹‹አገራዊ ምክክር በራሱ ኢትዮጵያን የሚፈውስ ነው››**

የአገራዊ ምክክር ኮሚሽን አባል ኮሚሽነር አምባሳደር መሐሙድ ዲሪር

ገጽ 6



**“አይቻልምን” የሰበረው የስራ ፈጣሪዋ መንታ ስኬት**

ገጽ 13



**ተወዳዳሪ የኮንስትራክሽን ኩባንያዎችን መፍጠር - ቀጣዩ የዘርፉ አብይ ተግባር**

ገጽ 14

ባህል፣ ኪነ ጥበብ እና ቱሪዝም ቢሮ
አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

**ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ባህል፣ኪነጥበብ እና ቱሪዝም ቢሮ ጋር በመተባበር በየሳምንቱ የሚታተም**

**አፍሪካዊቷ መልህቅ**

# ምክንያታዊ እልህ ለአገር እድገት ያለው ፋይዳ

**ኃይለማርያም ወንድሙ**

የአዲስ አበባ ባህል፣ ኪነ-ጥበብና ቱሪዝም ቢሮ "እልህን እንዴት በምክንያታዊነት እንግራ" በሚል ርዕሰ ጉዳይ ልዩ የሃሳብ መዋጮ መድረክ ከሰሞኑ አዘጋጅቶ ነበር፡፡ አንዱ የሰው ልጅ የስሜት ነጸብራቅ የሆነውን "እልህን" የመድረኩ አወያዮቹ በሳይንሳዊ፣ በመንፈሳዊ፣ በባህል እንዲሁም በፍልስፍና አተያይ ቃኝተውታል፡፡

እልህን ከፍልስፍና አኳያ የቃኙት በኮተቤ ዩኒቨርሲቲ የፍልስፍና መምህር አቶ ፍሬዘር ብርሃኑ እንደገለጹት፤ እልህ አወንታዊና አሉታዊ ጎን አለው። ባልተገራ እልህ ተነሳስቶ አፀፋዊ ምላሽ መስጠት ወይም ቂም በቀልን መወጣት አሉታዊ ጎን ነው። ምክንያቱም ሙሉ ደስታን አይሰጥም። ጸጸትን ያመጣል። የማይጠገኑ ስብራትን ሊያስፈጽም ይችላል፡፡ በአንጻሩ ጠንክሮ ሠርቶ ወደ ተሻለ ደረጃ ለመቀየር የሚያነሳሳ የተገራ እልህ "ትጋት"ብሎ መግለጽ ይቻላል። ይህም ወደ ተሻለ ምዕራፍ የሚያሻግር አወንታዊ ጎን ነው።

እልህ ውስጣዊ እንደሆነ የሚናገሩት መምህር ፍሬዘር፤ እያንዳንዱ ሰው የሚያንጸባርቅበት መንገድ ይለያል እንጂ ሰው በመሆናችን ብቻ እልኸኞች ነን፡፡ የግሪክ ፈላስፋ ፕላቶ እልህ ስጋዊ ፣ ወኔያዊ ፣መንፈሳዊ እያለ ይገልጸዋል፡፡ ስጋዊው ከመብላት ከመጠጣት ጋር፤ ወኔያዊው ከንዴት፣ ከቁጭት ጋር፤ መንፈሳዊው ደግሞ ከጥበብ፣ ከዕውቀት ጋር የሚያያዝ ነው፡፡ ስለዚህ እነዚህ ሦስት አካላት መስማማትና መዋሀድ አለባቸው ሲባል፤ እልህን በምክንያታዊነት ልንመራውና ልንገራው ይገባል ማለት እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡

ምክንያታዊ እልህ ደግሞ አገርን ወደ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ያሻግራል፤ ዴሞክራሲ እንዲጎለብትም ይረዳል፡፡ ተቀራርቦ መነጋገርን፣ መደራደርን፣ ወዘተ. ያበረታታል፡፡ እልህ፣ ጀግንነት፣ ቁጭት በአወንታዊ መንገድ ከተገለገልንባቸው ለሰው ልጆች በጣም ወሳኝ ነገሮች ናቸው፡፡ እንድንለወጥ፣ የተሻለ ደረጃ እንድንደርስ ኃይል የሚሠጡ ናቸው። በተቃራኒው በአሉታዊ መንገድ ከተጠቀምንባቸው ደግሞ ቂም በቅልና ጥላቻን የሚወልዱ፤ ነገን የሚያበላሹ ናቸው።

አርስቶትል እንደሚለው፤ ከልክ በላይ የሆነ እልህ መልካሙን ሰው አውሬያዊ ጠባይና ማንነት ሊያላብሰው ይችላል፡፡ ጊዜያዊ ዕብደት ሊስተዋልበት ይችላል። ያልተገራ እልህ ጽንፈኝነት ነው፡፡ በአገረ መንግሥቱ ግንባታ ላይ ከፍተኛ ችግር ይፈጥራል። ከመጠን ያለፈ እልህኝነት በፖለቲካ ልሂቃኖቻችን ላይ ይስተዋላል፡፡ በዚህም በተለይ የፖለቲካ ልሂቃኑ ተቀራርቦ የመነጋገር፣ የመወያየት፣ የመደማመጥ፣ ወዘተ ባህላቸው የቀጨጨው ከመጠን ባለፈ እልኸኝነት ነው። ሆኖም እልህ በጣም ሲያንስ ሰዎችን ቸልተኛ ባህሪ ያላብሳቸዋል፣ ለሥራ ያላቸው ተነሳሽናትና ቁርጠኝነት የወረደ እንደሚሆን መምህሩ ይናገራሉ።

በሌላ በኩል ከባህልና ኃይማኖታዊ ዕሴቶቻችን አኳያ እልህን የቃኙት ዑስታዝ በድሩ ሁሴን በበኩላቸው፤ እልህ ምክንያታዊነትን ከሳተ ሌላውን ብቻ ሳይሆን እራስንም ያጠፋል፡፡ "አምላኬ ሆይ ተሟጋቼን አዋቂና ምክንያታዊ አድርግልኝ፤ በእልህ አካሄድ እኔን የጎዳ መስሎት እራሱንም እንዳይጎዳ" የሚል አባባል አለ። ምክንያቱም አንዳንዴ ከበታችነት ስሜት የተነሳ ተገዳዳሪ ለመሆን በስሜት የሚደረጉ ነገሮች አሉ። ኃይማኖታዊ አስተምህሮቱ ላይ ይህንኑ ሁኔታ ‹‹የመሃይማን ወገንተኝነት›› ብሎ ቁርአን ይገልጸዋል። በወገንተኝነትና በወኔ ከእውነት በተቃራኒው መቆም በቁርአን እጅግ በጣም የተወገዘ ነው፡፡ በአንጻሩ ይህንን ቁርአን ‹‹ሰኪና›› ይለዋል፡፡ ማለትም መረጋጋት፣ መስከን፣ በራስ መተማመን፣ ሃሳብን በሃሳብ መመከት፣ የውስጥ መረጋጋት፣ ወዘተ. ሊኖረን እንደሚገባ ቁርአኑ ይመክራል፡፡

እውነቱን ክዶ ከእውነት በተቃራኒው የምናሳያቸው እልኸኝነት እና ሞገደኝነት ከውስጥ መሸነፍም ጋር ይገናኛሉ፡፡ ይህ አይነት ሰው ደግሞ በኃይል፣ በሞገድ ብቻ የሚሄድ ምክንያታዊ ያልሆነ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ጨካኝ ሞገደኛ የሆነና መጨረሻው እፍረት እንደሆነ ቁርአኑ ያስተምራል ይላሉ፡፡

በኩረ ትጉሃን ጥበቡ በለጠ በበኩላቸው እልህ ከማኅበራዊና ፖለቲካዊ ዕይታ ቃኝተውታል፡፡ የችግራችን ሰንኮፍ ያለው እልህ ላይ ነው፡፡ ሉዓላዊነታችን ለረጅም ዓመታት ሳይደፈር የፀናው በምክንያታዊ እልህ ነው፡፡ በእልህ የአገራችን ዳር ድንበር ከማስከበር አልፈን ጭቆና ውስጥ ለነበሩ በተለይ ለአፍሪካ አገሮች የነጻነት ተምሳሌት ለመሆን የበቃንበት አኩሪ ታሪክ አለን። የዓድዋ፣ የካራማራ ድል በምክንያታዊ እልህ የተገኘ ነው፡፡ በደርግ ዘመነ መንግሥት በምክንያታዊ እልህ በተካሄደው የመሰረተ ትምህርት ዘመቻ ብዙ ዜጎች ከመሃይምነት ተላቀው ማንበብና መፃፍ የቻሉበት ነው፡፡

ሆኖም ከንጉሡ ዘመነ መንግሥት ውድቀት በኋላ ላለፉት 50 ዓመታት በሴራ ፖለቲካ በመጠላለፍ እንዲሁም በእልህ በቀይሽብርና ነጭ ሽብር አያሌ ዜጎች ተቀጥፈዋል። በአገሪቱ ስደት፣ ሞት፣ ድህነት፣ መፈናቀል ነግሷል። አንዱ ሂዶ ሌላው ሲተካ ያለውን ጥሩ ነገር አስቀጥሎ የጎደለውን መሙላት ሲገባው ሁሉንም ይንዳል። የአንድ እናት ልጆች በጠላትነት ተፈራርጀ እርስ በእርስ ከመዋጋት ይልቅ ለአንድ አገር እድገትና ሰላም ተቀራርቦ የመወያየትና መደራደር ባህሉ ባለመኖሩ ስንቶች እንደቅጠል እረግፈዋል። አገር ጉዟዋ ከድጡ ወደማጡ ሆኗባት ትገኛለች። በጥቅሉ የእልህ ፖለቲካ አገርና ህዝብን እንደጎዳ ይናገራሉ፡፡

ስለዚህ እንደዜጋ ኢትዮጵያ ከድህነት፣ ከድርቅ፣ ከጦርነት ወዘተ. ለምን አትውጣም? የሚል ቁጭት መጫር፣ የአስተሳሰብ ለውጥ ሊመጣ የሚችልበትን ምህዳር መፍጠር ያስፈልጋል። መገናኛ ብዙሃንም እንዴት ነው? ዜጋው ወደ ልማት እንዲገባ የማነሳሳው የሚለውን በቁጭትና በወኔ መሥራት አለባቸው፡፡ ፖለቲከኞችም ዜጋው ከድህነት፣ ከእርዳታ እንዲወጣ አድርገነዋል ወይ? ብለው መጠየቅ አለባቸው፡፡ እንዲሁም ህብረተሰቡ ከጦርነት አዙሪት ተላቆ ፊቱን ወደ ሰላምና ልማት ለማዞር በቁጭት መነሳት እንዳለበት በኩረ ትጉሃን ጥበቡ ገልጸዋል፡፡

በኩረ ትጉሃን ጥበቡ አያይዘውም የሕዳሴ ግድብ፣ አረንጓዴ አሻራ እንዲሁም አዲስ አበባ ላይ (እንጦጦ ፓርክ፣ ሳይንስ ሙዚየም፣ ወዳጅነት፣ አንድነት ፓርክ፣ ወዘተ.) በምክንያታዊ እልኸኝነትና በቁጭት የተሠሩ ልማቶች በአገሪቱ የቱሪስት የቆይታ ጊዜን በእጅጉ የሚያራዝሙ፣ የአገርን ብሎም የከተማዋን ገፅታ የሚገነቡ እንደሆነ ጠቁመዋል፡፡

## የዘመን እንግዳ

# ‹‹አገራዊ ምክክር በራሱ ኢትዮጵያን የሚፈውስ ነው››

*የአገራዊ ምክክር ኮሚሽን አባል ኮሚሽነር*
*አምባሳደር መሐሙድ ዲሪር*

ምሕረት ሞገስ



በምክር ቤት አባልነት፣ በአምባሳደርነት፣ በሚኒስትርነት፣ በከፍተኛ አማካሪነት፣ በኢጋድ አስተባባሪነት፣ በሱዳን ልዩ መልዕክተኛነትና በአፍሪካ ቀንድ አካባቢ በዲፕሎማሲው መስክ ሰፊ ልምድ እና ዕውቀት ያላቸው ናቸው: - አምባሳደር መሐሙድ ዲሪር ጌዲ።

በዓለም አቀፍ ሕግ የሁለተኛ ዲግሪያቸውን የተከታተሉት እኚሁ አምባሳደር፤ በግብጽ የኢትዮጵያ አምባሳደር ሆነው አገልግለዋል። በዚምባብዌም በተመሳሳይ መልኩ ለዓመታት የኢትዮጵያ አምባሳደር ነበሩ። አምባሳደር መሐሙድ ድሪር የተለያዩ ተቋማትንም ሚኒስትር ሆነው መርተዋል። የባሕልና ቱሪዝም ሚኒስትር በነበሩበት ወቅት የአክሱም ሐውልት ወደ ኢትዮጵያ እንዲመለስ በተደረገው አገራዊ እንቅስቃሴ ሰፊ ጥረት በማድረግ የአስመላሽ ኮሚቴ አባል ሆነው ለተጫወቱት ከፍተኛ ሚና መንግሥት ሽልማት አበርክቶላቸዋል።

ሽልማታቸው ይህ ብቻ አይደለም። በሱማሌና በደቡብ ሱዳን የሰላም ሂደት በኢጋድ ስር ሆነው በማገልገላቸው፤ በሱዳን የሽግግር መንግሥት የሰላም ሂደት ላበረከቱት ከፍተኛ አስተዋፅዖም ሽልማት ተበርክቶላቸዋል። የግል ቢዝነስ ድርጅት ላይም ተሳትፎ ያላቸው አምባሳደር መሐሙድ ድሪር፤ የኢስት አፍሪካ ሆልድን ከፍተኛ አማካሪ ሆነው ሠርተዋል።

አምባሳደር መሐሙድ አሁን ደግሞ ኢትዮጵያን ከቆየችበት ሕመም ለመፈወስ " ሁሉን አቀፍ እና አካታች ምክክር ይካሄዳል" መባሉን ተከትሎ የኮሚሽነሮች ሹመት ሲካሄድ አምባሳደር መሐሙድ ድሪር የአገራዊ ምክክር ኮሚሽን አባል ኮሚሽነር ሆነው ተመርጠዋል። የዕለቱ እንግዳችንን ሀገራዊ የምክክር ኮሚሽኑ እስከ አሁን እየሠራቸው ስላሉ ሥራዎች እና በአጠቃላይ የኮሚሽኑ የሥራ እንቅስቃሴ ላይ አተኩረን አነጋግረናቸዋል። መልካም ንባብ፡-

**አዲስ ዘመን፡- አገራዊ ምክክር ኮሚሽኑ ከተመሠረተ ጀምሮ የሠራቸውን ተግባራት በአጭሩ ቢያስረዱን ?**

**አምባሳደር መሐሙድ፡-** አገራዊ ምክክር ኮሚሽኑ ከተመሠረተ ጀምሮ በኢትዮጵያ ዙሪያ ብዙ ሥራዎችን እየሠራ ቆይቷል። በሠራቸው ሥራዎች መሠረት አሁን ዋና እና ትልቁ ምዕራፍ የሚባልለት ደረጃ ላይ ደርሷል። አገራዊ ምክክር በባህሪው በአራት ምዕራፎች ይከፈላል። የመጀመሪያው ከዚህ በፊት እንደገለፅነው ቅድመ ዝግጅት የሚባል ነው። ከዛ የዝግጅት ምዕራፍ አለ። ቀጥሎ የምክክር ዓውድ ይከተላል። በመጨረሻም ከምክክሩ የሚመጡ ምረጥ ሃሳቦች ለይቶ በፖሊሲ ወይም በድንጋጌ መልክ ለመንግሥት አቅርቦ መከታተልንም ያካትታል።

አሁን ያለንበት ምዕራፍ ወደ ምክክር ዓውዱ የሚወስድ ነው። አሁን በአገራዊ ምክክር ሂደት ላይ የሚሳተፉት መለየት አለባቸው። ሒደቱ አጀንዳዎችን መለየትንም የሚያካትት ነው። በዚህ ሂደት የሚሳተፉ የተለያዩ የማኅበረሰብ ክፍሎች አሉ። ለምሳሌ ራሳቸውን የሚገልፁበት ዋና መተዳደሪያ ያላቸው አርብቶ አደሮች ሊሆኑ ይችላሉ ወይም አርሶ አደሮች ሊሆኑ ይችላሉ፤ መምህራንም ከሙያ አንፃር ይሳተፋሉ። ከፆታ አንፃር ካየን ሴቶች፣ ከዕድሜ አኳያ ወጣቶች የሚሳተፉ ይሆናሉ።

በአገራችን የተለያዩ ባሕሎች አሉ። ትልልቅ ዕሴቶች አሉን። ከትልልቆቹ እሴቶች መካከል አንዱ በዕድር የመሰባሰብ ባሕል ነው። ዕድሮች በዚህ ሂደት ውስጥ ተሳታፊዎች ናቸው። በየአካባቢው ማኅበረሰቡን በባሕል የሚመሩ የማኅበረሰብ መሪዎች የሚሳተፉበት ሁኔታ አለ። ምናልባትም አባ ገዳዎች ሊሆኑ ይችላሉ። አሁን ባለንበት ዘመንም በድሬዳዋና በሐረር ደሚና የሚባል አለ። በሶማሌ ባሕል ደግሞ ኡጋዞች፣ ገራዶች እና ሡልጣኖች የሚባሉ አሉ። እነዚህ ችግር ፈቺ የሆኑ በአካባቢያቸው አመኔታ የሚጣልባቸው ትልልቅ ሰዎች ናቸው። እነኚህ ሰዎች የሚሳተፉበት ሁኔታ ይኖራል።

ነገር ግን ደግሞ የሚያኮሩ በጎ ነገሮች እንዳሉ ሁሉ፤ የምናፍርባቸው ባሕሎችም አሉ። ለምሳሌ በሥራቸው የሚናቁ የተገለሉ የማኅበረሰብ ክፍሎች እንዳሉ ይታወቃል። እነዛን የተገለሉ ሰዎች ድምፃቸው መሰማት መቻል አለበት። ብሶታቸው ሊደመጥ ይገባል። እንደዜጋ ድምፅ ሊኖራቸው ይገባል። ከሚል መነሻ እነርሱን በሂደቱ ውስጥ ተሳታፊዎች ናቸው። የንግዱ ማኅበረሰብም ይሳተፋል። አንዳንድ አካባቢዎች ላይ በግጭቶች ወይንም በጦርነት ምክንያት ከቀያቸው የተፈናቀሉ ዜጎችም አሉ። እነርሱም ይህ ሂደት ይመለከታቸዋል።

> **በመጠራጠር እና በመለያየት ከዚህ በፊት በሞከርናቸው መንገዶች ሁሉ ችግሮቻችንን መፍታት አንችልም። በጦርነት ችግር መፍታት አንችልም። አንዱ ሌላውን በማብጠልጠል፤ በመናናቅ ችግሮቻችንን መፍታት አንችልም። በግጭት ውስጥ ሆነን ችግሮቻችንን መፍታት ይከብደናል። እነዚህ ያለያዩን ጉዳዮች አሁን ባለው ፖሊሲ እና ባሉን ሕግጋቶች ልንፈታቸው አንችልም። ችግሮችን የሚቻለው በአገራዊ ምክክር በመፍታት ብቻ ነው**

ኮሚሽኑ ይህንን ሁሉ ሥራ የሚሠራው ብቻውን አይደለም። በጣም ግዙፍ ከፍተኛ ሎጂስቲክ ማንቀሳቀስን የሚጠይቅ ሥራ ነው። ሌሎች በኮሚሽኑ በኩል አመኔታ የተጣለባቸው ወገኖች አሉ። እነዚህ አመኔታ የተጣለባቸው በልየታው እንዲሳተፉ ይደረጋል። ይህ የተሳታፊዎች የልየታ ሥራ በዋናነት የኮሚሽኑ ነው። በበላይነት የሚከታተለውም ሆነ የሚቆጣጠረው እርሱ ሆኖ የተለያዩ የማኅበረሰብ ክፍሎች ድጋፍ ይሠጣሉ።

ከተሳታፊዎቹ መካከል የኢትዮጵያ ሲቪል ማኅበራት ምክር ቤት፣ የኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት፣ የኢትዮጵያ መምህራን ማኅበር፣ የኢትዮጵያ አገር አቀፍ የዕድሮች ማኅበራት ጥምረት፣ የኢትዮጵያ የሃይማኖት ተቋማት ጉባኤ፣ የወረዳ ፍርድ ቤት ዳኞች እና አንዳንድ ጊዜ ልዩ ወረዳም ሊሆን ይችላል፤ ወይም የአስተዳደሩ ተወካዮች እነዚህ በሙሉ በሂደቱ ውስጥ የሚሳተፉ ናቸው። ምክንያቱም አስራ አንድ ኮሚሽነሮች ብቻቸውን ይሔንን ሥራ ሊወጡት እንደማይችሉ የታወቀ ነው።

በሌሎች አገሮችም ይህ ተሞክሮ እንዳለ ተገንዝበናል። ከእነዚህ ከጠቀስኳቸው የማኅበረሰብ ክፍሎች ጋር በሂደቱ በሙሉ በዕቅዳችን እና በአሠራሮቻችን ላይ ተሳትፎ እንዲያደርጉ እና ሃሳባቸውን እንዲያቀርቡ የተደረጉ ናቸው። ስለዚህ አሁን ይሄ ምዕራፍ በጣም ወሳኝ እንደመሆኑ መጠን፤ ከላይ ከጠቀስኳቸው የማኅበረሰብ ክፍሎች ማለትም ራሳቸውን የሚገልፁበት በግብርና መተዳደሪያ ላይ ያሉ አርሶ አደሮች፣ አርብቶ አደሮች፣ ወጣቶች፣ ሴቶች፣ ዕድሮች እና የማኅበረሰብ መሪዎች ወዘተርፈ ያልናቸውን የእነርሱን ክፋይ ሰዎች ይመረጣሉ።

እዚህ ላይ ማኅበረሰቡ ራሱ ተመካክሮ እና ተወያይቶ አጀንዳዎችን ለሚመለከተው መድረክ ያደርሱልኛል ብሎ አመኔታ የሚጥልባቸውን ሰዎች ይመርጣል። ኮሚሽኑም እዚህ ላይ እጁን አያስገባም። ሌሎች ተባባሪ ወገኖችም ከማስተባበር ውጪ፤ ይህንን እርስ በእርሱ የመመራረጥን የኅብረተሰብ ሥራ ጣልቃ አይገቡበትም። ይሄ አካታችነትን፣ ተዓማኒነትን እና ግልፅነትን የሚያሳይ ነው።

በዚህ ሒደት ውስጥ የሚሳተፉት ዜጎቻችን፤ በዚህ አግባብ ይንቀሳቀሳሉ። ይህን ታሳቢ በማድረግ ለሚመለከታቸው በሙሉ ሥልጠናዎችን ሰጥተናል። ለምሳሌ ለድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር እና ለሐረር ክልል ሥልጠና ሰጥተናል። ሌሎች የኮሚሽኑ አባላትም በሲዳማ ክልል፣ በደቡብ ምዕራብ ሕዝቦች ክልል፤ ይህንኑ ተመሳሳይ ሥልጠናዎች እና ግንኙነቶችን በመፍጠር ላይ እንዳሉ እናውቃለን። ይህንን ሥራ ጨርሰን፤ እነዚህ የተለያዩ የማኅበረሰብ ክፍሎች በራሳቸው የሚመርጡበት ጊዜ ላይ ደርሰናል። እኛም ተገኝተን ይህንን ሂደት ተከታትለን ልየታው የተሳካ መሆኑን ወደ ፊት የምንገልፅ ይሆናል።

የአገራችን የፖለቲካ ልሂቃን በሃሳቦች መለያየት በተለይም መሠረታዊ በሆኑ አገራዊ ጉዳዮች ላይ ልዩነቶች እንዳሉ ተደጋግሞ ይነገራል። እነዚህን ልዩነቶች በጋራ መግባባት በምክክር ለመፍታት ይሄ ሥራ በጣም አስፈላጊ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ጥሩ! በአገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች ግጭቶች ይታያሉ፤ በኦሮሚያ እና በአማራ ክልል አንዳንድ አካባቢዎች ላይ ተንቀሳቅሶ ለመሥራት አይቸግርም? ይህንን ኮሚሽኑ የሚወጣው እንዴት ነው?**

**አምባሳደር መሐሙድ፡-** እውነት ለመናገር መጀመሪያ የቅድመ ዝግጅቱ እና የዝግጅት ምዕራፍ ላይ ከትግራይ ክልል በስተቀር በሁሉም ክልሎች ተዟዙረን ከአስተዳዳሪዎች፣ ከኅብረተሰብ መሪዎች፣ ከሲቪል ማኅበራት፣ ከወጣቶች፣ ከሴቶች እንዲሁም ከተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ጋር ሂደቱን ለማስተዋወቅ እና ለመተዋወቅ የተንቀሳቀስንባቸው ሁኔታዎች አሉ። በዚያን ወቅት በትግራይ ክልል ውስጥ የነበረው ጦርነት እና ግጭት ወደ ትግራይ ክልል እንዳንሔድ አድርጎናል። ጦርነቱ ትልቅ ተግዳሮት ነበር።

ነገር ግን ይሄ አገራዊ ምክክር በሁሉም ክልሎች ሊካሔድ ስለሚገባ፤ በዚያን ወቅት በገጠመን ችግር አለመሔዳችንን ለማኅበረሰቡ በመገናኛ ብዙኃንም

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

# የዘመን እንግዳ

## ‹‹አገራዊ ምክክር በራሱ...



**አገራዊ ምክክር ለአገረ መንግሥት ግንባታ፣ መንግሥት በሕዝቡ ውስጥ ያለውን አመኔታ ለማጠናከር እና የማኅበረሰብ ውልን ለማደስ እንዲሁም የተሸረሸሩ እሴቶቻችንን ለመጠገን የምንከተለው ሒደት ነው። ስለዚህ በዚህ ሂደት ውስጥ ማንም መቅረት የለበትም። ሁሉም ወገኖች መሳተፍ አለባቸው**

ከገጽ 6 የዞረ

ገልፀናል። አሁን በአንዳንድ አካባቢዎች ያሉት ችግሮች ከእኛ ጋር ለወደፊትም ለዘላለም የሚኖሩ ናቸው የሚል እምነት የለኝም። ምክንያቱም ጦርነትን የሚያክል ነገር፤ በሰሜኑ የአገራችን ክፍል ተከስቶ መፍትሔ እና እልባት አግኝቷል። ስለዚህ መንግሥት በሚያደርገው ጥረት የመደራደር፣ ችግሮችን የመፍታት፤ ሰላምን የማስፈን ሁኔታዎች ይኖራሉ ብለን እናምናለን። ድርድር እና ምክክር አንዱ ሌላውን አይተካም። ነገር ግን ይመጋገባሉ፤ ይደጋገፋሉ። ስለዚህ በዚህ መልኩ አገራችንን ካለችበት አስቸጋሪ ምዕራፍ ለማሻገር እንችላለን ማለት ነው።

**አዲስ ዘመን፡- አገራዊ ምክክሩ አገራችን ከገባችበት የፖለቲካ ውጥንቅጥ ለመውጣት ምን ያህል አስተዋፅዖ ይኖረዋል? በተጨማሪ ለሌሎች አገሮች ምርጥ ተሞክሮ እንዲሆን በምን ዓይነት ጥንቃቄ ለመሥራት ታስቧል? የመንግሥት ተባባሪነትስ እንዴት ይገለፃል?**

**አምባሳደር መሐሙድ፡-** በመጀመሪያ ደረጃ መንግሥት በራሱ ተነሳሽነት አዋጅ አውጥቶ አገራዊ የምክክር ኮሚሽን እንዲመሠረት አድርጓል። ይህ የመንግሥት ወገንን ቁርጠኝት የሚያሳይ ነው። አንድ አገራዊ ምክክር እንዲሳካ ከሚያደርጉ ጉዳዮች መካከል አንዱ የመንግሥት ቁርጠኝነት ነው።

ሌላው የተለያዩ የማኅበረሰብ ክፍሎች ተሳትፎ ነው። ተሳትፎ ደግሞ በአገራችን ውስጥ የተለያዩ ብዝኃነቶች አሉ። የቋንቋ ብዝኃነት ፣ የባሕል፣ የሃይማኖት፣ የእምነት እና ሌሎችንም ብዝኃነቶችን ተመርኩዘን አካታች የሆነ አሳታፊ ሒደት ውስጥ እንገባለን ብለን እናምናለን። የተለያዩ የማኅበረሰብ ክፍሎች ወይም አደረጃጀቶች ከእኛ ጋር በቅርበት እንዲሠሩ የተደረገው ለዚህም ነው።

ስለዚህ ከላይ የጠቀስኳቸው የኢትዮጵያ ሲቪል ማኅበራት ምክር ቤት፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት፣ የኢትዮጵያ መምህራን ማኅበር፣ የሃይማኖት ተቋማት ጉባኤ እና የወረዳ ፍርድ ቤት ዳኞች፣ የወረዳ ወይም የልዩ ወረዳ አስተዳደር ተወካዮች ፣ የመምህራን ማኅበር እና ሌሎችም የሚሳተፉበት ዋና ምክንያት ሁሉም ወገን ድርሻውን እንዲያበረክት ለማድረግ እና አካታች አገራዊ ምክክር ለማካሔድ እንዲሁም አመኔታ እንዲመጣ ለማስቻል ነው።

ኢትዮጵያ በጣም በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ የምትገኝ መሆኗን ኅብረተሰቡ በሙሉ የሚረዳው ነው። ይህንን የአገራዊ ምክክር ጉዳይን ሕዝቡ በታላቅ ጉጉት እየጠበቀው ነው። ስለዚህ ሕዝቡ ዘንድ ሲመለስ እና የሕዝቡ ተሳትፎ በሰፊው ሲታከልበት ማለትም የተሳታፊዎች ልየታው በሰፊው ተከናውኖ የአጀንዳ አሰባሰቡ ሒደት ከተጠናቀቀ እና የአገራዊ ምክክሩ ዓውድ ውስጥ ሲገባ፤ አገራዊ ምክክር በራሱ ኢትዮጵያን ይፈውሳል። አገራዊ ምክክር በራሱ ፈዋሽ ነው።

በመጠራጠር እና በመለያየት ከዚህ በፊት በሞከርናቸው መንገዶች ሁሉ ችግሮቻችንን መፍታት አንችልም። በጦርነት ችግር መፍታት አንችልም። አንዱ ሌላውን በማብጠልጠል፤ በመናናቅ ችግሮቻችንን መፍታት አንችልም። በግጭት ውስጥ ሆነን ችግሮቻችንን መፍታት ይከብደናል። እነዚህ ያለያዩን ጉዳዮች አሁን ባለው ፖሊሲ እና ባሉን ሕግጋቶች ልንፈታቸው አንችልም። ችግሮችን የሚቻለው በአገራዊ ምክክር በመፍታት ብቻ ነው።

እነዛን ችግሮች ሰከን ባለ ሁኔታ ተማምነን፣ ተመካክረን የአንዱ ብሶት የሌላው ብሶት እንደሆነ ተረድተን ችግሮችን ለመፍታት የምናደርገው ጥረት አገራዊ የጋራ መግባባት ላይ ሊያደርሰን ይችላል። በአገራዊ ምክክሩ ውስጥ አገራዊ መግባባትን ስንፈጥር፤ ከዚህ በፊት የተሸረሸሩ እሴቶቻችን የምንጠግንበት፤ ጠንካራ አገረ መንግሥት የምንገነባበት ይሆናል። እንዲሁም በኅብረተሰቡ እና በመንግሥት መካከል ያለውን መተማመን የምናጠናክርበት ሲሆን፤ አገራችንን አሁን ካለችበት ሁኔታ ወደ ተሻለ ደረጃ የምናሸጋግርበት ነው።

**አዲስ ዘመን፡- አገራዊ ምክክሩ ከተሳካ ትልቅ ዕድል ካልተሳካ ደግሞ ትልቅ አገራዊ ስጋት ሲሆን እንደሚችል እየተገለፀ ነው። ይህንን ለማደናቀፍ የሚጥሩ ጽንፍ የያዙ ሰዎች ምክክሩ ላይ የሚያሳድሩት ስጋት እንዴት ይገለጻል?**

**አምባሳደር መሐሙድ፡-** ከተሳካ ሳይሆን ይሳካል እንበል፤ ምክንያቱም ይሳካል ብዬ አምናለሁ። ከዚህ ውጪ ሌላ አማራጭ መንገድ የለንም። ሌሎች አገሮች እንዳሳኩት ሁሉ ኢትዮጵያም ማሳካት ትችላለች ብዬ አምናለሁ። ምክንያቱም እንደሕዝብ እና እንደአንድ ማኅበረሰብ የሚያገናኙን እሴቶቻችን ከሚያለያዩን የበለጡ ናቸው። ይህንን መዘንጋት የለብንም። ምክክሩ የፖለቲካ ልዩነቶችን የምንፈታበት፤ መንገድ የምንቀይርበት ነው። ምክንያቱም በጦርነት እና በግጭት ሳይሆን ችግሮቻችንን የምንፈታው በመመካከር ነው።

ተጨማሪው ለሌሎች አገሮች ምሳሌ እንሆናለን የሚለውን ስንደርስበት የምናወራው ነው። አሁን ግን በትክክል ተዓማኒ፣ አሳታፊ እና አካታች የሆነ አገራዊ ምክክር ለማካሔድ በኮሚሽኑም ሆነ በኮሚሽነሮች በሙሉ ቁርጠኝነት መኖሩ መታወቅ አለበት።

ይህንን ምክክር ሕዝቡ ካመነውና ከተቀበለው ጽንፍ የያዙ ሰዎች የሚባሉት የሚያሳድሩት ተጽዕኖ እዚህ ግባ የሚባል አይደለም።

**አዲስ ዘመን፡- አሁን የተወሰኑ ቦታዎች ላይ ስትንቀሳቀሱ የሚያጋጥሙ ነገሮች አይጠፉም። ሰላማዊ ተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች ብቻ ሳይሆኑ በተቃውሞ በተለያዩ የትግል ስልት ውስጥ ያሉ አሉ። እነዚህንም በሙሉ ለማካተት የተጀመረ ነገር አለ? በዚሁ ላይ የሌሎች አገሮች ተሞክሮ ምን ይመስላል?**

**አምባሳደር መሐሙድ፡-** አገራዊ ምክክር ከተካሔደባቸው አገሮች አንፃር ሲታይ አንዳንድ የሚያመሳስሉን ጉዳዮች አሉ። ለምሳሌ የታጠቁ ኃይሎች ያሉበት አገር እንደ ኮሎምቢያ ዓይነቶቹ ችግራቸው የተፈታው በድርድር ነው። በድርድር ከተፈታ በኋላ ፋርክ የሚባለው ግንባር ተቀናቃኝ ሆኖ፤ መሣሪያውን ያነገበው ኃይል፤ መሣሪያውን አስቀምጦ ወደ ሰላማዊ ሒደት ገብቶ በምክክሩ ላይ ተሳትፏል። እዚህ ላይ ልብ መባል ያለበት ጉዳይ ምክክር እና ድርድር ይለያያል። ይህንን ያልኩበት ምክንያት ምክክር በራሱ ሰላማዊ ዓውድ ይፈልጋል። የታጠቀ ኃይል ማለትም ጠመንጃ ያነገበ እና በሌላ በኩል ያልታጠቀ ሰው ቁጭ ብሎ መመካከር የሚታሰብ አይደለም። በሌሎች አገሮችም ይህ ክስተት በዚህ መልኩ አልተካሔደም፤ የሚከወነው በድርድር የሚፈቱ ነገሮች በድርድር ይፈታሉ።

አገራዊ ምክክር ለአገረ መንግሥት ግንባታ፣ መንግሥት በሕዝቡ ውስጥ ያለውን አመኔታ ለማጠናከር እና የማኅበረሰብ ውልን ለማደስ እንዲሁም የተሸረሸሩ እሴቶቻችንን ለመጠገን የምንከተለው ሒደት ነው። ስለዚህ በዚህ ሂደት ውስጥ ማንም መቅረት የለበትም። ሁሉም ወገኖች መሳተፍ አለባቸው።

**አዲስ ዘመን፡- በእርግጥ ኢትዮጵያ አለመግባባቶችን የምትፈታበት ድንቅ ባሕሎች ያሏት አገር ናት። ሆኖም የልምድ ልውውጥ ለማግኘት ከኢትዮጵያ ወዳጆች ጋር በጋራ የተሠራ ነገር ካለ ቢገልፁልኝ? የመገናኛ ብዙኃንን ሚናስ እንዴት ይመለከቱታል ?**

**አምባሳደር መሐሙድ፡-** ሥራችንን ትተን የሌሎች አገሮችን ልምድ ለማየት ከአገር ወጥተን ስንዞር አልከረምንም። ነገር ግን የተለያዩ አገሮችን ልምዶች አይተናል፤ አንብበናል፣ ተረድረናል እንዲሁም ተገንዝበናል። ካየናቸው ውስጥ የሚመሳሰሉን አሉ። በሌላ በኩል ከእኛ የተለዩ አሉ። ጭብጣቸው እና የራሳቸው የባሕሪ ችግር ያለባቸውም ነበሩ።

ለምሳሌ በደቡብ አፍሪካ የተካሔደው አገራዊ ምክክር በራሱ በአፓርታይድ ጊዜ የነበረውን ጠባሳ እና ችግር ለመፍታት ያለመ ነበር። በኬኒያ የተካሔደው አገራዊ ምክክር ደግሞ በድሕረ ምርጫ የተፈጠረውን ቀውስ ለመፍታት እና መንግሥታዊ ሥርዓቱን ለማፅናት የተካሔደ ነበር። በሩዋንዳም እንደሚታወቀው ሁቱ እና ቱትሲ የሚባሉ ሁለት ማኅበረሰቦች ላይ በተደረገው ዘር የማጥፋት ሒደት ውስጥ የነበረውን ጉዳይ ለመፍታት ነው። ስለዚህ ከኛ የተለዩ ሲሆኑ፤ ከእኛ የሚያመሳስላቸው ጉዳይ ያላቸው አገሮችም አሉ።

በሌላ በኩል በቱኒዚያ፣ በማሊ እና በሴኔጋል የተካሔዱ ሒደቶች አሉ። ነገር ግን ከሕዝብ ብዛት አንፃር የእኛ የሕዝብ ብዛት እንደሚታወቀው ከ120 ሚሊዮን በላይ ሕዝብ ነው። በዚህ ሂደት ውስጥ ወኪሎችን ወይም ሕዝቡ የሚያምንባቸውን በውክልና የሚያሳትፍ መሆኑ ግድ ነው። ስለሆነም በራሱ ለእኛ ከሁሉም አስቀድሞ እንደአገር ጠቀሜታው በጣም የጎላ ነው። የልምድ ልውውጥ የሚለውን ያየነው በዚህ ነው። የተለያዩ አገሮች የተሳካላቸው ምን ስለሠሩ ነው? የከሸፈባቸውስ ምን ውስጥ ስለገቡ ነው? የሚለውን አጥንተናል።

መገናኛ ብዙኃንን በተመለከተ ሚዲያዎች በአንድ በኩል ፈዋሽ መሆናቸው የተረጋገጠ ነው። በሌላ በኩል ግን ችግር ሊፈጥሩ የሚችልበት ሁኔታም መኖሩ አይሸሸግም። ስለዚህ በሰከነ እና ከሁሉም በላይ አገርን በማሰብ የአገርን ጉዳይ ላይ የሚያገለግል የሚዲያ መንገድ ያስፈልገናል። ይህ አገራዊ ምክክር ምን እንደሆነ ለኅብረተሰቡ በማስተዋወቅ የምንሠራቸውን ሥራዎች በየጊዜው ለኅብረተሰቡ የማስገንዘብ፤ መልዕክቱን በትክክል ሳይዛነፍ፣ ሳይሸረፍ፣ ሳይበረዝ የማድረስ ኃላፊነትን መወጣት አለብን። በዚህ መልኩ መገናኛ ብዙኃኑ ቢሳተፉ ለአገራችን ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖራቸዋል። ነገር ግን የእኛ መገናኛ ብዙኃን ሁሉም በዚህ መልኩ ይዘግባሉ? መገናኛ ብዙኃኑ የሚገለፁት በዚህ መልኩ ነው? የሚለው ሌላ ጉዳይ ነው። ስለዚህ ሊታሰብበት ይገባል።

**አዲስ ዘመን፡- ስለነበረን ቆይታ በዝግጅት ክፍሉ ስም እጅግ አመሰግናለሁ።**

**አምባሳደር መሐሙድ፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

# ማህደረ ጤና

# ‹‹ፕሪኢክላምፕሲያ›› የእናቶች ሞት ጦስ

**አስናቀ ፀጋዬ**

እ.ኤ.አ በ2020 በዓለም ጤና ድርጅት በተሰራ ጥናት በዓለም አቀፍ ደረጃ በየቀኑ 800 የሚሆኑ እናቶች ከእርግዝናና ወሊድ ጋር ተያይዞ በሚከሰቱና መከላከል በሚቻሉ ምክንያቶች ይህችን ዓለም ይሰናበታሉ። በዚሁ ጥናት መነሻ ደግሞ በየደቂቃው አንድ እናት በዚሁ ምክንያት ህይወቷ ይቀጠፋል። 95 ከመቶ የሚሆነው የእናቶች ሞት የሚከሰተው በዝቅተኛና መካከለኛ ገቢ ባላቸው አገራት መሆኑንም ይኸው ጥናት ያሳያል። ከነዚህ መካከል ኢትዮጵያን ጨምሮ ከሰሃራ በታችና በደቡብ እስያ የሚገኙ አገራት 87 ከመቶ ወይም 253 ሺ ያህሉን የእናቶች ሞት ይሸፍናሉ።

እ.ኤ.አ በ2025 የእናቶችን ሞት ወደ 279 ለመቀነስ ታቅዶ እ.ኤ.አ በ2020 ወደ 267/ከ100 ሺ መቀነስ መቻሉን መረጃዎች ጠቁመዋል። በኢትዮጵያም የእናቶች ሞት ዋነኛ መንስኤዎች ከወሊድ በኋላ የሚከሰት ደም መፍሰስ፣ በእርግዝና ወቅት የሚከሰት ደም ግፊትና ኢንፌክሽን መሆናቸው በጥናት ተረጋግጧል።

በርግጥ ከወሊድ በኋላ የሚከሰት ደም መፍሰስ በኢትዮጵያ ለሚከሰተው የእናቶች ሞት ቁጥር አንድ ድርሻ ቢኖረውም ከቅርብ ግዜ ወዲህ ግን በእርግዝና ወቅት የሚከሰት ደም ግፊት /preeclampsia/ ትልቅ አስተዋፅኦ እያደረገ ነው። በከተማም ሆነ በገጠር በእናቶች ዘንድ ስለህሙ ያለው ግንዛቤ ዝቅተኛ መሆን ደግሞ ሳይታወቅ ብዙ እናቶችን ለሞት እየዳረገ ይገኛል።

ለመሆኑ በእርግዝና ወቅት የሚከሰት ደም ግፊት /preeclampsia/ ምንድን ነው? ህመሙስ እንዴት ይከሰታል? በምን መልኩስ ነው ህመሙን መከላከል የሚቻለው? ለነዚህና ሌሎች ተያያዥነት ያላቸው ጥያቄዎች በቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ህክምና ኮሌጅ የማህፀንና ፅንስ ስፔሽያሊስት ሃኪም ዶክተር ፍላጎት ታደሰ መልስ አለኝ ይሉናል።

ዶክተር ፍላጎት እንደሚናገሩት በእርግዝና ወቅት የሚከሰቱ የተለያዩ የደም ግፊቶች አሉ። ከነዚህ ውስጥ አንዱ /preeclampsia/ ሲሆን ከአንድ መቶ እናቶች ውስጥ ከሁለት እስከ ስምንት በሚሆኑት ላይ እንደሚከሰት ዓለም አቀፍ ጥናቶች ያሳያሉ። ከፍተኛ የሆነውን የእናቶችንና የጨቅላ ህፃናትን ሞት እንደሚያስከትለም እነዚሁ ጥናቶች ይጠቁማሉ።

ለእናቶች ሞት አንደኛው መንስኤ መሆኑንም ጥናቶቹ ያመላክታሉ። በወሊድ ወቅት ደም መፍሰስም ከዚሁ ከእርግዝና ደም ግፊት ጋር አብሮ የተያያዘ ስለመሆኑ በጥናቶቹ ተረጋግጧል። ሆኖም በእርግዝና ወቅት የሚከሰት የደም ግፊት /pre-eclampsia/ በሚመለከት በኢትዮጵያ በቂ መረጃ የለም። ሆኖም በወሊድ ወቅት ከሚከሰተው የደም መፍሰስ ቀጥሎ ለእናቶች ሞት ሁለተኛው መንስኤ መሆኑ ተነግሯል።

እንደ ጥናቶቹ ከሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ በእርግዝና ወቅት የሚከሰት የደም ግፊት /pre-eclampsia/ ምክንያት በየዓመቱ ከ76 ሺ እናቶች በላይ ይሞታሉ። ከ500 ሺ ጨቅላ ህፃናት በላይ ደግሞ ከዚሁ የጤና ችግር ጋር በተያያዘ ህይወታቸው ይቀጠፋል። በጥናቱ ይህ ቁጥር ተመላከተ እንጂ በዚህ የእርግዝና ደም ግፊት ምክንያት በርካታ እናቶች ሊሞቱ እንደሚችሉ ይገመታል። ከዚህ አንፃር ችግሩ እጅግ አሳሳቢ መሆኑን ያመላክታል።

ዶክተር ፍላጎት እንደሚያብራሩት በእርግዝና ወቅት የሚከሰት የደም ግፊት /preeclampsia/ ምክንያት ጨቅላ ህፃናት በመጀመሪያዎቹ 28 ቀናት ሊሞቱ አልያም ደግሞ ግዚያቸው ሳይደርስ ሊወለዱ ይችላሉ። ችግሩ በመጀመሪያዎቹ አንድና ሁለት የእርግዝና ዓመታት ተከስቶ የጨቅላ ህፃናትን ሞት ሊያስከትል ይችላል። ከዚህ አንፃር የእርግዝና ደም ግፊት ከእናቶች ሞት በዘለለ ለጨቅላ ህፃናት ሞትም ትልቅ አስተዋፅኦ አለው።

ከሌሎች በእርግዝና ወቅት ከሚከሰቱ የደም ግፊቶች /preeclampsia/ የሚለየው በእናቶችና



ዶክተር ፍሳጎት ታደሰ፣

በህፃናት ላይ በሚያመጣው ችግር ነው። ይህ ሲባል ግን ከእርግዝና ውጪ የሚከሰቱ የደም ግፊቶች በእናቶችና በህፃናት ላይ የሚያመጡት ችግር የለም ማለት አይደለም። ሆኖም እርግዝናን ብቻ ጠብቆ የሚከሰተው የደም ግፊት /preeclampsia/ በእናቶችና በጨቅላ ህፃናት ላይ የሚያመጡት የጤና ችግር የተወሳሰበ ነው።

የደም ግፊቱ ከጭንቅላቷ ጀምሮ የእናቲቱን የተለያዩ የሰውነት ክፍሎችን ይጎዳል። የጭንቅላት ውስጥ ደም መፍሰስ፣ ራስን መሳት፣ የልብ ድካም፣ የጉበትን ስራ ማስተጓጎል፣ ኩላሊት ስራውን እንዲያቆም፣ የደም መፍሰስና ሌሎች ችግሮችንም ያስከትላል።

ከእርግዝና ውጪ ያለ የደም ግፊት በማንኛውም ግዜ ሊኖር ቢችልም በእርግዝና ወቅት የሚከሰተው የደም ግፊት /preeclampsia/ ግን በእርግዝናው ወቅት በአብዛኛው ከሀያ ሳምንት ጀምሮ ባለው ግዜ ውስጥ ነው። ሆኖም ደም ግፊቱ አንዳንዴ በወሊድና በምጥ ወቅት ወይም ከወሊድ በኋላ ሊታይ ይችላል።

ዶክተር ፍላጎት እንደሚሉት በርካታ ጥናቶች በዓለም አቀፍ ደረጃም ሆነ በአገር ውስጥ ቢሰሩም የእርግዝና ወቅት ደም ግፊት /preeclampsia/ ትክክለኛ መንስኤ በሚገባ አልታወቀም። በዚህም ምክንያት ህክምናውንም ሆነ ክትትሉን ከባድ አድርጎታል። ሆኖም የችግሩን መንስኤ ሊጠቁሙና ለህክምና ሊጠቅሙ የሚችሉ አንዳንድ መላምቶች አሉ። አጋላጭ ምክንያቶች ግን ሊኖሩ ይችላሉ። ሆኖም ችግሩ አጋላጭ ምክንያት ባላቸው ሴቶች ብቻ ሳይሆን በማናቸውም ሴቶች ላይ ሊከሰት እንደሚችል ማጤን ያስፈልጋል። አጋላጭ ምክንያት ያላቸው ሴቶች ግን ለችግሩ ይበልጥ ተጋላጭ እንደሚሆኑ አጠያያቂ አይደለም።

ከዚህ አንፃር እርግዝና የመጀመሪያቸው የሆነ፣ ከዚህ በፊት በእርግዝና ግዜ የደም ግፊት የታየባቸው ወይም በቤተሰብ ውስጥ ተመሳሳይ ታሪክ ያላቸው፣ ከዚህ በፊት የደም ግፊት፣ የኩላሊት ወይም ሁለቱም በሽታዎች የነበረባቸው፣ እድሜያቸው ከአርባ ዓመት በላይ የሆኑ፣ እርግዝናው መንታ ወይም ከዛ በላይ የሆነባቸው፣ እንደ ስኳር አይነት ተጓዳኝ በሽታ ያለባቸው፣ ከመጠን በላይ ውፍረት በእርግዝና ወቅት ለሚከሰት የደም ግፊት ይበልጥ ተጋላጭ ይሆናሉ።

አጋላጭ ሁኔታዎቹ እንዳሉ በእርግዝና ወቅት የሚከሰት የደም ግፊት በእናትም በፅንስም ላይ ችግር ሊያስከትል ይችላል። ለምሳሌ በፅንሱ ላይ የልጁ ክብደት ከእርግዝና ግዜ ጋር ሲታይ የቀነሰ ይሆናል። የውሃ ሽንት ይቀንሳል። በእትብት በኩል ለልጁ የሚደርሰው ደም ይቀንሳል። እንዲሁም ፅንሱ በማህፀን ውስጥ እንዳለ ሊሞት ይችላል።

በሌላ በኩል ደግሞ በእናቲቱ ላይ በአብዛኛው ምንም አይነት ምልክት ላያሳይ ይችላል። በአብዛኛው ምልክቶቹ የሚታዩትም ችግሩ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ሲደርስ ነው። ነገር ግን በምርመራ ግዜ የደም ግፊት መጨመር ሽንት ውስጥ ያለው ፕሮቲን ከፍ ማለት ሊታይ ይችላል። ከዚህ አኳያ ለእርግዝና ወቅት ደም ግፊት ምንም አጋላጭ ሁኔታ የሌላት ነብሰ ጡር ሴት ቢያንስ ስምንት ግዜ ያህል ወደ ጤና ተቋም ሄዳ ክትትል እንድታደርግ ይመከራል።

ዶክተር ፍላጎት እንደሚገልፁት ከባድ ራስ ምታት፣ የእይታ ለውጥ /የእይታ ብዥ ማለት፣ የእይታ መጋረድ/፣ ትንፋሽ ማጠር፣ በሆድ የላይኛው ክፍል ላይ ከባድ የህመም ስሜት፣ ከፍተኛ የደም ግፊት፣ የፊትና የእጆች ማበጥ በእርግዝና ወቅት የሚከሰት የደም ግፊት /preeclampsia/ አደገኛ ምልክቶች ናቸው። ሆኖም ከዚህ ውጪ ከእርግዝና ጋር ተያያዥነት ያላቸው የህመሙ ምልከቶች ሊኖሩ ይችላሉ። ለምሳሌ አንዲት ሴት የጭንቅላት ውስጥ ደም መፍሰስ ቢኖራት እጅና እግር እምቢ ማለት፣ ለመናገር መቸገር፣ ራስን መሳት፣ መንቀጥቀጥ ያለባቸው የዚሁ ህመም ምልክት ሊሆን ይችላል።

የሽንት መጠናቸው በጣም ዝቅተኛ መሆንና ይህንኑ ተከትሎ አጣዳፊ የሆነ የኩላሊት መድከም መከሰትም የህመሙ ምልክት ነው። በተመሳሳይ ጉበት ላይ ችግር ካለ አይናቸው ቢጫ መሆን፣ ነስር፣ የተለያየ የሰውነት ቦታ ላይ መድማት፣ በማህፀን ደም ማየትና ሌሎችም ከእርግዝና ጋር ተያይዞ የሚከሰት ደም ግፊት ምልክት ሊሆን ይችላል።

ስለዚህ እንዲህ አይነቱን ምልክት የተመለከተች ሴት ደሟን መለካት ብቻ ሳይሆን በአፋጣኝ ወደ ጤና ተቋም በመሄድ ተጨማሪ ምርመራና ህክምና ማድረግ ይጠበቅባታል። ህብረተሰቡ ጋር መድረስ ያለባቸው ዋነኛ መልእክቶችም እነዚህ አደገኛ የሆኑ የህመሙ ምልክቶች ናቸው።

አብዛኞቹ ብዙ ግዜ በእርግዝና ወቅት የሚያጋጥም ምልክቶች እንደመሆናቸው እናቶች በቸልታ የሚያልፏቸው ስለሆነ በምልክቶቹ ላይ ግንዛቤ ወስደው በአፋጣኝ ወደጤና ተቋም መምጣት ይኖርባቸዋል።

በሌላ በኩል ደግሞ ከእርግዝና ጋር ተያይዞ የሚመጣ የደም ግፊት ዋነኛ መፍትሄ መውለድ ነው። ምክንያቱም እናቲቱ ስትወልድ የሚጠፋ የደም ግፊት በመሆኑ ነው። ሆኖም ግን የእርግዝና ግዜውንና በማየት የሚደረጉ ህክምናዎች ይኖራሉ። ለምሳሌ ለመውለድ ወሯ ያለደረሰች ሴት ከሆነች የእናቲቱንና የፅንሱን ሁኔታ በሚሰሩ የላብራቶሪ ምርመራዎች፣ በአልትራሳውንድ፣ በደም ግፊት ልኬት ነገሮችን መቆጣጠር ከተቻለ የእርግዝና ወቅት የደም ግፊቱን መከላከል ይቻላል።

ሆኖም አሳሳቢ የሆኑ የህመሙ ምልክቶች ማለትም ማንቀጥቀጥም ራስን መሳት፣ የኩላሊት መድከምና ደም መፍሰስ ከታዩ ለእናቲቱ ህይወት አደጋ በመሆኑ ወዲያውኑ ማዋለድ ይኖራል። ግዜው ያልደረሰና የማያድግ ፅንስ ከሆነ ደግሞ ፅንሱ እንዲቋረጥ ይደረጋል። በዚሁ የህክምና ሂደት አንዳንዴ ያለግዜያቸው የተወለዱ ልጆች ካሉም ሙቀት ክፍል እንዲገቡ ይሆናል።

በእርግዝና ወቅት የሚከሰት የደም ግፊት ሁነኛ መንስኤው ምን እንደሆነ ስለማይታወቅ ህመሙን ሙሉ በሙሉ ለመከላከል የሚያስችሉ መንገዶች የሉም። ሆኖም ከዚህ ጋር የተያያዙ ችግሮችን ለመከላከል የቅድመ ወሊድ ክትትል በመጀመሪያ ሶስት ወር መጀመር ያስፈልጋል። በዚሁ አጋጣሚም ከጤና ባለሞያ ጋር የመመካከር እድል ይፈጠራል። የቅድመ ወሊድ ክትትሉ በተለይ ደግሞ ለዚህ ህመም ተጋላጭ ለሆኑ ሴቶች እጅግ ጠቃሚ ነው።

ለምሳሌ ከልክ ያለፈ ውፍረት የህመሙ አንደኛው አጋላጭ ምክንያት እንደመሆኑ ክብደት ቀንሳ እርግዝናዋን እንድታስብ ማድረግ ይቻላል። በተመሳሳይ አንዲት ሴት ስኳር ቢኖርባት አስቀድሞ ስኳሩን በመቆጣጠር ለህመሙ እንዳትጋለጥ መርዳት ያስችላል። ኩላሊት ላይም በተመሳሳይ አስቀድሞ መቆጣጠር ያስፈልጋል። ከዚህ አንፃር የቅድመ ወሊድ ክትትል እጅግ ጠቃሚ ይሆናል።

በተመሳሳይ ጤነኛና ምንም አይነት የእርግዝና ወቅት የደም ግፊት አጋላጭ ሁኔታ የለኝም የምትል ሴት ቢያንስ ስምንት ግዜ የእርግዝና ክትትል ማድረግ አለባት። ምልከቶቹን አይተው በግንዛቤ እጥረት የሚዘናጉና ይህንኑ ተከትሎ ለህልፈተ ህይወት የሚዳረጉ በርካታ ሴቶች በመኖራቸው በአፋጣኝ ወደ ጤና ተቋም መጥተው በእርግዝና አስራ ሁለተኛ ሳምንት ላይ የሚሰጣቸውን መድሃኒት በመውሰድ ህመሙ የመከሰት እድሉን በአብዛኛው መቀነስ ይቻላል።

ስለዚህ የእናቶች እነዚህን ምልክቶች ሲያዩ በአፋጣኝ ወደ ጤና ተቋማት መምጣት እንዲህ አይነት የህክምና መፍትሄ ርምጃዎችን ለመውሰድ ይረዳል። ለህመሙ ተጋላጭ ምክንያት ያላቸው እናቶች በቶሎ ወደ እርግዝና ክትትል መምጣታቸው የሚጠቅመውም በነዚሁ የህክምና መፍትሄዎች ህመሙን ለመከላከል ነው።

እንዲያም ሆኖ የወሊድ ወቅት ደም ግፊት ኖሯት የወለደች ሴት በቀጣዮቹ አስር ዓመታት ውስጥ ሌሎች የጤና ችግሮችን ይዞባት ስለሚመጣ በዓመት አንዴ አጠቃላይ የሰውነት ጤና ምርመራ እንድታደርግ ትመከራለች።

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ

የሥነ ጽሑፍና የኮሙዩኒኬሽን ባለሙያ ናቸው። የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበርን ለዘጠኝ ዓመታት ያህል በፕሬዚዳንትነት መርተዋል። ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ ዘመንና የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ፤ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ታትመው በሚሠራጩ የተለያዩ የኅትመት ውጤቶች ላይ (ዳግላስ ጴጥሮስ) በሚል የብዕር ስሙ በርካታ ጽሑፎችን አስነብበውናል። በግላቸው 12፣ ከሌሎች ጸሐፍት ጋር በርካታ መጻሕፍትን ለአንባብያን አቅርበዋል።



(በጌታቸው በለጠ /ዳግላስ ጴጥሮስ)
gechoseni@gmail.com

# “እንባ ሲሻኝ፤ ዐይኔን ጢስ ወጋኝ”

**መንደርደሪያችን፤**

ለዚህ ጽሑፍ በዋና ርዕስነት የተመረጠው ነባር ብሂል የሚብራራው፡- “እንኳንስ እናቴ ሞታ እንዲያውም አልቅስ አልቅስ ይለኛል” በሚል ጥንታዊ አቻ አባባል ነው። ከዕለት ወደ ዕለት ግራ እያጋቡንና እየተወሳሰቡ የሚያስተክዙንና የሚያስቆዝሙን መራር ሀገራዊ የውስጥ አበሳዎቻችን ያነሱን ይመስል ሌሎች ውጫዊ ጫናዎች ሲጨመሩብን እንደምን ስሜታችንን፣ አካላችንንና መንፈሳችንን እያኅበጡ እንደሚያስነክሱን ደግመን ደጋግመን መወትወታችን አይዘነጋም።

መልካቸውንና ባሕርያቸውን እየለዋወጡ ስሜታችንን፣ ኑሯችንንና ውሏችንን ቤትኛ በማድረግ ሥር የሰደዱትን “ብሔራዊ” ችግሮቻችንንና መከራዎቻችንን ስናስብ ትዝ የሚለን፤ “መከራው ያላለቀለት በሬ፤ ከሞተም በኋላ ቢሆን ቆዳው ለነጋሪት ይጠፈራል” የሚለው የአንጋፎች አባባል ነው።

የፈተናዎቻችን ዓይነቶች በአንድ አካባቢና ሁኔታ ብቻ የተወሰኑ ሳይሆኑ፤ “ጉድ! ጉድ! ምን ያንተ ብቻ ጉድ! እየው የእኔንም ጉድ” የምንባባልባቸው የጋራ ሕመሞቻችንና የግል ተሞክሮዎቻችን እንደ ሻህላ እያመነዠኩን ዕለት በዕለት እያመነመኑን እንዳሉ የሚካድ አይደለም። ደግመን ደጋግመን በዚህ ነፃ ዓምድ ላይ የሚጠቃቀሱትን ሀገራዊ ቁስሎቻችንን ተመልከቱልን፣ አንብቡልን፣ ስሙልን ማለታችን “ከዝምታ፡- መፍትሔ እናፋልግ በውትወታ” ለሚለው የአበው ምክር ዋጋ የሰጠን መስሎን ነው።

የዛሬ አኗኗራችንና ቅጥ ያጣው ውሎ አምሽቷችን ቀድሞ የገባው ነፍሰ ሔሩ ባለቅኔያችን ጸጋዬ ገብረ መድኅን ልክ የዛሬ ሃምሳ አምስት ዓመት “እሳት ወይ አበባ” በሚል ርዕስ በጻፈው ግጥም ውስጥ (የግጥም መድበሉ ርዕስም ይሄው ነው) የተጠቀመባቸው ጥቂት ስንኞች ጉምጉምታችንን ጮክ አድርገው የሚያስተጋቡ ስለመሰለን እነሆ ነቅሰን ለማውጣት ግድ ብሎናል።

የግጥሙን ማዕከላዊ ጭብጥ በተመለከተ በዚህ ጽሑፍ ለመነካካት ብንሞክር በዝርዝር ሊታዩ የሚገቡት ጉዳዮች እንዳይጨነግፉብን ስለምንሰጋ ወደፊት ዘርዘር ባለ ሂሳዊ ግምገማ ተመልሰንበት “በንስር ዐይን” ብንቃኘው የተሻለ ስለሚሆን በችኮላ ያለመነካካቱ መልካም መስሎ ታይቶናል።

**“እንጂ…እኛማ ተረግመን፣**
**መቸ መነጋገሪያ አለን?**
**የእርግማን ቢሆን ነው አዎን፤ እንጂ ከየት መጣ አመሉ፣**
**ሳንዲት አፍታ ሳንጠቀም፣ በደስታ ጎሕ በፀበሉ፣**
**በብርሃኑ በፀዳሉ።**
**ለአሉ ባልታ ለስም ብቻ፣ ለይስሙላ መደለሉ፣**
**የተደሰትን ማስመሰሉ፤ ለማስመሰል መታለሉ፤**
**በፍቅራችን መዋሸቱ፤ በነፍሳችን መዶለቱ፣**
**በፍቅራችን ግፍ መዋሉ፤ እርግማን እንጂ ትርጉሙ፣**
**ሌላ ምን ሲባል ነው ስሙ?”**

እርግጥ ነው ለአብዛኞቹ የሀገራችን “ብሔራዊ” እንቆቅልሾች “ምን አውቅልህ/ሽ” ባይ “የልብ አውቃ” መላሽ ስላጣን በነጋ በጠባ “ሀገር ስጡን” እየተባባልን መጠያየቁን የባሕል ያህል ተቀብለን “በአሜንታ” ካጸደቅን ሰንብቷል። እስከ መቼ? እንጃ!

**የተቃርኖ ወግ፣**

የሀገሪቱ ብዙኃን መገናኛ ሰሞኑን ጎላ አድርገው ከዘገቧቸው ዜናዎችና በስፋት የተሠሩት ዘገባዎች ይፋ ያደረጉልን አንዱ ጉዳይ “የአፈር ማዳበሪያ በወቅቱ አልቀረበልንም” የሚለውን የአርሶ አደሮቻችንን ብሶት ነው። ይህ የአርሶ አደሮቻችን ጥያቄ ቀለል ተደርጎ እንደቀረበው ሳይሆን ጥያቄያቸውን ያቀረቡበት የተስፋ መቁረጥ ስሜትና ድምጻታቸው ከሺህ ቃላት የበለጠ ገላጭ ነበር።

በተለይም በአንድ ክልል የሚኖሩ አርሶ አደር አባት የማዳበሪያ ችግራቸውን የገለጹበት የብሶት ንግግር ውስጥን ሰርስሮ መግባት ብቻ ሳይሆን ስሜታዊ የሚያደርግ ጭምር ነበር። “እስቲ መልካችንን ተመልከቱት። የሰው መልክ ይመስላል? ምናለ በአግባቡ አርሰን ይህ መልካችን እንኳን እንዲወዛ መንግሥት ቢደግፈንና ቢረዳን።

ለእኛ ለአርሶ አደሮች የተመደበላችሁ ኮታ አልመጣም እየተባለ ገበያዎቻችን መካከል ግን ማዳበሪያ በሲኒ ሲቸረቸር እያየን ነው። ለሽያጭ የቀረበው ማዳበሪያ ከየት መጣ…” የሰነዘሩት ጥልቅ ሃሳብ ስሜትን የሚያነዝር መሆኑን ብቻ በማስታወስ ማለፉ ይሻል ይመስለናል።

የሀገሪቱ የጀርባ አጥንት የሚባለውና ከ80% በላይ የሚሆኑ ዜጎች “ኋላ ቀር ሞፈር እየጎተቱ” ነፍሳችን እንዳይወጣ እየመገቡንና የኢኮኖሚው ዋነኛ ምንጭ ነው የሚባለው የግብርና ዘርፍ ለምን ጉስቁልና እንደበዛበት ማሰቡ ልብን ያታክታል። እንዴት ለሺህ ዓመታት “በሬ ሆይ! በሬ ሆይ!” እየተባለ የአስተራረስ ባሕላችን እንደተከበረ እንዲኖር ፈቀድንለት?

ከማዳበሪያው እጥረት ጎን ለጎን በአስርና በአስራ አምስት ዓመታት እያዘነጋ ዞሮ የሚመጣው ድርቅ፣ የአንበጣ ወረርሽኝና ረሃብ “የዚሁ ገበሬ የመርገምት ዕጣ ፈንታ” እንደሆነ ዘመናት መቆጠሩስ እንደ ሀገር አይቆጠቁጠንም። እኛ በእኛው ቋንቋ የገለጽነው “ብሔራዊ እፍረታችን” በባዕዳኑ ሪፖርት ሲደጋገም የኖረው በሚከተለው ዓይነት አገላለጽ ነው።

“Most of the people in Ethiopia lack coping mechanisms designed to help them face famine induced by drought. They have inadequate knowledge regarding contingency planning… Based on this basic fact 68.7 percent of the population of Ethiopia (80,000,000 people in 2020) multidimensional poor while an additional 18.4 percent is classified as vulnerable to multidimensional poverty.” “ከሰደበኝ መልሶ የነገረኝ ገደለኝ” እንዲሉ አበው፤ በርህራሄ እጃቸውን የሚዘረጉልን ሀገራትና ተቋማት የሚሉንን ሁሉ ደግመን ብናስታውስ ራሳችንን ሙልጭ አድርገን ከመስደብ ስለማይተናነስ፤ እንዲሁ “በሆድ ይፍጀው” ፈሊጥ ማለፉ ይበጃል።

ከሀገራችን የግብርና ዘርፍ ጋር ተያይዘው የሚጠቀሱት የውስጥና የውጭ “ብሔራዊ ፈተናዎቻችን” መልካቸውም ይሁን ዓይነታቸው የተዥጎረጎረ ብቻ ሳይሆን የረቀቀም ጭምር ነው።

ለምሳሌ፡- “እንደ ረሃብ ቀን ሰብል እየተቆነጠረ ከካዝና በሚወጣ ገንዘብ ማዳበሪያ የሚገዛበት የውጭ ምንዛሪ” በተፈላጊው ጉዳይ ላይ ውሎ የግብርና ግብዓቶች ሀገር ውስጥ ገብተው ከገበሬው ቀዬ ከደረሱ በኋላ በፈጣን ሁኔታ ተቀነባብሮ የሚፈጸመው ሌብነት በእጅጉ የፊልም ያህል በሚደንቅ ሴራ የተወሳሰበ ነው። ይህንን የሌብነት ዘዴ ገበሬው ራሱ እንዲናገር ቢበረታታ ይሻላል። ሆዳቸው ከሕሊናቸው የገዘፈ ሹመኞች ለገበሬው የመጣውን ማዳበሪያና ኬሚካል ለነጋዴ እያሸጋገሩ እንደሚቸበችቡ አርሶ አደሮቹን የሚሰማቸው ጠፋ እንጂ በቂ መረጃ መስጠት ይችላሉ።

የድፍረታቸው ድፍረት አርሶ አደሩ “የማዳበሪያ ያለህ!” እያለ በሚጮኽበት በራሱ ቀዬ በሚቆሙ ገበያዎች ላይ ለእርሻ ግብዓት የሚያገለግሉ የአፈር ማዳበሪያና የተባይ መከላከያ መድኃኒቶች በሺህ እጥፍ ዋጋ ወጥቶላቸው ሲቸበቸቡ ማየት የተለመደ እንደሆነ ብሶተኞቹ በአደባባይ የሚመሰክሩት ነው።

ይኼው የፈረደበት አርሶ አደር በግብዓት እጥረት እርሻው ሲመክንበትና አዝመራው ሲነጥፍበት እጁን ለእርዳታ መዘርጋቱ የተለመደ ነው። ዓለም አቀፍ የተራድዖ ድርጅቶችና መንግሥታትም ይህንን እንደ ብርቱ ባሕልና ወግ የተጣባባን ችግር እንዲቀረፍ ሲረዱን የኖሩት “ደግሞ ኢትዮጵያ ተራበች!” እያሉ በመነጫነጭ እንጂ የወርቅ ሜዳሊያ በአንገቱ ላይ እንደሚጠለቅለት አሸናፊ አትሌት እያጨበጨቡልንና እያሞገሱን አይደለም።

> **“ከሰደበኝ መልሶ የነገረኝ ገደለኝ” እንዲሉ አበው፤ በርህራሄ እጃቸውን የሚዘረጉልን ሀገራትና ተቋማት የሚሉንን ሁሉ ደግመን ብናስታውስ ራሳችንን ሙልጭ አድርገን ከመስደብ ስለማይተናነስ፤ እንዲሁ “በሆድ ይፍጀው” ፈሊጥ ማለፉ ይበጃል**

እርስ በእርስ በግጭቶች ስንፋለምና አርሶ አደሩ ሲጎዳ ለእርዳታ እጅ መዘርጋት፣ ድርቅና ረሃብ ሲጠናወተን “ስለ ነፍስ ብሎ መማጠን”፣ አንበጣና ተምች ሲበረታብን “ድረሱልን!” እያልን እሪ ስንል “በሆዳቸው እያጉተመተሙም ቢሆን” የሕዝባችንን ነፍስ ላዳኑልን ሰብዓውያን ለእስካሁኑ በጎነታቸው ምሥጋናችንን ካልተጠየፉ “ለሰጭም እግዜር ይስጠው” ብለን ብንመርቃቸው ክፋት አይኖረውም።

ሰሞኑን እየሰማን ያለው አሳዛኝ መርዶ ግን ማስደንገጥ ብቻ ሳይሆን ምን ያህል “ብሔራዊ ክብራችንን” ዝቅ የሚያደርግ እንደሆነ መገመቱ አይከብድም። “ስም አይጠሬ” አንዳንድ ሀገራትና ተቋማት “ለኢትዮጵያ የምንሰጠው የእርዳታ እህል በሕገ ወጥ መንገድ እየተዘረፈና ለገበያም እየቀረበ መሆኑን ስላረጋገጥን ለጊዜው ምንም ዓይነት እርዳታ አንሰጥም” እስከ ማለት ደርሰዋል። ውሳኔያቸውን በምሥጢር ሹክ ቢሉን ባልከፋ ነበር። እጅግ የሚያሳዝነው ዜናውን ለመላው የዓለም ማኅበረሰብ ለማድረስ መፍጠናቸው ነው።

“ልብ ያለው ልብ ይበል!” የሚለው የቀዳሚ ዘመን ብሂል መታወስ ካለበት ሊታወስ የሚገባው በዚህ ወቅት ነው። ለምነንም፣ የለመኑትን ተሰራረቁ ተብለንም እንደምን ስማችን በድርብ ክስ ይጥፋ? “አለብሰን ብናርስ፤ በአረም መመለሳችን ስለማይቀር” ይህንን ጉዳይ ንቀንም ይሁን አፍረን ዝም ልንል የሚገባ አይመስለንም።

ይህም ሲባል “ጡንቻቸውን አሳይተው አንረዳችሁም” ካሉን መንግሥታትና ተቋማት ጋር እንካ ሰላንትያ እንግጠም ማለት ሳይሆን እፍረታችንን ለማደስ በራሳችን ላይ ኮስተር ያለ እርምጃ መውሰድ የሚገባን ይመስለናል። “የልመና እንጀራ ምንግዜም ከልመና አያወጣም” እንዲሉ መፍትሔው በራሳችን ላይ መጨከን ብቻ ነው። እንዴት? የመፍትሔውን መላ ምሑራንና ገዢዎቻችን ቀድመው ቢነግሩን የተሻለ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ እኛ “ተገዢ ዜጎችም” ሃሳባችን ቢደመጥ ክፋት ያለው አይመስለንም።

ለምሳሌ፡- የእርሻውን ዘርፍ ከማሳ እስከ ጉርሻ ከተተበተበት ውስብስብ ችግሮች ማላቀቅ። የሀገርን ውጪያዊ መልክ ከሚያደምቁ ወጭዎች ይልቅ ለመሠረታዊ የእርሻ ግብዓቶች ቅድሚያ መስጠት። ተፈላጊው ማዳበሪያም ሆነ ሌሎች ግብዓቶች ከአርሶ አደሩ እጅና አፍ የሚነጥቁትን “የኅሊና ድኩማን” በአግባቡ መቅጣትና ቅጣቱንም ያለምንም ይሉኝታ ለሕዝብ ግልጥ አድርጎ “እኔን ያየህ ተማር” እንዲሉ ማድረግ።

መከራው ወደ ልጆቻችን እንዳይሸጋገር መንግሥት እየተጋበት ላለው የተፈጥሮ አጠባበቅ ፕሮግራሞች ውጤታማነት “ቢርበንም ሆነ ቢጠማንም” ችለንና ጠንክረን ተባብረን አካባቢያችንን በመታደግ “ነፍሳችንን ማዳን። ” ሁሉንም ነገር ለመንግሥት ጥላቻ መግለጫነት ማዋል እስከ ዛሬ አልረባንም ወደፊትም ሊጠቅመን የሚችል አይደለም።

መንግሥት ግዴታውን ካልተወጣ ሊገሰጽና ሊወቀስ ግድ ነው። ነገር ግን ሁሉንም የመንግሥት እቅዶች ጥላሸት እየቀቡ መቃወምና መተቸት “የሚነቀፈውን ብቻ ሳይሆን፤ የተቼውን ማንነትም የሚገልጽ” መሆኑን ልብ ማለት ይገባል። መቼም ሳር ቅጠሉ ሁሉ ፖለቲካ የሆነበት ሀገር እንደ ኢትዮጵያ ሌላ ሀገር ይኑር አይኑር ለማወቅ ያዳግት ይመስለናል።

“ወንዞች ይገደቡ ይዋሉ ለልማት፤ በከንቱ ፈሰዋል ለብዙ ሺህ ዓመታት” የሚለው የደርግ ዜማ እውነታነት ስላለው ጠንክሮ ተፋሰሶቻችንን ሥራ ላይ ማዋል። “ይሄ ጉዳይ መች ይጠፋናል፤ እስከ ዛሬስ እየሠራንበት አይደለም ወይ!” የሚሉ የመንግሥት ሹመኞች እንደሚኖሩ አንጠራጠርም። አልፎም ተርፎም በምንሰጠው “አስተያየቶች” የሚዘባበቱም ሆነ ላለማንበብ ዐይናቸውን የሚጨፍኑ የፖለቲካው ጋሻ ጀግሬዎችና ሹመኞች እንደማይጠፉ እንገምታለን።

ይህ ጉዳይ ከተነሳ አይቀር ደፈር ብለን አምቀን ያቆየነውን ስሜታችንን ይፋ እንግለጠውና ለመሆኑ የመንግሥት ዋና ዋና ሹመኞች የሕዝቡ ሃሳብ የሚስተናገዱባቸውን ጋዜጦች ሥራዬ ብለው ያነቡ ይሆን? እነርሱ እንኳን ባይሞላላቸው በዙሪያቸው ያሉትን የበታች ሠራተኞቻቸውን “የጋዜጦችን አጢራራ” ማለዳ ማለዳ እንዲያቀርቡላቸው ያዟቸው ይሆን? መልስ ለመጠበቅ ሳይሆን እንደ ማስታወሻ ማቅረባችን እንደሆን ልብ ይባልልን።

አንዳንድ የተራድዖ ድርጅቶች “እርዳታ እስከማቆም የደረሱት” ምናልባት መንግሥት ስንዴ ወደ ውጭ መላክ መጀመሩ ስላልተመቻቸው ይሆን? ወይስ ያቆሙበት ምክንያት በርግጡ አሳማኝ ስለሆነ? እንደ እውነቱ ከሆነ የቀረበብን ክስ “ሀገራዊ ገጽታችንን ያጎድፋል ብለን በመስጋት” ብቻ ሙሉ ለሙሉ ምክንያታቸው ሐሰት ነው ብሎ መቃወሙም አግባብ ስላልሆነ መንግሥት የራሱን ጓዳና ጎድጓዳ ቢፈትሽ አይከፋም።

ይህ ሀገራዊ ተቃርኖ እልባት አግኝቶ እንዲፈታ የፖለቲካ ቁርጠኝነት ብቻ ሳይሆን ጾምና ፀሎት የታከለበት የእምነት ቤተሰቦችን ትጋት የሚጠይቅ ጭምር ሳይሆን ይቀራል? “እርግማን ካለብን” መፍትሔው ለሥራ እየተጉ ሕሊናን ከእድፈት፣ እምነትን በፈጣሪ ላይ መጣሉ ዋጋ ስላለው መሆኑን ልብ ይሏል። ሰላም ለሕዝባችን ለዜጎችም መልካም ፈቃድ።

# ተናጋሪው ዶሴ

## በሕዝብ በዓላት መሥራትና ክፍያ አለመፈጸም- በህግ ዓይን

ክፍለዮሐንስ አንበርብር



**የክርክሩ መነሻ**

ክርክሩ የተጀመረው በባህርዳር ወረዳ ፍርድ ቤት ነው። ዮቴክ ኮንስትራክሽን ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር በደል ደርሶብኛል ሲል በነገረ ፈጁ በኩል ለፍርድ ቤት አቤት ብሏል። አቶ ገብሬ በላይነህ፣ አቶ ግርማ ስንታየሁ፣ አቶ አበጀ ካሴ፣ አቶ መጣለም ገነት እና ወይዘሮ ገበያነሽ መኮንን ደግሞ በዚህ መዝገብ በዳይ ተብለው በመዝገብ ቁጥር 87338 የክስ ፋይል ተከፍቶባቸው ፍርድ ቤት ቀርበዋል።

ችሎቱም ግንቦት 21 ቀን 2005 ዓ.ም የመጨረሻውን ፍርድ የሚሰጥ በመሆኑ የችሎት ታዳሚዎች እና ባለጉዳዮች ግራ ቀኝ ከችሎቱ ፊት ለፊት ተቀምጠዋል። ጉዳዩም በአዋጅ ቁጥር 377/1996 መሠረት የቀን ሰራተኛ ሆነው የተቀጠሩ ሰራተኞች የሳምንት እረፍት ቀናት የዓመት እረፍት ቀናት እና የህዝብ በዓላት ቀናት ክፍያ ሊያገኙ የሚችሉበት ሕጋዊ አግባብ እያለ መብታችን ተነፍጓል በሚል የተጀመረ ክርክር ነው።

**የክሱ ይዘት**

የክስ ይዘትም በአመልካች ድርጅት በተለያየ ጊዜ በግንበኝነትና በአናፂነት ስራ ተቀጥረው በመስራት ላይ መሆናቸውንና ያገለገሉበትን ጊዜ ጠቅሰው በስራ ላይ በቆዩባቸው ጊዜያት ያልተጠቀሙበት የዓመት ፈቃድ የነበራቸው ከመሆኑም በተጨማሪ የሳምንት እረፍት የህዝብ በዓላት የሰሩበት ታስቦ ያልተከፈላቸው መሆኑን፣ ካሌንደሩ የማይዘጋቸው ቀናትም ያላአግባብ ተዘግተው ስራ ሳይሰሩ የቀሩ መሆኑን ጠቅሰው ለእያንዳንዳቸው ገንዘቡ እንዲከፈላቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው።

ዮቴክ ኮንስትራክሽንም ለክሱ በሰጠው መልስም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያና የፍሬ ነገር ክርክር አቅርቧል። ዮቴክ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ገልፆ የተከራከረው ጉዳዩ የወል የስራ ክርክር በመሆኑ በፍርድ ቤት ሊታይ የሚገባው አይደለም፣ ይህ ከታለፈም ክሱ በይርጋ የታገደ ነው የሚል ነው። በፍሬ ነገር ረገድም ተጠሪዎች በቀን የሚከፈላቸው ክፍያ በክሳቸው ላይ ያቀረቧቸው የክፍያ ጥያቄዎችን ክፍያ ከግምት ውስጥ አስገብቶና አጠቃልሎ የያዘ በመሆኑ የተለየ ክፍያ ሊኖር የሚችል ስለመሆኑ የሚሰራበት መሆኑንና በቅጥር ውሉ ላይ የተለየ እንደማይደረግ እና ክፍያ የሚፈፀምላቸው በካርዳቸው ላይ ስራ የተሰራባቸው ቀናት ተቆጥረው ስራ ለተሰራበት ቀን ብቻ እንደሚከፈል የተስማሙ ስለሆነ ጥያቄው አግባብነት የለውም በማለት ተከራክረዋል።

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የወረዳው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ በአመልካች በኩል የቀረቡትን መከራከሪያ ነጥቦችን ሙሉ በሙሉ ውድቅ አደረገ። ድርጅቱ ለከሳሾች የሳምንት እረፍት፣ የሕዝብ በዓላት እና የዓመት እረፍት ክፍያ በገንዘብ ተለውጦ እንዲከፍል ሲል ወሰነ። በዚህ ውሳኔ ዮቴክ ኮንስትራክሽን ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለምዕራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ ተጠሪዎች በቀን በሰሩት ስራ መጠን ታስቦ ክፍያ የሚፈፀምላቸው በመሆኑ የጠየቁትን የክፍያ ዓይነቶች ሊያገኙ አይችሉም በማለት የወረዳው ፍርድ ቤት በጉዳዩ ላይ የሰጠውን ውሳኔ ሙሉ በሙሉ ይሽረዋል። እንግዲህ የሥር ፍርድ ቤት የቀን ሰራተኞቹ ያቀረቡት ቅሬታ አግባብነት አለው፤ ሲል ዞኑ ደግሞ የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ በመሻር የተለያየ ውሳኔ ያሳልፋሉ። ይህ ነገሩን የበለጠ እንዲካረር አደረገው።

በዚህን ጊዜ የቀን ሰራተኞቹ የሰበር አቤቱታቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ችሎቱ ጉዳዩን መርምሮ ክርክሩ የግል የስራ ክርክር በመሆኑ በመደበኛ ፍርድ ቤት መታየቱ ተገቢ መሆኑን፣ ተጠሪዎች በቀን በሰሩት ታስቦ በወር የደመወዝ ክፍያ የሚከፈላቸው መሆኑ የተረጋገጠ መሆኑን በምክንያትነት ይዞና የሕጉ ጥያቄ ከኢትዮጵያ ህገ መንግስትም ሆነ ከአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንፃር ሲታይ ለክሱ መሰረት የሆኑትን የመብት ጥያቄዎች ተጠሪዎች ለመጠየቅ የማይችሉበት ሕጋዊ ምክንያት የለም የሚለውን አስቀመጠ።

በመቀጠል የቀን ሰራተኞቹ የሳምንት እረፍት ጊዜ፣ የሕዝብ በዓላትና በካሌንደሩ ላልተዘጉት ቀናት ክፍያ እንደሚገባቸው፣ የዓመት የረፍት ጊዜያት ግን የስራ ውሉ ባልተቋረጠበት ሁኔታ በገንዘብ ተቀይሮ ይከፈልን በማለት መጠየቅ የማይችሉ መሆናቸውን ዘርዝሮ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በመሻር የወረዳው ፍርድ ቤት የሠጠውን ውሳኔ በማሻሻል ሊስማማ ወይንም ሊያቀራርብ የሚችል ውሳኔ አስተላለፈ።

**ሰበር**

ጉዳዩ ወደ ሰበር አቤቱታ ያመራው ከላይ የተሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ በማሰብ ነበር። የሜቴክ አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም የቀን ሰራተኞቹ ጥያቄ ከራሳቸው አልፎ ሌሎች በተመሳሳይ ሁኔታ ተቀጥረው የሚሰሩትን በርካታ ሰራተኞችን ተመሳሳይ ጥያቄ እንዲያነሱ የሚያደርግ ሆኖ እያለ ክርክሩ የግል የስራ ክርክር መባሉ ያላግባብ ነው ሲል ተቃወመ። የቀን ሰራተኞቹ በስራ ላይ በቆዩባቸው ከሦስት ዓመታት የሚበልጥ ጊዜ ለሰሩባቸው ቀናት ብቻ እየታሰበ ሲከፈላቸው የነበረ መሆኑን፣ በቀን ታስቦ የሚከፈለው ገንዘብ የእሁድና የበዓላት ቀናትን የሚያጠቃልል መሆኑን ስራ ሲጀምሩ በተደረገው የስራ ውል ተስማምተው ክፍያው በዚሁ መልክ ሲፈፀም እና እየተሰራበት ያለ ሆኖ የቀን ሰራተኞቹ የተጠየቁት ክፍያዎች እንዲከፈሉ መወሰኑ ያለግባብ ነው በማለት አቤቱታ አቀረበ።

የጉዳዩ አመጣጥ ከስር መሰረቱ የመረመረው ችሎቱ የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች እና በሁለቱም ወገኖች ከተያዘው ጭብጥ አንጻር መረመረው።

ችሎቱም በምርመራው ከሳሾች የተጠየቁት የበአላት፣ የሳምንት እረፍትና የዓመት እረፍት ክፍያዎች አመልካች በስራ ላይ ተጠሪዎች ላሳለፉት ቀናት ብቻ እንጂ እነዚህን ክፍያ ሊፈጸም አይገባም፣ ተጠሪዎች ከሶስት ዓመት በላይ በሰሩበት ጊዜም እነዚህን ጥቅማ ጥቅሞች ጠይቀው አያውቁም በማለት ያቀረበው ክርክር ውድቅ መደረጉ ተገቢ መሆን ያለመሆኑን መረመረ።

በክርክሩ ሂደትም መገንዘብ የተቻለው ዮቴክ በኮንስትራክሽን ሥራ የተሰማራና ተጠሪዎችን ቀጥሮ ሲያሰራ የነበረው በግንበኝነትና በአናፂነት ስራ መሆኑን፣ አመልካች ለተጠሪዎች ለቀን ስራ የሚያስበው የደመወዝ መጠን የተለያየ ሆኖ አከፋፈሉ ግን በወር ተጠቃልሎ በፔሮል የሚከፈል መሆኑን ተደረሰበት። በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አግባብ ሲታይ ደግሞ በአጠቃላይ የቅጥር ውል አይነቶች ለተወሰነ ሥራ ወይም ለተወሰነ ጊዜ ወይም ላልተወሰነ ጊዜ ሊደረግ የሚችሉ ናቸው። ከዚህ አኳያ ሕጉ የቅጥር ውል አይነቱ ቋሚም ይሁን ጊዜያዊ ለሰራተኛው በሕጉ የተፈቀዱ ጥቅሞችና ከለላዎች የቅጥሩ አይነት መሰረት ተደርጎ ልዩነት ማድረግ የማይቻል መሆኑን ያብራራል። በመሆኑም ጊዚያዊ ሰራተኞችም ሆነ ቋሚ ሰራተኞች በሕጉ የተጠበቁላቸውን ጥቅማጥቅሞችንና ከለላዎችን እንደሚያገኙ የህጉ ይዘትና መንፈስ ያሳያል ሲል የምርመራ ውጤት ግኝቱን አስቀመጠ።

የአገሪቱ ሕገ መንግስት አንቀጽ 42(2) ድንጋጌ ሲታይ ደግሞ ሰራተኞች በአግባቡ የተወሰነ የስራ ሰዓት እረፍት፣ የመዝናኛ ጊዜ፣ በየጊዜው ከክፍያ ጋር የሚሰጡ የእረፍት ቀኖች፣ ደመወዝ የሚከፈልባቸው የሕዝብ በዓላት እንዲሁም ጤናማና አደጋ የማያደርስ የስራ አካባቢ የማግኘት መብት ያላቸው መሆኑን የሚያረጋግጥ ሆኖ ተገኘ። ይህ ህግ የሕጎች ሁሉ የበላይ የሆነው ሕገ መንግስት ድንጋጌ እነዚህን ጥቅሞችና ከለላዎችን የሚያገኙትን ሰራተኞች ብሎ በጥቅሉ ከማስቀመጥ ባለፈ የቅጥር አይነቱን ለይቶ አላሰፈረም።

በመሆኑም ጊዜያዊ ሰራተኞችም ቢሆኑ በሕገ መንግስቱ የተረጋገጡትን ጥቅሞችና ከለላዎች ተጠቃሚ የማይሆኑበት አግባብ የለም ሲልም አስረግጦ የህግ ክፍተት አለመኖሩን አስቀመጠ። ዮቴክ ኮንስትራክሽን አምስቱን ግለሰቦች የቀጠረው በኮንስትራክሽን ስራ መሆኑ ከተረጋገጠ የቅጥሩ ዓይነት ለተወሰነ ሥራና ጊዜ የተቀጠሩ መሆናቸው ግልፅ ቢሆንም በሕጉ የተጠበቁላቸውንና የተቀመጡላቸውን ጥቅሞች ከለላዎች ተጠቃሚ የማይሆኑበት ምክንያት የለም።

ከዚህ አንፃር ሲታይ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ፤ «አምስቱ ግለሰቦች የመብቶቹ ተጠቃሚ የማይሆኑበት ሕጋዊ ምክንያት የለም በማለት የሰጠው የውሳኔ ክፍል ሕጋዊ ሆኖ አግኝተናል» ሲል ደመደመ። ሌላኛው ከጊዜ ጋር በማያያዝ የሚያሳየው ክርክር ሲታይ አምስቱ ግለሰቦች በአመልካች ድርጅት ከሦስት ዓመታት በላይ ሲሰሩ የጥቅማ ጥቅሞችን ጥያቄ አንስተው ያለማወቃቸው የሚገልፅ ሲሆን እንዲህ መሆኑ ተጠሪዎች ጥያቄውን ከነጭራሹ እንዳይጠይቁ የማድረግ ሕጋዊ ውጤት የለውም በማለት ጉዳዩ በሦስት ዓመት ውስጥ በይርጋ የማይታለፍ መሆኑን አመላከተ። ምክንያቱም ደግሞ በሕጉ ተለይቶ የተቀመጠው የይርጋ ጊዜ ጥቅማ ጥቅሞችን ከማግኘት የሚያግዳቸው ከሚሆን በስተቀር የአመልካችን እርምጃ ሙሉ በሙሉ ሕጋዊ ሊያደርግ የሚችልበት ሕጋዊ አግባብ የሌለ መሆኑን ከአዋጁ አንቀጽ 162 ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ መገንዘብ የሚቻል መሆኑንም በዝርዝር አስቀመጠው።

በመሆኑም ዮቴክ ኮንስትራክሽን የቀን ሰራተኞቹ ለሦስት ዓመታት ያህል ጥያቄውን አላቀረቡም የሚለው ክርክር ተጠሪዎች ጥያቄውን ለማንሳት አይችሉም ለማለት የማያስችለው ህጋዊ መሰረት የለም። ይህም ብቻ ሳይሆን የሥር ፍርድ ቤቶችም በይርጋ የማይታገዱትን ክፍያዎች ለይተው የወሰኑ በመሆኑ በዚህ ረገድም የሕግ ስህተት የለም ሲል ቅልብጭ አድርጎ አስቀመጠ።

የዓመት እረፍትን በተመለከተም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ለተጠሪዎች እንደሚገባቸው፣ ግን የዓመት እረፍቱን መጠቀም ሲገባቸው በስራ ላይ እያሉ በገንዘብ ተቀይሮ እንዲከፈላቸው ጥያቄ ማቅረባቸው ከአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 77(5) ድንጋጌ አንፃር ተገቢነት የሌለው መሆኑን ገልፆ መወሰኑ ሕጋዊ እንጂ የሚነቀፍ አለመሆኑንም አስረግጦ አስቀመጠ።

ተከሳሾች ስራ ለመስራት ዝግጁ ሆነው ሳለ ዮቴክ ኮንስትራክሽን ስራ የመስጠት ግዴታውን ያለመወጣቱ የተረጋገጠ ሲሆን፤ ለእነዚህ ቀናት ደመወዝ የመክፈል ሕጋዊ ኃላፊነት የሚያስከትልበት ስለመሆኑ ከላይ ከተጠቀሰው አዋጅ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ መገንዘብ ይቻላል። በመሆኑም በዚህ ረገድ የተሰጠው ውሳኔም ነቀፌታ የሚቀርብበት አይደለም ሲል የሥር ፍርድ ቤቶቹ ያሳለፉትን ውሳኔ አግባብነት ያለው ስለመሆኑም በድጋሚ አረጋገጠ።

በአጠቃላይ የድምር ውጤት ሲታይም አምስቱ የቀን ሰራተኞች ለተወሰነ ስራ የተቀጠሩና ደመወዝ በቀን ሂሳብ ታስቦ በወር የሚከፈላቸው ቢሆንም በአዋጅ ቁጥር 377/1996 ለማንኛውም ሰራተኛ የተጠበቁትን ጥቅማጥቅሞችንና ከለላዎች የማግኘት መብታቸውን የሚነፈጉበት ሕጋዊ መሰረት የሌለ መሆኑን ሰበር በይፋ አስቀመጠ። በይርጋ ያልታገዱትን ጥቅማ ጥቅሞችን ብቻ በመለየት አምስት ተከሳሾች (ተጠሪዎች) እንዲያገኙ ተብሎ በተሰጠው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የሌለበት መሆኑ ሰበር በማያወላዳ በማስቀመጥ ውሳኔ አስተላለፈ።

**ውሳኔ**

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 24912 ጥር 06 ቀን 2005 ዓ.ም የተሰጠው ውሳኔ በፍትሃብሄር ሥነ ሥርዓት ቁጥር 348(1) መሰረት የታየ ሲሆን፤ አምስት ግለሰቦች በቀን ሂሳብ ታስቦ በወር ደመወዝ የሚከፈላቸው ለተወሰነ ስራ የተቀጠሩ ሰራተኞች ቢሆንም የሳምንት እረፍት፣ የሕዝብ በዓላት እረፍት ደመወዝ ክፍያ የማግኘት፣ የዓመት እረፍት የማግኘትና ያለካሌንደር የተዘጉ ቀናት ክፍያ ደመወዝ የማግኘት መብት አላቸው ተብሎ መወሰኑ ተገቢ ነው ሲልም የመጨረሻውን ውሳኔ አስተላለፈ።

መዝናኛ

# ማረፊያ/ ትዝብት

## የመንገድ ነገር ...

**መልካምሥራ አፈወርቅ**

በየጊዜው የሚስተዋለው ፈጣን የከተሞች ዕድገት እሰየው ያስብላል። ቀድሞ በአሮጌ ገጽታቸው የሚታወቁ በርካታ አካባቢዎች ዛሬ በዘመናዊ ሕንጻዎች ተተክተዋል። ትናንት ያለአንዳች ፋይዳ ዓመታትን የዘለቁ ስፍራዎች አሁን ይበል በሚያስብል ተግባራት መታየት ጀምረዋል።

እንደ እኔ ዕምነት በየጊዜው ይህን መሰሉን ለውጥ ማስተዋል በጎውን ትርጉም ከፍ ያደርጋል። ለምን ከተባለም በነዚህ ለውጦች ውስጥ ሌሎች በርካታ የእድገት እርከኖች ስለሚኖሩ። እውነት ነው የአንድ አካባቢ መለወጥና ማደግ ጠቀሜታው ለአንድ ወገን ብቻ አይደለም። በየጊዜው ታላቅ የለውጥ ግሰጋሴ በተፈጠረ ቁጥር ሌሎች በርካቶችም የቱርፋቱ ተቋዳሾች ይሆናሉ።

አንዳንዴ ግን በእንዲህ አይነቶቹ ለውጦች መሐል የሚታዩ እንከኖች ከፍ ያለችግር ሲያስከትሉ ይስተዋላል። ለምሳሌ የመንገድ ግንባታዎችና ተያያዥ ችግሮቻቸው።

ቀደም ሲል እንዳነሳሁት ለከተሞች ለውጥና ዕድገት መኖር የመንገድ ግንባታዎችም ከፍ ያለ አስተዋፅዖ አላቸው። ይህ እውነታ እንዳለ ሆኖ መንገዶቹ ሲጀመሩ አንስቶ እስኪጠናቀቁ ድረስ የሚስተዋሉ ችግሮች ደግሞ በአሳሳቢነታቸው ይጎላሉ።

ለአብነት የሚሆን አንድ ምሳሌ ልጥቀስ። እርስዎ በሚኖሩበት፣ አልያም በሚሠሩበት አካባቢ አንድ ቁፋሮ እየተካሄደ ነው። ይህ ቁፋሮ ረዘም የሚል መንገድ በመያዙ በአንድ ስፍራ ተገድቦ የሚቆይ ላይሆን ይችላል። ርቀቱን እየጨመረ፣ ጉድጓዱን እያጠለቀ የሚካሄደው ቁፋሮ በራሱ ብቻ አለመገደቡ የእግረኛ መንገዱን አስፋፍቶ ይዟል።

ይህ ብቻ አይደለም። የግንባታ ግብዓቱ ባልተገባ ቦታ በመዘርገፉ መራመጃ መላወሻ ይሉት መንገድ አይኖርም። ይህ አጋጣሚ ደግሞ በአካባቢው ለሚንቀሳቀስ ሁሉ ፈተና ሆኖ ይውላል። መንገዱ በእጅጉ መጨናነቁ በእግረኞች ብቻ አይወሰንም። የጎዳናውን ዳርቻ ተጠግተው የሚተላለፉ ተሽከርካሪዎች ሳይቀሩ ስፍራውን የሚሻሙት ይሆናል።

ወዳጆቼ እዚህ ላይ ለአብዛኞቻችን ስጋት የሆነን አንድ ጉዳይ ልብ እንድትሉት እሻለሁ። በእግረኞች መንገድ ላይ የተቆፈረው ጉድጓድ ሳያንስ የግብዓቱ መሙላትና የመኪኖች መተራመስ ብዙዎችን ለትራፊክ አደጋ እያጋለጠ ነው።

አብዛኛውን ጊዜ በትራፊክ አደጋ ሰዎች ሲሞቱ፣ አልያም ሲጎዱ ሊቀርብ የሚችለው ሪፖርት የተለመደው ዓይነት ነው። የአደጋው ዝርዝር ሁኔታና ዕለታዊ ሁኔታዎች ብቻ። ሁሌም በሪፖርቱ መስማት እንደለመድነው የአደጋው መንስኤ እየተጣራ መሆኑ ተጠቅሶ ይታለፋል። ምን አልባትም በእንዲህ አይነቶቹ አጋጣሚዎች ሊደርሱ የሚችሉ ችግሮች ትኩረት አይሰጣቸውም።

እንዲህ በሆነ ቁጥር ግን ችግሮች ከስሩ እንዳይቀረፉና እንዲባባሱ ምክንያት ይሆናል። በየጊዜው አካፋና ዶማቸውን ይዘው የእግረኞች መንገድን ለሚጋፉትም ኃይልና ብርታት እንደ መስጠት ይቆጠራል።

በአንዳንድ ስፍራዎች ለከባድ መኪኖችና አውቶቡሶች ሲባል የሚሠሩ መንገዶች ከያዙት ዓላማ አኳያ ግንባታቸው ለየት ያለ ትኩረት የሚሰጠው ነው። መንገዶቹ ጥራት፣ ስፋትና ጥንካሬ የተላበሱ እንዲሆኑም ልካቸውን የሚመጥን በጀት ተይዞ ግንባታ ይካሄድባቸዋል።

የመንገዶቹን ግንባታ ስንመለከት ሁላችንም እንደዜጋ የሚሰማን በጎ ስሜት ይኖራል። ትናንት በድንጋይ አልያም በጭቃማነት ገጽታው የምናውቀው ስፍራ ተለውጦ በዘመናዊነት ስናየው ከልብ ደስ ይለናል። ግንባታው ተጀምሮ የሚያልቅበትን ጊዜ እንናፍቃለን። የነገውን ውጤት አሻግረን እናያለን።

አንዳንዴ ግን እነዚህ ታላላቅ መንገዶች በታሰበው ጊዜ አለመጠናቀቃቸው ዋጋ ሲያስከፍሉ እናያለን። እንዲህ በሆነ ጊዜ ዋና የሚባሉ አዳዲስ መንገዶች ላይ ያልተገባ እንቅስቃሴ ይስተዋላል። በነዚህ መስመሮች መኪኖች ያለቦታቸው ይጓዛሉ። የፈረስ ጋሪዎች፣ ባጃጆች፣ እግረኞች በእኩል ይጋፋሉ።

ጥቂት የማይባል በጀት የፈሰሰበት፣ የመንገድ ግንባታ በጊዜ ያለመቋጨቱ ብዙ ሊገኝበት የሚችለውን ጥቅም እንደዋዛ ያሳጣል። በዚሁ ልክም ሥርዓት አልባው ጉዞ የትራፊክ አደጋውን ለማባባስ ምክንያት ይሆናል። ቁፋሮው ጉድጓድ፣ ጉድባና ሌሎች መሰናክሎች አሁንም ለመንገደኞች እንቅፋት ሆነው ይቀጥላሉ።

ይህን ጉዳይ በዚህ መልኩ ስንቃኝ ለችግሩ መከሰት ምክንያት በምክንያትነት ለሚጠቀሱ አካላት ደግሞ እውቅናን መስጠት ያስፈልጋል። ለተመሳሳይ ዓላማ ቦታውን የሚቆፍሩ አንዳንድ አካላት በስፍራው ሲገኙ ሊደርስ የሚችለውን ችግር አስቀድሞ በመከላከል ነው።

እነዚህ ተቋማት አካባቢውን ከጉዳት ለመጠበቅ በቁፋሮው ዙሪያ ጽሑፍ የታተመበት ባለቀለም ሪቫን ያስራሉ። ይሔኔ በስፍራው የሚንቀሳቀስ ሁሉ ምልክቱን እያስተዋለ ራሱን ከጉዳት ይጠብቃል። እንዲህ ማድረጋቸው የሰውን ሕይወት ሀገርን ሀብትና ንብረት ከጥፋት ለመታደግ አስተዋፅዖው የጎላ ነው።

በከተማችን የአስፓልት ዳርቻዎች የሚስተዋሉ ሕገወጥ ንግዶች ዓመታትን አስቆጥረዋል። በሥራው ያሉ ነጋዴዎች ከሸማቹ በቀጥታ ለመገናኘት ቀዳሚ ምርጫቸው የመንገድ ዳርቻዎች ናቸው። የዚህ ዓይነቶቹ ተግባራት ባብዛኛው የእግረኞችን መንገድ አስፋፍተው የሚይዙ ከመሆናቸው ጋር ለብዙኃን መሰናክል ሲሆኑ ቆይተዋል።

በስፍራው የሚዘወተረው የንግድ እንቅስቃሴ በተለይ ምሽቱን ይዞ የሚካሄድ ከሆነ የችግሩን ስፋት ይበልጥ ያጎላዋል። ብዙ ግዜ እንደሚስተዋለው እነዚህ ዳርቻዎች ለእግረኞች ፈጽሞ የተከለከሉ እስኪመስሉ የተጨናነቁ ናቸው።

በአጋጣሚ ጠርዙን ተከትሎ በአካባቢው የሚያልፍ መንገደኛ ቢኖር እንደነውር ሊቆጠርበት ይችላል። ምናልባትም ቦታውን አስፋፍተው ከያዙት ነጋዴዎች ውግዘትና ተቃውሞ ሊደርስበትም ይችላል።

አንዳንዴ ደግሞ መንገድ ሲዘጋጋ አማራጭ ፈላጊዎች በእግረኞች መንገድ መጓዝን እንደመብት ይቆጥሩታል። ዋናውን አስፓልት ለቀው በእግረኞች መራመጃ ላይ ሲጓዙ የማንም ፈቃድ አያሻቸውም። እንደውም መንገደኞች መንገድ ያለመልቀቃቸውን ጥፋት አድርገው በጡሩንባ እያጨናነቁ በስድብና በቁጣ መብት መንጠቅ ልማዳቸው ይሆናል።

በዚህ አይነቱ ልማድ የሚታወቁት አንዳንድ ሚኒባስ ታክሲዎች፣ ሞተረኞችና ሕግ አልባ የቤት መኪኖች ፊትና ኋላ እየተመራሩ ጎዳናውን ሲያጨናንቁ ሕግ አክብሮ የሚጓዘው እግረኛ መድረሻ የሚያጣበት አጋጣሚ የሰፋ ነው። እናም መንገድ መንገደኞችና ሕግ በአግባቡ ታርቀው እንዲጓዙ ማስተዋል ያሻል መልዕክታችን ይሁን።

# ዓለም አቀፍ

## በጭስ "በታፈኑት' የአሜሪካ ከተሞች በርካታ የአየር ጉዞዎችና መርሐ ግብሮች ተሰረዙ

በካናዳ ተቀስቅሶ ሚሊዮኖች ላይ ተጽዕኖ እያሳደረ ያለው የሰደድ እሳት በአሜሪካ ከተሞች ዋሽንግተን ዲሲና ፊላዴልፊያ ከተሞች ያለው የአየር ጥራት በዓመታት ውስጥ ታይቶ በማይታወቅ ደረጃ እንዲያሽቆለቁል ምክንያት ሆኗል። በዚህ የአየር ሁኔታ የተነሳ በመላው አሜሪካ የተለያዩ መርሐ ግብሮችና የአውሮፕላን ጉዞ እየተሰረዙ ነው።

በሰሜን አሜሪካ ወደ 10 ሚሊዮን የሚጠጉ ሰዎች እጅግ ዝቅተኛ ጥራት ያለውን አየር እየማጉ ይገኛሉ። የአሜሪካው ፕሬዚዳንት ጆ ባይደን ክስተቱን "የአየር ንብረት ለውጥ እያመጣ ያለውን ተጽዕኖ የሚያመላክት ትልቅ ማንቂያ ነው" ሲሉ ገልጸውታል። ከአሜሪካ የአየር ንብረት ጥበቃ ኤጀንሲ የወጣ የአየር ጥራት አመላካች በሰሜን አሜሪካ የሚገኙ ከተሞች የሐሙሱ በዓለም ላይ ካሉ ከተሞች ሁሉ እጅግ ዝቅተኛ ጥራት ያለው አየር እንደነበራቸው ጠቁሟል።

ዋሽንግተን ዲሲ፣ ፊላዴልፊያ እና ኒውዮርክ ሁኔታው ከከፋባቸው ከተሞች መካከል ይገኙበታል። በካናዳው ሰደድ እሳት ሳቢያ ከተሞችን የሸፈነው ጭስ የትምህርትና ስፖርታዊ ክንውኖች እንዲሰረዙ ምክንያት ሆኗል። በተጨሪም የተዘጉ መካነ እንስሳት ማዕከላት ያሉ ሲሆን በውስጣቸው ያሉ እንስሳትም ጭሱን ሽሽት ወደ ቤት ውስጥ እንዲገቡ ተደርጓል።

በአንዳንድ አካባቢዎች ነዋሪዎች የዕለተ ተዕለት ኑሯቸውን ለመግፋት የአፍ እና አፍንጫ መሸፈኛ ጭምብል (ማስክ) ለማድረግ ተገደዋል። የአሜሪካ ከተሞችን እያጥለቀለቀ የሚገኘው ጭስ መነሻው በካናዳዋ ኪዩቤክ የተነሳው ሰደድ እሳት ሲሆን ግዛቷ ታይቶ የማይታወቅ ሰደድ እሳት እያስተናገደች ነው። የተወሰኑ የካናዳ አካባቢዎች እጅግ የከፋ የአየር ብክለትን እየታየባቸው ነው።

የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ጆ ባይደን ከካናዳው ጠቅላይ ሚኒስትር ጀስቲን ትሩዶ ጋር ሐሙስ ዕለት በስልክ እንደተነጋገሩ የገለጹ ሲሆን በካናዳ የተቀሰቀሰውን ሰደድ እሳት ለመቆጣጠር አሜሪካ ከ600 በላይ የእሳት አጥፊ ባለሙያዎችን እንደምትልክ ጠቅሰዋል። በቶሮንቶ የሚታየው ጭስ እየጨመረ እንደሚመጣና ሁኔታዎች እንደሚከፋ የገለጸው የካናዳ የአየር ንብረት መሥሪያ ቤት ከቤት ውጪ የሚሆን ማንኛውም ሰው ማስክ እንዲያደርግ መክሯል።

በጭሱ ምክንያት የኒውዮርክ መገለጫዎች ለእይታ አስቸጋሪ ሆነዋል። ጭሱ ፈጣንና ዘላቂ የጤና ጉዳት ሊያመጣ



እንደሚችል የገለጹት የኅብረተሰብ ጤና ባለሙያዎች ሰዎች ወደ ውጪ እንዳይወጡ አሳስበዋል። እየታየ ካለው የሰደድ እሳት የሚወጣው ጭስ ለተዛባ የልብ ምት፣ ለደረት ሕመም ሊዳርግ የሚችል ሲሆን ዓይን፣ አፍንጫና ጎሮሮ ላይም ጉዳት ሊያስከትል እንደሚችል መግለጹን ቢቢሲ መረጃዎችን ጠቅሶ ዘግቧል።



ቮልከር ፔርትዝ

## ሱዳን ከተመድ ተወካይ ጋር እንደማትተባበር አስታወቀች

የሱዳን መንግሥት ከተባበሩት መንግሥታት ድርጅት (ተመድ) ልዩ ተወካይ ጋር እንደማይተባበር አስታውቋል። የሱዳን ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ የሱዳን መንግሥት ከተመድ ዋና ጸሐፊ ተወካይ ከሆኑት ቮልከር ፔርትዝ ጋር ከትናንት ጀምሮ እንደማይተባበር ገልጿል።

የሱዳን ጦር ዋና አዛዥ አል ቡርሃን ቀደም ሲል በቴርትዝ ላይ ቅሬታ ማቅረባቸው ይታወሳል። የሱዳን ተፋላሚ ኃይሎች በአሜሪካ እና ሳዑዲ ዓረቢያ ግፊት አማካኝነት በጂዳ ተኩስ አቁም እንዲደርሱ የተደረገው ጥረት አልተሳካም። ተፋላሚ ኃይሎቹ ካርቱምን ጨምሮ በትላልቅ ከተሞች የሚያደርጉት ጦርነት ቀጥሏል።

አሜሪካ በጂዳ ካሉት የሁለቱ ተፋላሚ ኃይሎች ጋር በተለይም የሰብዓዊ አገልግሎት አቅርቦት ማመቻቸትን በሚመለከት እየተነጋገረች መሆኗን ገልጻ ነበር። ከዚህ በተጨማሪም አሜሪካ በሱዳን ያለውን ጦርነት የማባባስ ሚና አላቸው ያለቻቸውን ሁለቱንም ኃይሎች በሚደግፉ ኩባንያዎች ላይ ማዕቀብ ጥላለች።

ከተጀመረ ከሰባት ሳምንታትን በላይ ያስቆጠረው ጦርነት 400ሺ ዜጎች ሀገራቸውን ለቀው እንዲሰደዱ ምክንያት ሆኗል። ይህ ጦርነት ሱዳንን 30 ዓመታት በላይ የገዙት ፕሬዚዳንት አልበሽር በሕዝባዊ አመጽ ከስልጣን መውረዳቸውን ተከትሎ ሊቋቋም የነበረው የሲቪል አስተዳደር አምክኗል።

ማህበራዊ

## መጋቢ አዕምሮ

# ራስን መግዛት

**አስናቀ ፀጋዬ**

ስኬታማ እንደምትሆንና እንደማትሆን የሚጠቁምህ ነው። የነገ ህይወትህ የጀርባ አጥንት ነው። በህይወታቸው ደስተኛና ስኬታማ የሆኑ ሰዎችም በዚህ እሳቤ ይስማማሉ። በርካታ ምርምሮችና የጥናት ውጤቶችም የስኬታማ ሰው ቁልፍ ፀባይ እሱ መሆኑን ይመሰክራሉ-ራስን መግዛት ወይም /self discipline/።

ስኬት ከመቶ ቢታረም ዘጠና ከመቶው ዲስፕሊን ነው። ራስን መግዛት ከትናንሽ ልፋቶች ጀርባ ህልምህን ለማሳካት የሚገፋህ ኃይል ነው። ከዚህ ውጪ የምታልመው ህልም ጭንቅላትህ ውስጥ የቀረ ምስል ብቻ ሆኖ ይቀራል። መሬት ማውረድ አትችልም። ህልምህን መሬት የምታወርደው ዲስፕሊን ካለህ፣ ራስህን ከተቆጣጠርክና ራስህን ከገዛህ ነው።

ልክ ስትነቃቃ ወይም የመስራት ፍላጎት ሲኖርህ የምታደርገው ነገር ትልቅ ለውጥ አይሰጥህም። ስፖርት መስራት ልትጀምር ትችላለህ። ማንበብም እንደዛው። አዲስ ቋንቋ ትለማመዳለህ። ራስህን ማሳደግ ትጀምርና የሆነ ሰዓት ላይ ታቆማለህ። አየህ ዲስፕሊን ያለው ሰው አያቆምም። ምኞት ባይኖረውም የጠበቀውን ትልቅ ለውጥ ቶሎ ባይሰጥህም የዛሬውን ቅፅበታዊ፣ ጊዜያዊ ደስታህን አዘግይተህ ለነገህ ትልቁ እርካታህ ዋጋ የምትከፍልበት መንገድ ነው ዲስፕሊን።

የተሻለ ህይወት አላቸው፣ ትላንትናቸውን ቀይረውታል፣ ከነበሩበት ችግር ወጥተዋል የምትላቸውንና የምታከብራቸውን ሰዎች ሁሉ አስተውል። ውጫዊ ገፅታቸው ላይ ከሚታየው ደስታ፣ ጥንካሬና እርካታ ጀርባ አንድ ተመሳሳይ ነገር አላቸው። ዲስፕሊን! እነዚህ ሰዎች ትልቅ ደረጃን በአንዴ ካልወጣን ብለው ክቾች ከማለት ይልቅ ትናንሽ እርምጃዎችን በልካቸው ሰርተው በየቀኑ እነዚህን ደረጃዎች እየወጡ ከግባቸው የደረሱ ናቸው። ወሳኙን ነገር አውቀውታል። ስኬት የአንድ ቀን ተግባር ብቻ እንዳልሆነ ገብቷቸዋል። ራሳቸውን መግዛት ላይ ተከነውበታል። ህልማቸው ጋር ለመድረስ በሃሳብ ከመኳተን ይልቅ ዲስፕሊንን መጓጓዣቸው አድርገውታል።

በርግጥ በቀላሉ በወሰድናቸው እርምጃዎች በምናገኘው ደስታ ልንሳሳት እንችላለን። የምንኖርባት ዓለም ራሱ አንድን ነገር ለማድረግ አቋራጭ መንገዶችን ላሳያችሁ በሚሉ ሰዎች የተሞላች ነች። ቀላል የተባለው ነገር ሲነገድ የሚዋልባት ገበያ ነች ዓለም። ምንም ብታገኘውም ታዲያ ከዚህ ገበያ ቀላሉን አትምረጥ። እውነተኛው ስኬት በአቋራጭ አይገኝም። የራስህ የሆነውን ከፍታ የምታገኘው በዚህ ቀላልን በምትሰብክ ዓለም ላይ አንተ ከባዱንም እንደምትቋቋም ስታሳይ ነው።

ምን ያህል ለአላማህ ፅኑ እንደሆንክ ስታስመሰክር፣ አሻግረህ ማየት ስትለምድ፣ ሲደክምህ፣ ሰውነትህ ለስራ ሳይጋበዝ ሲቀር መተኛት፣ ቲቪ ማየት እያማረህ አንተ ግን ስሜትህን አሸንፈህ ስለ አላማህ አንድ ርቀት ስትጓዝ ያኔ ትክክለኛውን ከፍታ ታየዋለህ። ይህ አይነት ራስን የመግዛት ጥንካሬ የሚከተሉትን አምስት ቅደም ተከተሎችን አትርሳ።

**1ኛ. ራስህን በሚገባ አጥና**

በየቀኑ የምታደርገውን ነገር አስተውል። ውሎህ ምን ይመስላል? ዓላማህስ ምንድን ነው ? ምን አቀድክ? የእለት ተእለት ተግባርህ ምንድን ነው? ከዓላማህ ጋር አብሮ የሚሄድ አንድ እንኳን ድርጊት በየቀኑ ታደርጋለህ? ሁሌም ቢሆን የቀን ውሎህን ለነገ ስኬትህ መሰረት እንዲሆን አድርገህ ቅረፀው። ከዛሬው ግዜያዊ ምኞትህ ይልቅ የነገው የረጅም ግዜ ድሎትህ ይበልጣል በልና የሩቁን አስቀድመው።

ስታስብ የምትውለው ምንድን ነው? ምክንያቱም አስተሳሰብ ተግባርን ይወስናል። ተግባር ደግሞ መድረሻህን ይወስናል። ግልፅ የሆነው ግብህ ምን እንደሆነ አስብ። እዚያ ላይ ለመድረስ የሚያስፈልግህን ለውጥና ተግባር ለእያንዳንዱ ቀን አከፋፍለው። ስራህን በትንሹ ጀምር። ለዚህ እቅድህ ቆራጥ ሁን። በአጓጊ ነገሮች አትሰናከል። ይሔ ነው ዲስፕሊን ማለት።

ውሎህን ስትመርጥ አስተሳሰብህን ስታቃና ታዲያ አብረው የሚውሉትን ሰዎች አስተውል። ምክንያቱም አንተ ብዙውን ግዜ አብረሃቸው ከምትውላቸው አምስት ሰዎች አማካይ ነህ። ከአምስት ሰነፍ ሰዎች ጋር የምትውል ከሆነ ስደስተኛው ሰነፍ አንተ ነህ። ከአምስት ጎበዝ ሰዎች ጋር ከዋልክ ግን ስድስተኛውም ጎበዝ ሰው አንተ ነህ።

> **ራስን መግዛት ማለት ከነገ ህልማችን ጋር አብረው የሚሄዱ ትናንሽ ምርጫዎችን በየቀኑ መምረጥ ነው። አሁን ልደሰት ካልክ ስሜትህ ሲያረኩልህ የሚችሉ በርካታ ነገሮች አሉ። ነገ ልደሰት ካልክ ግን አሁን ዋጋ እንድትከፍል የሚያስገድዱ ብዙ ነገሮች አሉ። ያንን ማመጣጠን ነው እንግዲህ ዲስፕሊን ወይም ራስን መግዛት ማለት። የማትጨነቅበትና ትክክለኛ ነፃነትን የምታገኝበትን ህይወት የምትኖረው በዚህ መንገድ ብቻ ነው። ይህን መንገድ ከተረዳኸው መጨነቅ ሳይሆን በማመስገን ትኖራለህ**

ያንተን ማንነት የዛሬው ውሎህ ይወስነዋል። ከሚያጠነክሩህ፣ ራስህን ለመግዛት ያለህን ተነሳሽነት የሚደግፉ ሰዎች ጋር መዋል አለብህ። ራስን መግዛት ግን ደስታ የሌለውና የተጨቆነ ህይወት መምራት ማለት አይደለም። ብዙ ግዜ ዲስፕሊን ወይም ራስን መግዛት የሚለው ሃሳብ ሲነሳ ብዙዎች ‹‹እኔ እንደዚህ የተጨናነቀ ሕይወት መኖር አልፈልግም›› ይላሉ። ሃሳብንና ስሜትን ከመገደብና ራስን ከማስጨነቅ ጋር ያያይዙታል።

ነገር ግን ራስን መግዛት ማለት ከነገ ህልማችን ጋር አብረው የሚሄዱ ትናንሽ ምርጫዎችን በየቀኑ መምረጥ ነው። አሁን ልደሰት ካልክ ስሜትህ ሊያረኩልህ የሚችሉ በርካታ ነገሮች አሉ። ነገ ልደሰት ካልክ ግን አሁን ዋጋ እንድትከፍል የሚያስገድዱ ብዙ ነገሮች አሉ። ያንን ማመጣጠን ነው እንግዲህ ዲስፕሊን ወይም ራስን መግዛት ማለት። የማትጨነቅበትና ትክክለኛ ነፃነትን የምታገኝበትን ህይወት የምትኖረው በዚህ መንገድ ብቻ ነው። ይህን መንገድ ከተረዳኸው መጨነቅ ሳይሆን በማመስገን ትኖራለህ።

**2ኛ.ወስን**

የህይወትህን ኃላፊነት በራስህ ላይ ጣል። አንተን በሚመለከቱ እድገቶች ላይ አተኩር። ድክመትህን ለይተህ አውቀህ ያንን ለማስተካከል ወስን። ታዲያ ውሳኔህ ወጥነት ይኑረው። በህይወትህ ሁለት ምርጫዎች አሉህ። አንደኛው በትክክለኛው መንገድ ፀንቶ መሄድ ወይ ደግሞ ተስፋ ቆርጦ መተው ነው። ሁለቱም ከባድ ምርጫዎች ናቸው። በትክክለኛው መንገድ ሄደን ህልማችንን ለማሳካት የምንታመመው እስኪሳካ ነው። በተስፋ መቁረጥና በመቆጨት የምንኖረው ህይወት ግን የዘላለም ህመም ነው፤ ፀፀት ነው።

በዛሬው ሁኔታህ ላይ ተመስርተህ ሳይሆን የነገውን ተስፋህን አይተህ ወስን። አየህ ግዚያዊ ደስታ አይሸውድህም። ነገን አስቀድም ማለት ነው። ሁሌም ዲስፕሊንን እንደመርህ አድርገህ ተቀበለው። ብዙ ሰዎች ለመለወጥ ተአምር ይጠብቃሉ። ይህ ግን የማይሆን ነገር ነው። ተአምር ያለው በየአንዳንዱ ቀንህ ውስጥ ነው። ትክክለኛ ውሳኔ መወሰንህ ውስጥ ነው ተአምር ያለው። ያለበለዚያ ከሰማይ የሚወርድ ከምድር የሚፈልቅ ተአምር የለም።

አንድ ሃውልት ቀራፂ ድንጋዩን ለመቅረፅ በሚጠቀመው ሹል መዶሻ የሚያሳርፈው አንድ ምት ምን አልባት ሊሰራ ላሰበው ሃውልት ምንም ጥቅም የሌለው ሊመስል ይችላል። ነገር ግን እነዚህ ተደጋጋሚ ትናንሽ ምቶች ሃውልቱን ይቀርፁታል። እኛም በየቀኑ የምናሳርፈው የዓላማችን ትናንሽ ምቶች ናቸው ህይወታችንን የሚቀርፁት። ትናንሽ እርምጃዎች ኃይል የሚኖራቸው ያለማቋረጥ በፅናት ስናደርጋቸው ነው። ከግዜ ወደ ግዜ ሲጠራቀሙ ሊሰጡን የሚችሉት ውጤት ተአምር ነው።

ለምሳሌ በቀን ለሰላሳ ደቂቃ ምንሰራው ስፖርት ምን አልባት የሚታይ ለውጥ ላያመጣ ይችላል። ነገር ግን በነዚህ ትናንሽና ተደጋጋሚ እርምጃዎች ውስጥ ቁልፉ ጉዳይ የእኛ ፅናት ነው። ታዲያ ስለምናደርገው ነገር ቀጣይነት ብቻ ሳይሆን ጠቃሚነትም ልናስተውል ይገባል። ገበሬ የሚዘራውን ነገር መርጦ እንደሚዘራ ሁሉ አንተም የምትከተለውን ልማድ በትኩረት መምረጥ አለብህ። እያንዳንዱ እርምጃህ ማቅናት ያለበት ወደ ዓላማህ ብቻ ነው። 3ኛ.ዓላማ ያዝ

የቤተሰብ፣ የህይወት፣ የስራና የሁሉም ዓላማ ሊኖርህ ይገባል። አለበለዚያ ዓላማ ያለው ሰው አገልጋይ ነው የምትሆነው። ገንዘብ፣ መኪና፣ ልብስ ብቻ አይደለም መቅደም ያለበት። እነዚህ የልፋትህ ክፍያዎች፤ የጥረትህ ጭራዎች ናቸው። አንተ በጣም በጣርክ ቁጥር ሲሳካልህ እነዚህ ነገሮች ይከተሉሃል። ፍፁም ደስታ የሚሰጠን፣ መኖራችንን ትርጉም የሚሰጠን፣ ህይወታችንን ሙሉ የሚያደርግልን ዓላማ ያስፈልገናል።

ያንን ምክንያት ፈልጎ የመኖር ዓላማህ ምንድን ነው? ሁሌም ደካማነት ሲሰማን ጥሩ ስንቅ ይሆነናል ዓላማ። ‹‹ዓላማ ከሌለህ ትሞታለህ›› የሚባል አንድ የጥንት አባባል አለ። ሰዎች ማንን ማግኘት እንደሚፈልጉ፣ የት መሄድ እንደሚፈልጉ፣ ማዳበር የሚፈልጉትን ክህሎት ወይም መሆን የሚፈልጉት ነገር ይኖራል። ለማሳካት መሰልቸትን ማሸነፍ ይኖርብሃል። ይሄ የወደፊት እይታችንና እቅዳችን ነው። መሆን እንችላለን ብለን ያመንበትን ነገር ነው። ያለበለዚያ ህይወት ዋጋ አይኖረውም።

ነገር ግን ግልፅ የሆነ እይታ ካለን የሚከፈለውን ዋጋ እንከፍላለን። እንማራለን። ክህሎቱን እናዳብራለን።

ነገን ለመቅረፅ ዋጋ እንከፍላለን። ቁጭ ብለን ልንመኝ እንችላለን። እንዲህ ቢሆን ኖሮ እያልንም ልናስብ እንችላለን። መጀመሪያ ግን የያዝነውን ድንቅ አእምሮ ካላዘዝንበት፣ የሚታዘዘውን ሰውነት በድካም ውስጥ እንኳን ታታሪ እንዲሆን ካላደረግነው በቁጭት መኖራችን አይቀሬ ነው። ሁኔታዎች አንተ ብትደሰትባቸውም ባትደሰትባቸውም መሆን እንዳለባቸው ይሆናሉ። ይህን መቀየር አትችልም። አንተ ግን ራስህን መቀየር ትችላለህ። የተሻለ ሰው ከሆንክና ከሁኔታው በልጠህ ከተገኘህ ሁሌም የተሻለውን ነገር ታገኛለህ። በዙሪያህ ያለውም አብሮ ይለወጣል።

**4ኛ.ከትናንሽ ተግባሮች ጀምር**

መለወጥ የወሰንክ ግዜ ለራስህ ትናንሽና ቀላል ተግባሮችን መከወን ጀምር። ራስህ ላይ አታክብድበት። ራስህን መግዛት ከፈለክ ከበደኝ ብለህ እንደትተወው በአቅምህ ልክ ፍላጎትህን ከፋፍለው። ትልቅ ቦታ የሚደርስ ነገር የሚጀምረው በትናንሽ ነገር ግን ወጥ በሆኑ እርምጃዎች ነው። የየቀኑ ልማዶችህን ትቀይራለህ። መጥፎ የምትለው ተግባሮችን ሁሉ ቀስ በቀስ በጥሩ ተግባሮች ትተካቸዋለህ። ትጋት ግን የግድ ያስፈልግሃል። ራስህን ስትገዛው ዲስፕሊንድ ስትሆን አይምሮህ በለመደው መንገድ እንዲሰራ እያዘዝከው ስለሆነ እስክትለምደው ግዜ ይወስዳል። ብቻ ግን ቁርጠኛ ሁን።

ምንአልባት ዛሬ አደርጋለሁ ብለህ ያሰብከውን ሳታደርገው ልታድር ትችላለህ። ከዛ እኔ እኮ ድሮም ራስን ለመግዛት አልታደልኩም። ይሄ ነገር መቼ ይሆንልኛል ብለህ ነው ብለህ እርግፍ አድርግህ አትተወው። ለምሳሌ ማጨስ ማቆም አለብኝ ትልና ሁለት ቀን ታግሰህ በሶስተኛው ቀን ስትሸነፍ በጭራሽ ልታሳካው እንደማትችል ታስባለህ። የመጀመሪያው ነገር ይህን በብዙ ዓመት የተገነባ ሱስ በቀናት ውስጥ አሸንፋዋለሁ ብለህ ከባድ ውሳኔ ውስጥ አትግባ። ወስን ግን በቀላሉ መለወጥን አትተጠብቅ። በመጀመሪያ ውስጥህ የሚያስደስተውን መልካም ልማድ ፈልግ። ከዛ መጥፎውን ልማድ በምታከናውንበት ሰዓት እነዚህን መልካም ልማዶች ማድረግ አዘውትር። በዚህ መንገድ ታሳካዋለህ።

አቅማችንን ሁሉ አሚጠን የምንሰጠው አንድ የተፈጠርልነት ነገር ይኖራል። ስትጀምር ታዲያ አንድ ብር ካለህ በዛ ጀምር። ብዙ ነገር ሊጎድልህ ይችላል። በቃ ከነጉድለትህም ጥረትህን ጀምር። ከታመምክ ታማሚ ሆነህ ትጀምራለህ። ሁሉ ነገር ኖሮህ ካላስደሰተህ አመስጋኝ ሆነህ ትጀምራለህ። ብቻ ጀምር። አስበው እስኪ ያልካቸውን መፅሃፍት ብታነብ፣ ያሰብከውን ትምህርት ብትማር ዲስፕሊን፤ ቆራጥነት ቢኖርህ ፕ! ምን ማድረግ ትችላለህ? እነዚህኑ ዛሬውን በትንሹ ጀምራቸው። በትልቅ የሚያልቁ ታሪኮች ተስፋ ይሰጡናል። በመሃል ያሉትን ትግል ግን መረዳት ይገባል። በየቀኑ ወጥ በሆነ መንገድ ዘላቂ ሆነህ ካንተ የሚጠበቀውን ስታደርግ ህይወት ብዙ አስገራሚ ነገሮችን ታሳይሃለች። ያላሰብከው ሲሳይ እጅህ ላይ ይወድቃል።

ቁጭ ብለህ ግን እድሎች አይመጡም። እድሎች ቢመጡም ራሱ አትጠቀምባቸውም። አንዳንድ ሰዎች የአቅማቸው ልክ በሚፈተንበት ከባድ ሁኔታ ውስጥ ይገባሉ። በብዙ ፈተና ያልፋሉ። ላቁመው ልቀጥለው የሚል ፀብ ከራሳቸው ጋር ይገባሉ። ይሰቃያሉ። ነገር ግን ከዚህ ሁሉ ጭንቀት ውስጥ አስደማሚ ለውጥን ይዘው ይወጣሉ። እነዚህ ሰዎች የሰው ልጅ የአቅም ችግር እንደሌለበት ምስክር ናቸው።

**5ኛ. በየቀኑ ራስህን አሻሽል**

ራስህን ለመግዛት ከፈለክ በየቀኑ ራስህን ማሻሻል ይጠበቅብሃል። ከትላንት የተሻለ ለመሆን ጣር። ለምሳሌ የተሻለ ባለሞያ፣ የተሻለ ተናጋሪ፣ የተሻለ ተግባቢ መሆን ልትፈልግ ትችላለህ። ስትጀምረው፤ ለለውጥህ ስትጓጓ በእያንዳንዱ እርምጃህ የሚያስደስት ነገር ታገኛለህ። ለቀጣዩ እርምጃህ ይጋብዝሃል። ሁሌም የመማርና የመለውጥ ጉጉትህ ይኑርህ። በስራ ቦታህ አለህ ብቻ አትባል። ለውጥ ፈጣሪ ሁን። የሚማር አስተማሪ፣ የሚማር አባት ለምትመራው ቦታ የሚማር መሪ ሁን። የመማርና የመለወጥ ውስጣዊ ፍላጎት ካለህ ራስን መግዛት አይከብድህም። ዲስፕሊን ማምጣት አይከብድህም።

በቀን አስር ገፅ ማንበብ ማለት በወር ሁለት መፅሃፍ ማንበብ ነው። በዓመት ደግሞ ሀያ አራት መፅሃፍቶች ማንበብ ነው። ‹‹ይሄ እውነት ከሆነማ ለማንበብ ቀላል እኮ ነው›› ልትል ትችላለህ። ማወቅ ያለብህ ነገር ግን ለማድረግ ቀላል የሆነው ነገር ላለማድረግም ቀላል ነው። ማድረግ እንዳለብህ ካላደረከው አንተ የውድቀትን ቀመር እየቀመርክ ነው። እናም ዛሬውኑ አንድ ነገር ማድረግ ጀምር። ለዚህም ማድረግ እችላለው በል።

ኢኮኖሚ

# ስኬት

# “አይቻልምን” የሰበረው የስራ ፈጣሪዋ መንታ ስኬት

ፍሬሕይወት አወቀ

የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርቷን በትውልድ አካባቢዋ የቀድሞው ባሌ ክፍለ አገር፤ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቷን ደግሞ አዲስ አበባ አቃቂ አድቬንቲስት አዳሪ ትምህርት ቤት ተከታትላለች። የ12ኛ ክፍል ትምህርቷን ባጠናቀቀች ማግስት ስደት አጓጉዞ ከባህር ማዶ ከሆላንድ አገር አደረሳት። በባዕድ አገር የብቸኝነት ኑሮ በሕይወት ትግል ውስጥ ብዙ ተምራለች። ከስደት ሕይወት የቀሰመችውን ትምህርት፣ በመውጣት በመውረድ ውስጥ ያካበተችውን ልምድና ተሞክሮ ቀምራ ረጅሙን ጉዞ በአገሯ ለማድረግ ሌት ተቀን ተግታለች።

ከላይ ታች የመውጣት የመውረዱ ትጋትና ጥድፊያዋ ሁሉ አገሯ ገብታ አዳዲስ ሥራዎችን ለመሥራትና የሥራ ዕድል ለመፍጠር እንደነበር ታስታውሳለች። አገሯ ገብታ ሰርታ ለማሰራት በነበራት ጥድፊያና ጉጉትም ብዙ ደንቃራዎች ገጥመዋት ሁሉንም በጽናት አልፋለች። ከስደት ለመመለስ በተሰናዳችበት ወቅት ‹‹አገሬ ጎደሎዋ ምንድን ነው?›› በማለት ራሷን ጠይቃለች። ለጥያቄዋ ምላሽ ብዙ ጎዶሎዎችን መመልከት ብትችልም ‹‹ሃምሳ ሎሚ ለአንድ ሰው ሸክሙ፤ ለሃምሳ ሰው ጌጡ›› እንዲሉ፤ እርሷ በአቅሟ የምትችለውን ለማድረግ መውተርተር ጀመረች። የዕለቱ የስኬት አምድ እንግዳችን ወይዘሮ እመቤት ታደሰ።

ከሁለት አስርት ዓመታት በኋላ ስደት ደህና ሰንብት በማለት ከሆላንድ ወደ ትውልድ አገሯ ኢትዮጵያ ተመልሳለች። የ12ኛ ክፍል ትምህርቷን ባጠናቀቀች ማግስት ስደት የወጣችው ወይዘሮ እመቤት፤ በውጭው ዓለም ስትኖር ሕይወት ብዙ እንዳስተማረቻት ትናገራለች። በሕይወት ውጣ ውረድ ውስጥ ብዙ ያሳለፈች ቢሆንም፣ ‹‹እችላለሁ›› የሚል ጠንካራ እምነት የነበራት በመሆኑ ያሰበችውን ሁሉ በከፍተኛ ጥረትና ትጋት ማሳካት ችላለች። ‹‹ምንም ሳይኖረኝ በሆላንድ አገር ሬስቶራንት ለመክፈት አቅጄ ከፍቻለሁ›› የምትለው ወይዘሮ እመቤት፤ ወደ ትውልድ አገሯ በተመለሰች ጊዜም በተለያዩ የሥራ ዘርፎችን ለመሥራት ስትሞክር ‹‹ተይ አይሆንልሽም›› በማለት ወደ ኋላ የሚጎትቷት ብዙዎች ነበሩ።

እርሷ ግን ያሰበችውን ሳታሳካ እንቅልፍ የማይወስዳት በመሆኗ፤ አይሆንም የተባለውን እንዲሆን በማድረግ ሁለት ያልተለመዱ የሥራ አማራጮችን ይዛ ብቅ ብላለች። በሆላንድ አገር ስትኖር የምግብ ጥበቃና እንክብካቤ ትምህርትን በዲፕሎማ የተማረችው ወይዘሮ እመቤት፤ በአገረ ሆላንድ የአፍሪካውያን ሬስቶራንት ከፍታ ሠርታለች።

በውጭው ዓለም ማንኛውም ሰው ገንዘብ ስላለው ብቻ ተነስቶ ማንኛውንም ሥራ መሥራት አይችልም። ስለሚሠራው ሥራ ዕውቀት ሊኖረው የግድ ነው የምትለው ወይዘሮ እመቤት፤ የምግብ ጥበቃና ክብካቤ ትምህርት እንደመማሯ የመጀመሪያ የሥራ አማራጭ አድርጋ የጀመረችው ሥራ ፈጣን ምግብ (Fast Food) ማዘጋጀትን ነው።

በወቅቱ ሥራው አገር ውስጥ የተለመደ ካለመሆኑ ጋር ተያይዞ ብዙ ድካም እንደነበረው የምታስታውሰው ወይዘሮ እመቤት፤ በምግብ ዘርፍ ብዙ ክፍተት እንዲሁም ብክነት ስለመኖሩ አጫውታናለች። ሆቴሎች የሚሰጡት አገልግሎት በቂ ካለመሆኑ ጋር ተያይዞ በርካታ ክፍተቶችን ተመልክታለች። በተለይም አትክልትና ፍራፍሬ ኢትዮጵያ ውስጥ ጥቅም ላይ ከሚውለው ይልቅ ተበላሽቶ የሚጣለው ይበልጣል በማለት ቀደም ባለው ጊዜ ፒያሳ የነበረውን አትክልት ተራ በማስታወስ ሰፊ ብክነት እንደነበር ታዝባለች። ይህን መነሻ በማድረግም አትክልቶች ሳይበላሹ ረዘም ላለ ጊዜ እንዲቆዩ የማድረግ ሥራ እንደጀመረች ትገልጻለች።

ከሁለት አስርት ዓመታት የውጭ ቆይታ በኋላ ወደ አገሯ ጠቅልላ የመጣችው ወይዘሮ እመቤት፤ የሚታጠብ ዘላቂ የሴቶች ንጽህና መጠበቂያ ምርት ለማምረት እንዲሁም የምግብ ሥራን ለመሥራት የወሰነች ቢሆንም አስቀድማ የጀመረችው ግን የምግብ ሥራውን ነው። የምግብ ሥራው አትክልቶች ተልጠው፣ ተከትፈውና ለምግብነት ተዘጋጅተው ረዘም ላለ ጊዜ በማቆየት መጠቀም የሚቻልበት ዘዴ




ወይዘሮ እመቤት ታደሰ

ነው። ይህ ዘዴ በውጭው ዓለም ተግባራዊ ሲደረግ ከማየት ባለፈ ሥራዋ እንደነበር ያነሳችው ወይዘሮ እመቤት ሥራውን ለመጀመር አላመነታችም።

ድንች፣ ካሮት፣ ፎሰሊያና ሌሎች አትክልቶችም ታጥበው፣ ተልጠውና ተከትፈው ረዘም ላለ ጊዜ በማቆየት ለምግብነት ማዋል በውጭው ዓለም የተለመደ ቢሆንም፤ በአገር ውስጥ ይህን ተግባራዊ ለማድረግ ትንሽ ተፈትናለች። በወቅቱ የነበሩ ጥቂት ሱፐርማርኬቶችም ቢሆኑ በራቸው ክፍት አልነበረም። ይህም ገበያ ውስጥ ለመግባት ብዙ አታግሏታል። ያም ቢሆን ለችፕስ አገልግሎት የሚውለው ድንች ከውጭ የሚገባ እንደሆነ ከእነዚህ ከሱፐርማርኬቶች በሰማች ጊዜ ‹‹ኢትዮጵያ ድንች ለምን ከውጭ ታመጣለች›› የሚል ቁጭት ገብቷታል። ቁጭቷን በሥራ በመወጣት አስፈላጊውን እንክብካቤ በማድረግ ድንችን አዘጋጅታ ለሱፐርማርኬቶች የማቅረብ ሥራዋን አንድ ብላ ጀምራለች።

ከሱፐርማርኬቶች በተጨማሪም ወደ ሸራተን አዲስ እና ሂልተን ሆቴል በመሄድ ድንች በተገቢው እንክብካቤ አዘጋጅታ ለማቅረብ ተስማማች። ድንቹ የሚጨመርበት ምንም አይነት ግብዓት አለመኖሩን ያነሳችው ወይዘሮ እመቤት፤ በሚፈለገው የሙቀት መጠን በስሎና በአግባቡ ታሽጎ ማቀዝቀዣ ውስጥ ለረጅም ጊዜ መቀመጥ እንደሚችል ነው ያስረዳችው። በትላልቅ ሆቴሎች የሚቀርቡት የድንች ጥብስ (ችብስ) በዚህ መልኩ የሚዘጋጁና ከውጭ አገር የሚገቡ እንደነበርም አጫውታናለች። “እርግጥ ነው ከውጭ የሚመጣው የድንች አይነት ይለያያል” የምትለው ወይዘሮ እመቤት፤ በአሁኑ ወቅት በአገር ውስጥ ያለው የድንች ዝርያም እየተሻሻለ መሄድ የቻለ በመሆኑ ከውጭ የሚገባው የተቀቀለ ድንች እየቀረ መሆኑን ተናግራለች።

ለዚህም አንድ ምክንያት ነኝ የምትለው ወይዘሮ እመቤት፤ ተቀቅሎ ለችፕስ የተዘጋጀ ድንች ሸራተንና ሂልተንን ጨምሮ በተለያዩ ሆቴሎች ተደራሽ እያደረገች እንደሆነም አጫውታናለች። ከድንች በተጨማሪ ሌሎች አትክልቶችንም በአግባቡ አጥቦ፣ ከትፎና አስፈላጊውን ክብካቤ አድርጎ በማቀዝቀዣ ማስቀመጥና ረዘም ላላ ጊዜ መጠቀም እንደሚቻልም ነው የገለጸችው።

ከዚህ በተጨማሪ ሁለተኛ ዕቅዷ የነበረውን የሚታጠብ ሞዴስ ወይም ዘላቂ የሴቶች የንጽህና መጠበቂያ ምርት ለማምረት ከላይ ታች ያለችው ወይዘሮ እመቤት፤ ከብዙ ድካም በኋላ “ማሪዮድ የሚታጠብ የሴቶች ንጽህና መጠበቂያ” በሚል የንግድ ስያሜ ወደ ማምረት መግባቷን ገልጻለች።

ዘላቂ የሴቶች ንጽህና መጠበቂያን ለማምረት መነሻ ምክንያቶቿ ብዙ ስለመሆናቸው በማንሳት፤ ‹‹የሴቶች የንጽህና መጠበቂያ/ሞዴስ/ ድህነት ሴት ተማሪዎችን ወደ ኋላ የሚጎትት ነው›› ትላላች። ሴት ተማሪዎች የንጽህና መጠበቂያውን በቀላሉ ማግኘት ባለመቻላቸው ከትምህርት ገበታ ከመቅረት ጀምሮ የተለያዩ ግፍና በደል ይደርስባቸዋል ስትል ገልጻ፤ ይህን ችግር ለመከላከል የሚወስዱት መፍትሔ ደግሞ ወደ ኋላ የሚጎትታቸው ከመሆኑም በላይ ያልተገቡ ግብአቶችን እንዲጠቀሙ እያደረጋቸው መሆኑን ተናግራለች። ይህም ከፍተኛ ለሆነ የጤና ቀውስ የሚዳርጋቸው መሆኑን በመገንዘብ ለጉዳዩ ትኩረት መስጠቷን ትናገራለች።

ኢትዮጵያ ውስጥ ከፍተኛ የሆነ የሴቶች የንጽህና መጠበቂያ/ሞዴስ/ ድህነት ስለመኖሩ ያነሳችው ወይዘሮ እመቤት ከስደት መልስ ትኩረት ሰጥታ የሠራችውም በዚሁ ምክንያት ነው ትላለች። ዘላቂ የሴቶች የንጽህና መጠበቂያን በአገር ውስጥ ለማምረት ስትነሳ ሃሳቡ አዲስና የመጀመሪያ እንደመሆኑ ተቀባይነትን ለማግኘትና ጠቀሜታውን ለማስረዳት ብዙ ታግላለች። በትግሎቿም ወደኋላ ለሚጎትቷት ደንቃራዎች ሳትበገር ውጥኗን ከዳር ለማድረስ ተግታለች። የችግሩ ገፈት ቀማሽ እንደነበረች በማስታወስም ችግሩ አንገብጋቢና ከፍተኛ ትኩረት የሚያሻው እንደሆነ ትናገራለች።

‹‹የሚታጠብ አልያም ዘላቂ የሴቶች ንጽህና መጠበቂያ ላምርት ብዬ ስነሳ ብዙ ሰው ስቆብኛል፤ እንዴት በዚህ ዘመን ስለሚታጠብ ሞዴስ ታወሪያለሽም ተብያለሁ›› የምትለው ወይዘሮ እመቤት፤ ችግሩን ተቸግራ የኖረችበት በመሆኑ ከሃሳቧ አልቀረችም። አስፈላጊውን ሁሉ አሟልታ ለመጀመሪያ ጊዜ ያመረተችውን ዘላቂ የሴቶች የንጽህና መጠበቂያ አስቀድማ ለራሷ ተጠቅማዋለች። በአገልግሎቱ እርካታ ማግኘት እንደቻለች የምታስታውሰው ወይዘሮ እመቤት፤ ወደ ሥራው ከገባች አስራ አራት ዓመታት ቢቆጠርም አሁንም ድረስ ምርቱን ለሁሉም ሴቶች ተደራሽ ማድረግ እንዳልተቻለ ነው ያስረዳችው።

እሷ እንደምትለው፤ ምርቶቹን ለሁሉም ሴቶች በቀላሉ ተደራሽ ለማድረግ ሰፊ የማስታወቂያ ሥራ እንዲሁም የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ ያስፈልጋል። በአሁኑ ወቅት ምርቶቹ መንግሥታዊ ባልሆኑ የውጭ አገር ለጋሽ ድርጅቶች አማካኝነት በገጠሪቷ ኢትዮጵያ እየደረሱ ይገኛሉ። የሴቶች የንጽህና መጠበቂያ / ሞዴስ/ ድህነት በከተሞች ሳይቀር ስር የሰደደ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ሰፊ ሥራ ሊሠራበት ይገባል፤ ምርቱ ተኪ ምርት እንደመሆኑ በአገር ውስጥ በስፋት ቢመረትና ገበያ ውስጥ እንደልብ ቢገባ የሚኖረው አበርክቶ ጉልህ ስለመሆኑም አጽንኦት ሰጥታ ተናግራለች።

በውጭ ምንዛሪ ወደ አገር ውስጥ የሚገባው የሴቶች የንጽህና መጠበቂያ ምርት በአገር ውስጥ ለመተካት በሚደረገው ጥረት መንግሥትን ጨምሮ የሚመለከታቸው አካላት ሊረባረቡ እንደሚገባ ያስገነዘበችው ወይዘሮ እመቤት፤ ምርቱ ለሁለት ዓመታት የሚያገለግል በመሆኑ ለተማሪዎች አይነተኛ መፍትሔ ነው። በተለይም ተማሪዎች በንጽህና መጠበቂያ ምርት እጥረት ከትምህርት ገበታቸው እንዳይጎድሉ ከማድረግ ባሻገር የውጭ ምንዛሪን በማስቀረት ረገድም ትልቅ ድርሻ እንዳለው ትገልጻለች። ለተደራሽነቱ በብርቱ እንትጋ ስትልም ነው ያሳሰበችው።

ስደት ደህና ሰንብት በማለት በሁለት ያልተለመዱ የሥራ ዘርፎች ተሰማርታ እየታገለች ያለችው ወይዘሮ እመቤት፤ በሁለቱም ዘርፎች 70 ለሚደርሱ ዜጎች በቋሚነትና በጊዜያዊነት የሥራ ዕድል መፍጠር ችላለች። በቀጣይም ፈጣን ምግቡንም ሆነ ዘላቂ የሴቶች ንጽህና መጠበቂያ ምርቶችን በስፋት አምርቶ ወደ ገበያው የመግባትና ተጨማሪ የሥራ ዕድል የመፍጠር ሰፊ ዕቅድ አላት።

‹‹ትልቁ ትኩረቴ ዘላቂ የሴቶች ንጽህና መጠበቂያው ላይ ነው›› የምትለው ወይዘሮ እመቤት፤ በተለይም ‹‹የአካል ጉዳት ያለባቸው ሴቶች ያሳስቡኛል›› ነው የምትለው። ለዚህም አመቺ ነው ያለችውን የንጽህና መጠበቂያ በቀላሉ መጠቀም እንዲችሉ በማድረግ ሰርታለች። ዊልቸር ላይ የዋሉ አካል ጉዳት የደረሰባቸው ሴቶች የማንም እርዳታ ሳያሻቸው በቀላሉ በራሳቸው መጠቀም የሚያስችላቸውን የውስጥ ሱሪና የንጽህና መጠበቂያም አምርታለች። ከዚህ በተጨማሪም ለሆስፒታሎች የሚያገለግል አንሶላን ጨምሮ ሴቶች በሚወልዱበት ወቅት የሚጠቀሙትን እንዲሁም በተለያዩ ምክንያቶች አልጋ ላይ ለዋሉ ሰዎች የሚያገለግል የአዋቂዎች ዘላቂ የንጽህና መጠበቂያም ታመርታለች።

የንጽህና መጠበቂያ ምርቶቹ ኮተን በሆኑ ጨርቆች የሚመረቱ መሆናቸውንም ጠቅሳ፣ ቆዳ ላይ ምንም አይነት የማሳከክ ችግር የማይፈጥር እንደሆነም ነው የገለጸችው። ለዚህም ከጤና ሚኒስቴር የማረጋገጫ ሰርተፊኬት ማግኘት ችላለች። ኮተን ከሆነው ጨርቅ በተጨማሪ እንደ ቁልፍና ውሃ የሚይዘውን ፕላስቲክ ከውጭ በማምጣት የሚመረተው ዘላቂ የሴቶች ንጽህና መጠበቂያ ምንም አይነት ኬሚካል የሌለው መሆኑን ጠቅሳ፣ ከውጭ ከሚገባው ይልቅ ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ ያለው ስለመሆኑም አስረድታለች።

ምርቱን አጥበው መልሰው መጠቀም የሚችሉት በመሆኑ ከአካባቢ ብክለት ጋር ተያይዞ የሚመጡ ችግሮችን ያስቀራል። ነገር ግን ከውጭ የሚገባው የሴቶች የንጽህና መጠበቂያ ወይም ሞዴስ በየአካባቢው ተጥሎ አካባቢን ሲበክል ይስተዋላል። በተለይም በጋራ መኖሪያ ቤቶች አካባቢ የፍሳሽ ማስወገጃ ቱቦዎችን በመዝጋት ቀዳሚ የሆነው ይኸው የንጽህና መጠበቂያ ሞዴስ መሆኑን ያመላከተችው ወይዘሮ እመቤት፤ የህጻናት ዳይፐርም ሌላው ችግር እንደሆነ በመጠቆም በአገር ውስጥ ተኪ ምርት ላይ ሰፊ ሥራ ቢሠራ መልካም እንደሆነ ትመክራለች።

የህጻናት ዳይፐርም ሆነ የሴቶች የንጽህና መጠበቂያ ምርቶችን በአገር ውስጥ ምርት መጠቀም የሚኖረው አበርክቶ ዘርፈ ብዙ እንደሆነ በመግለጽ፤ ሴቶች አቅማቸው ፈቅዶ ሞዴስ ቢገዙም በየቦታው የሚጣል በመሆኑ አካባቢን ከመበከል ባለፈ እንስሳት እንዲበሉት ዕድል የሚፈጥር በመሆኑ ጉዳቱ የትየለሌ ነው ስትል ትገልጻለች። ስለዚህ ከውጭ የሚገባውን የሴቶች የንጽህና መጠበቂያ ሞዴስ በአገር ውስጥ በሚመረተውና መልሶ ጥቅም ላይ በሚውለው ምርት በመጠቀም ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ተጠቃሚ እንሁን የምትለው ወይዘሮ እመቤት፤ በተለይም ሁሉም ሴቶች ምርቱን በቀላሉ ገዝተው መጠቀም እንዲችሉ ግንዛቤ በመፍጠር ለማስተዋወቅና ለመጠቀም እንበርታ ብላለች።

‹‹በአገር ውስጥ ያለውን የሴቶች የንጽህና መጠበቂያ/ሞዴስ/ድህነትን ከማንም በላይ እኔ አውቀዋለሁ›› የምትለው ወይዘሮ እመቤት፤ በተለይም በትምህርት ቤቶችና በገጠሪቷ ኢትዮጵያ ችግሩ የከፋ እንደሆነ ነው ያነሳችው። ምርቱን በስፋት ገዝተው በገጠራማ አካባቢዎች ተደራሽ የሚያደርጉት የውጭ ድርጅቶች ሲሆኑ፤ በከተሞች አካባቢ በሚገኙ አንዳንድ ትምህርት ቤቶች ምርቶቹን በመለገስ ማህበራዊ ኃላፊነቷን እየተወጣች እንደሆነም አጫውታናለች። በመጠለያ ጣቢያዎች ለሚገኙ ተፈናቃዮችና በጦርነት ምክንያት ጉዳት ላይ ላሉ ሴቶች ምርቱን እያቀረበች መሆኑን በመጥቀስ፤ የሚታጠብ የሴቶች የንጽህና መጠበቂያ ምርት ከውጭ የሚገባውን መተካት የቻለ ተኪ ምርት እንደመሆኑ ሙሉ ለሙሉ ጥቅም ላይ እንዲውል እንሥራ የሚል መልዕክቷ አስተላልፋለች።

ኢኮኖሚ

# መሠረተ ልማት

## ተወዳዳሪ የኮንስትራክሽን ኩባንያዎችን መፍጠር - ቀጣዩ የዘርፉ አብይ ተግባር

ኃይሉ ሣህለድንግል

የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው በአሁኑ ወቅት በግብአት አቅርቦት በተለይ በሲሚንቶ እጥረት በእጅጉ ፈተና ውስጥ መሆኑ ይታወቃል። የሲሚንቶ እጥረቱ በርካታ ፕሮጀክቶች እንዲጓተቱ፣ የፕሮጀክቶች ዋጋ እየናረ እንዲሄድ፣ ተቋራጮች ላይ አሉታዊ ተጽእኖ እያሳረፈ ስለመሆኑም በተለይ የዘርፉ ተዋንያን አጽንኦት ሰጥተው ይጠቁማሉ። የዘርፉ ፈተና የግብአት እጥረት ብቻ አለመሆኑንም ነው እነዚሁ አካላት የሚያመለክቱት።

በቅርቡ የከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስቴር በቀጣይ ሊያዘጋጀው ላቀደው አዲስ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ፖሊሲ ሰነድ ግብአት ለማሰባሰብ ከዘርፉና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመከረበት መድረክ ላይ እንደተጠቆመውም፤ ከግብአት አቅርቦት እጥረት በተጨማሪ የፋይናንስ አቅርቦት እጦት፣ የተቋራጮች የመወዳደር አቅም ውስንነት ሌሎች የዘርፉ ፈተናዎች ሆነዋል።

የውጭ ምንዛሬን ጨምሮ በአጠቃላይ የፋይናንስ እጥረት ለዘርፉ የሚያስፈልጉ ማሽነሪዎችን ለማግኘት፣ ግብአቶችን ከውጭ ለማስመጣት ተግዳሮቶች ተፈጥረዋል። ኢንዱስትሪው በዘርፉ ተወዳዳሪ ለመሆን መቸገሩን ተቋራጮችን ጨምሮ በዘርፉ የተሰማሩ አካላት ይጠቁማሉ።

መንግስት ግዙፍ ፕሮጀክቶችን ለውጭ ኩባንያዎች እየሰጠ ያለበት ሁኔታ እንዳሳሰባቸውም የኮንስትራክሽን ዘርፉ ተዋንያን ይናገራሉ። በአጠቃላይ ዘርፉ ክፉኛ መታመሙን በመጥቀስ፣ ለመፍትሄው መስራት እንዳለበትም ጠቁመዋል። በአንድ ወቅት ኮንስትራክሽን ያበበባት ኢትዮጵያ አሁን ዘርፉ ለመቀዛቀዝ የተዳረገባት መሆኗ ተጠቁሟል።

አንዳንዶች ችግሩ ሰፊ መሆኑን በመጥቀስ፣ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ውድቀት አርገው ወስደውታል። በአንጻሩ ዘርፉ ብዙ ፈተናዎች ውስጥ የሚገኝ ቢሆንም እድሎች እንዳሉትም በመድረኩ ተጠቁሟል። አዲስ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ፖሊሲ ረቂቅ ሰነድ ለማዘጋጀት ግብአት ለማሰባሰብ በተካሄደው መድረክ ላይ ለውይይት መነሻ የሚሆኑ ሶስት ጥናቶች ቀርበዋል። ጥናቶቹ በኮንስትራክሽን ግብአት እንዲሁም በፋይናንስ አቅርቦትና ተወዳዳሪ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ በመፍጠር ላይ ያተኮሩ ሲሆኑ፣ መድረኩ ለዘርፉ ባለድርሻ አካላት ሀሳብ ሰፊ ጊዜ የሰጠና በርካታ ጉዳዮች የተነሰቡትም ነው።

የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ለኢትዮጵያ መሰረታዊ ኢንዱስትሪ መሆኑን በመድረኩ ላይ ማብራሪያ የሰጡት የኮንስትራክሽን ማኔጅመንት ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር ኢንጅነር ታምራት ሙሉ ይገልጻሉ። ከአገሪቱ ካፒታል በጀት ውስጥ ከ60 እስከ 65 በመቶው በኮንስትራክሽን ዘርፉ እንደሚንቀሳቀስ ጠቁመው፣ ስለአገር ልማት ሲታሰብ ቅድሚያ ኢንቨስትመንት ሆኖ የሚመጣው ኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው መሆኑን አመልክተዋል። የአገሪቱ የልማት አጀንዳዎች ሊሳኩ የሚችሉትም በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ፍጥነት ልክ መሆኑ ዋና ዳይሬክተሩ ጠቅሰው፣ የኮንትስትራክሽን ኢንዱስትሪው ካላደገ አገራዊ እድገትን ማሰብ አይቻልም፤ ይህን ኢንዱስትሪ ረስተን የትም መድረስ አንችልም ሲሉም አስገንዝበዋል።

በመድረኩ ላይ የተገኙት የከተማ እና መሰረተ ልማት ሚኒስቴር የመሰረተ ልማት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ ኢንጂነር ወንድሙ ሴታ እንዳሉት፤ ኢንዱስትሪው እንደ አገር ብዙ እድሎች አሉት። ከእነዚህ እድሎች ውስጥ ተግባራዊ እየተደረገ ባለው የአስር አመቱ መሪ እቅድ አገሪቱን መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገሮች ተርታ ለማሰለፍ የተያዘውን ራእይ ይጠቀሳል።

በእዚህ ራእይ ሁሉም ግቦች ወስጥ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ሚና ከፍተኛና ዘርፉ ለሁሉም ልማት መግቢያና ፈር ቀዳጅ መሆኑን ሚኒስትር ዴኤታው ጠቁመዋል፤ ሚኒስትር ዴኤታው እንዳብራሩት፤ በአስር ዓመቱ እቅድ ከ102 ሺ ኪሎ ሜትር በላይ የአዳዲስ መንገዶች ግንባታ፣ ከ28 ሺ ኪሎ ሜትር በላይ የመንገዶችን ደረጃ የማሳደግና ማጠናከር ስራ፣ ከ3 ሺ ኪሎሜትር በላይ የባቡር መስመር ግንባታ፣ ከ4 ሚሊየን በላይ ቤቶች ግንባታ፣ የአውሮፕላን ማረፊያዎችና ሌሎችም ግንባታዎች የኮንስትራክሽን ዘርፉን የሚፈልጉ ናቸው።

እድሎች አንዳሉ ሁሉ አብረው ደግሞ ፈተናዎችም



ፎቶ- በከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስቴር

ለሚቀረጸው ፖሊሲ ከተሰብሳቢዎች ግብአቶች፤ ከመድረኩም ተጨማሪ ሀሳቦችና ማብራሪያዎች ተሰጥተዋል

አሉ ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፣ እነዚህን ፈተናዎች በአግባቡ መለየት፤ የሚፈቱበትን መንገድ ማስቀመጥና ዘርፉ ለአገር ማበርከት ያለበትን አስተዋጽኦ እንዲያበረክት ማድረግ ይገባል ብለዋል። የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪውን አሁናዊ ችግሮች በመፍታት የኢኮኖሚ እድገት ፍላጎትን የሚመጥን የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ዘርፍ ለመፍጠር የዘርፉን ችግሮች የሚፈታና የእድገት ፍላጎትን የሚመጥን የአሰራር ስርአት መዘርጋት ወቅቱ የሚጠይቀው አንገብጋቢ ጉዳይ መሆኑንም አስታውቀዋል።

እንደ እሳቸው ማብራሪያ፤ ይህንን እድል በመጠቀም የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪውን ችግር መፍታት ያስፈልጋል። በእነዚህ እድሎች የተመለከቱ ግቦች ያለኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ተወዳዳሪነትና ብቃት አይሳኩም። የዘርፉን ችግር መፍታት ለእነዚህ ግቦች መሳካት አስተዋጽኦ ያደርጋል። የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው በዘላቂነት ተወዳዳሪ ሆኖ አቅሙ ተገንብቶ እንደገና ለሚቀጥሉት የልማት ግቦች አቅም የሚሆንበት ምቹ ሁኔታ መፍጠር ላይም መስራት ይኖርበታል።

በአዲሱ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ፖሊሲ ሰነድ እንዲታይ የተጠቆመው አንዱ ጉዳይ የተቋራጮች የተወዳዳሪነት አቅምን ማሳደግን ይመለከታል። በአስር አመቱ አገራዊ እቅድ የአገር በቀል ተቋራጮችን የተወዳዳሪነት አቅም በማሣደግ ቢያንስ 75 በመቶ የሚሆነውን የገበያ ድርሻ፣ ከዚያም ባለፈ ደግሞ ቢያንስ 25 በመቶ የሚሆኑን ሪጂናል/የምስራቅ አፍሪካ አካባቢ/ ድርሻ እንዲኖራቸው ለማድረግ ታቅዷል። አሁን ያለው የተቋራጮች የተወዳዳሪነት አቅም ግን አነጋጋሪ መሆኑ በመድረኩ ተጠቁሟል። ተወዳዳሪ መሆን መቻል ቀርቶ ኢንዱስትሪው ውስጥ መቆየትም ስጋት እየሆነ እንደሚገኝ ነው የተመለከተው።

መንግስትም በሚዘጋጀው አዲስ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ፖሊሲ ከሚመለከታቸው ጉዳዮች አንዱም ይሄው ሆኗል። የተቋራጮች የመወዳደር አቅም፣ የአማካሪዎችና የባለሙያዎች አቅም ግንባታ በመድረኩ በሰፊው ተዳሷል።

ሚኒስትር ዴኤታው ኢንጂነር ወንድሙ እንዴት ተደርጎ ተወዳዳሪ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ መገንባት እንደሚቻል ሲናገሩ፤ ቅድሚያ ስራ አርገን የወሰድነው ትላልቆቹ ተቋራጮች በዓለም አቀፍ ደረጃ መወዳደር እንዲችሉ ማድረግ እንዲሁም ውድድሮችን መቋቋም የሚችሉ ኩባንያዎችን መፍጠር፣ ትንንሾቹ ደግሞ አቅማቸውን እየገነቡ እንዲሄዱ ማድረግ ነው ሲሉ ያብራራሉ።

ከዚህ አኳያ እንደ መንግስት ዘርፉን እንደሚቆጣጠር አካል የራሳችንን የአሰራር ስርአት ማስተካከል ላይ መስራት ይኖርብናል ያሉት ኢንጂነር ወንድሙ፣ ከዚህ አኳያ እስከ አሁን ስራ ላይ ያለውን የተቋራጭ፣ የአማካሪ እና የባለሙያ የምዝገባ መመሪያዎችንና የአሰራር ስርአቶችን ማሻሻል እንደሚያስፈልግ አስታውቀዋል።

በአገሪቱ ተቋራጮች፣ አማካሪዎች እና ባለሙያዎች ብዛትና ብቃት ጉዳይ ሌላው አነጋጋሪ ጉዳይ መሆኑም በመድረኩ ተጠቁሟል። ሚኒስትር ዴኤታው እንዳሉት፤ በአገሪቱ አጠቃላይ ያለው ተቋራጭ ብዛት ከ26ሺ ይበልጣል፤ በቅርቡ ባለው መረጃ ደግሞ 22 ሺ ተቋራጭ ነው ያለው፤ ከዚህ ውስጥ በሚገባ እየተንቀሳቀሱ የሚገኙት ደግሞ ሁለት ሺ995 ብቻ ናቸው።

እሳቸው እንዳሉት፤ አማካሪዎችን በተመለከተ ደግሞ አንድ ሺ ሶስት መቶ አካባቢ አማካሪዎች ናቸው በአገሪቱ እንዳሉ የሚታወቀው፤ አሁን ገበያ ላይ ያሉት ግን 285 ብቻ ናቸው። ወደ 138 ሺ እና 140 ሺ ባለሙያዎች ቢኖሩም፣ በገበያው ውስጥ በየዓመቱ እያደሱ ያሉት ከ25 እስከ 26 ሺ የሚደርሱት ብቻ ናቸው።

‹‹በዚህ ላይ የውሸት ቁጥር ነው ያለን። ካሉን ሁለት ሺ ዘጠኝ መቶ ተቋራጮች መካከል አገሪቱ ልትሰራ የምትፈልገውን አፋጣኝ ፕሮጀክት የሚሰራ ተቋራጭ ብንፈልግ 20 አናገኝም›› ሲሉም ጠቅሰው፣ ከ20ውም መካከል በተለያየ ምክንያት የሚንጠባጠብ እንደሚኖር ተናግረዋል። ይህን ማጥራትና ወደምንፈልገው ደረጃ ማምጣት ይኖርበታል ሲሉ አስገንዝበዋል።

ከዚህ አኳያ የተቋራጮች፣ አማካሪዎችና ባለሙያዎች ምዝገባ ስርዓት ማሻሻል አለብን ብለን የጀመርነው ስራ አለ። ከባለሙያም አኳያ እንዲሁ ብቁ /ሰርቲፋይድ/ ያልሆኑ ባለሙያዎች ዘርፉ ውስጥ መቆየት አይኖርባቸውም፤ እንዲህ ስንል ስለብቃት /ኮፒተንስ/ ማሰብ ይጀመራል፤ እንዲህ ሲሆን ኢንዱስትሪው ውስጥ ያለውም ገበያ ውስጥ ዘላቂ ሆኖ ተወዳዳሪ ሆኖ መቀጠል ያስባል ብለዋል። ስለዚህ በብቃት የሚሰራበት ከባቢ መፍጠር ይኖርብናል፤ ከዚህ አኳያ ማሰልጠን፣ መመዘን፣ ሰርቲፋይድ ማድረግ ከዚያም የሙያ ፈቃድ መስጠት ያስፈልጋል ሲሉ አብራርተዋል።

እሳቸው እንዳሉት፤ በቀጣይ የተቋራጮችን ደረጃ ለማውጣት አንዱ መስፈርት የሚሆነው ፕሮጀክት የመምራት አቅም ይሆናል። ቁጥር ብቻ ተይዞ ደረጃ አይሰጥም፤ ደረጃ የሚሰጠው የፕሮጀክት አስተዳደር ብስለት መስፈርት /ኢንዴክስ/ እየታየ ነው። አስር ኢንዴክሶች አሉ፤ በእነዚህ ኢንዴክሶች መሰረት የብቃት ደረጃው ከደረጃ ሶስትና ከዚያ በላይ የሆነ ብቻ ደረጃ አንድ ተቋራጭ እንዲሆን ይደረጋል።

ከዚያ በታች የሆነው ደግሞ እዚያው እንዳይቆም አቅሙ እየተገነባ ወደ ላይ የሚመጣበትን ስርአት ይገነባል። ይህም በአንዴ የሚፈጸም አይደለም፤ የስልጠና ሞጁሎች ተዘጋጅተዋል፤ የምዘና ስርአትም እየተዘረጋ ነው፤ በዚህም በቅተው እንዲመዘኑ ይደረጋል። በስልጠናው የሚጎላቸው ነገር ካለም የሚገባቸው ደረጃ እየተሰጠ እንዲበቁ እየተደረገ ወደሚፈልጉበት ደረጃ የሚደርሱበት ሁኔታ ይፈጠራል፤ ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነታቸውንም እየተገነባ እንዲመጣ ይደረጋል።

ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነት ከዓለም አቀፍ የብቃት ማረጋገጫ /ሰርተፊኬሽን/ ጋር ይያያዛል፤ ከኢትዮጵያ ሚዲያ ወጥቶ ለመስራት የአይሶ የብቃት ማረጋገጫ፣ ዓለም አቀፍ የምዘና ስርአት፣ ዓለም አቀፍ የማኔጅመንት ሲስተም ሊኖር ይገባል። ይህን ማድረግ የሚቻለው ኩባንያዎቻችን በዚያ ደረጃ የተደራጁ፣ የፕሮጀክት ማኔጅመንት አቅምን የገነቡ ሲሆኑ ነው።

ይህን ስራ ደግሞ ለተቋራጮች ብቻ ሰጥተን የምንተወው አይደለም ሲሉ ኢንጂነሩ ተናግረዋል። ተቋራጮችም አማካሪዎችም የሙያ ማህበራትም ባላቸው አደረጃጀት በስራቸው ያሉ ኩባንያዎችን ባለሙያዎችን እያሰለጠኑ የሚያበቁበት፣ እኛም የራሳችንን ሚና የምንጫወትበት በዚያ ደረጃ ኢንስቲቲዩቶች የሚኖሩበትን ስርአት መፍጠር እንደሚገባም አስታውቀዋል። ይህ ሂደት ህጋዊ እና በዓለም አቀፍ ደረጃም ተቀባይነት ያለው ስርአት ይሆናል ማለት ነው ብለዋል።

ሚኒስትር ዴኤታው እንዳሉት፤ ወጪ ሄዶ ተወዳድሮ መስራት የሚችል በአገር ውስጥ መቆየት /ስስቴይን ማድረግ/ የሚችል ኩባንያ ለማፍራት በመጀመሪያ በዚህች አገር ውስጥ የኮርፖሬት ባህል/ ኮርፖሬት ካልቸር/ እንዲገነባ ማድረግ ያስፈልጋል። የኮርፖሬት ባህል ማለት አምስት ስድስት ኩባንያዎችን መጨፍለቅ አይደለም፤ ብቻውንም ቢሆን በሚገባ የተዋቀረ የኮርፖሬት የአሰራር ስርአት ያለው ተቋራጭ እንዲኖር ማድረግ ከተቻለ ጠንካራ ተቋም ማግኘት ተችሏል ማለት ነው።

የተቋራጮችን ተወዳዳሪነት ለማሳደግ እኛ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ የአቅም ግንባታ ፕሮጀክት እንቀርጻለን፤ በዚህም መስፈርቶችን በማዘጋጀት ኩባንያዎችን በማብቃት ትልልቅ ኩባንያዎችን እንፈጥራለን ያሉት ኢንጂነር ወንድሙ፣ ይህ የሚሆነው ግን በሂደት ነው ብለዋል።

እሳቸው እንዳሉት፤ ከዚህ አንጻር የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው የተለየ አሰራር/መካኒዝም/ ይፈልጋል፤ የቻይና ኩባንያ እዚህ አገር መጥቶ ለመስራት ድንገት አልመጣም፤ የአገሪቱ መንግስት ኩባንያው ወጥቶ ሰርቶ ገንዘብ እንዲያመጣ ይደግፈዋል። ከዚህ አንጻር የኛ አገር መንግስት ተቋራጮች ወጥተው እንዲሰሩ ድጋፍ ማድረግ ይኖርበታል።

በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ላይ የሚመጣው ተወዳዳሪነት የሚባክነውን ሀብት ከመቀነስ ባሻገር የሚመደበውን ሀብት በውጤታማ መልኩ ስራ ላይ ማዋል የሚቻልበትን ከባቢ ይፈጥራል። ይህን ተወዳዳሪነት ከፈጠርን በኋላ ይህን ለውጥ /ዳይናሚክ/ የሚሸከም አዲስ ስትራቴጂ መንደፍ ያስፈልጋል ሲሉም ተናግረዋል።የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ አብቦ የነበረባቸውን የቀደሙትን ዓመታትም አስታውሰው፣ በዚያን ወቅት ላይ ያንን እድገት የሚጠብቅ ተግባር አልሰራንም፤ ቁጥር አበዛን፤ ተወዳዳሪነት ላይ ግን እዚህ ግባ የሚባል ተቋራጭ ሳናገኝ ቀረን ሲሉ ገልጸዋል።

ሚኒስትር ዴኤታው እንዳሉትም፤ ከዚህ አንጻር አዲስ ለውጥ /ዳይናሚዝም/ መፍጠር ይገባል፤ ያለውን የገበያ እድል ማስፋት፤ አዳዲስ የገበያ እድሎች መፍጠር ያስፈልጋል። የዛሬ ሰባት ዓመት መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገሮች ተርታ እንደርሳለን ስንል መንገዱ ኮንስትራክሽን ነው ሲሉም ጠቅሰው፣ ኮንስትራክሽን የሚፈጥረው አሴት፣ ለውጥና የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ነው መካከለኛ ገቢ ላይ የሚያደርሰን ብለዋል።

ኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪውን ዘጋን ማለት መንገዱን ዘጋን ማለት ነው። በዚህ ሂደት ውስጥ በየዓመቱ በኮንስትራክሽን ዘርፉ ያለው ኢንቨስትመንት እየጨመረ ነው፤ ከመጨመርም አልፎ ጥሩ ጥሩ ግንባታዎችም አሉ ያሉት ኢንጂነር ወንድሙ፣ ‹‹ሁሉም ሊባሉ በሚችል መልኩ ሜጋ ፕሮጀክቶች ናቸው። የስራ ተቋራጮቻችንን የባለሙያዎቻችንን የአማካሪዎቻችንን ተወዳዳሪነት ካላሳደግን በስተቀር እነዚህ ሜጋ ፕሮጀክቶች መቶ በመቶ ለውጭ ተቋራጮች ሊሰጡ ይችላሉ›› ሲሉ አስገንዝበዋል።

እሳቸው እንዳሉት፤ እዚህ ላይ መያዝ ያለብን ሁሉም አገሮች ያደጉበት መንገድ የውጭ ኩባንያዎች ተሳትፎ ነበር። የውጭ ኩባንያዎች ተሳትፎ ግን የአጭር ጊዜ መሆን አለበት። በእነሱ ተሳትፎ ፕሮጀክቶች እየተሰሩ ቴክኖሎጂ እየተሸጋገረ እውቀት እየተቀሰመ ከዚያም የአገር ውስጥ ተቋራጭነት አቅም እያደገ መምጣት አለበት። የአገር ውስጥ ተቋራጮች ከውጪዎቹ ጋር ያላቸው ትስስር እንዲጠናከር ማድረግ ላይ መሰራት ይኖርበታል። እስከ አሁን ያንን ጠንክረን አልሰራንበትም ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፣ በዚህ የተነሳም በሚባለው ደረጃ ቱሩፋቱን ማግኘት አልተቻለም ይላሉ።

የቻይና ወይም የአውሮፓ ኩባንያ መጥቶ አይስራ ማለት የለብንም ሲሉ ተናግረው፣ እነሱም ይስሩ፤ እኛ ግን የተገነባውን ህንጻ፣ ድልድይ መጠቀም ብቻ ሳይሆን ያለብን፣ እውቀት ቴክኖሎጂና ልምድ ማግኘት ላይ መስራት ይኖርብናል ብለዋል። ከዚህ አንጻር የውጭ ኩባንያዎች ሲመጡ ስንት እጇን ስራ ለአገር ውስጥ ኩባንያዎች ሰጥታችሁዋል፤ ምን እውቀትና ቴክኖሎጂ አሸጋግራችኋል የሚል ስታንዳርድ እናስቀምጣለን፤ ይህ እስከ አሁን አልነበረም ››ሲሉም ጠቅሰው፣ ከዚህ አንጻር ሰፋ ያለ ስራ ከእኛ፣ ከእናንተ ከተቋራጮች ደግሞ ለእዚህ የሚያበቃ ዝግጁነት ይጠበቃል ሲሉም አስገንዝበዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ችግሮቻችን ነገ ላይ ባለን ብሩህ ተስፋ በቀላሉ የምንሻገራቸው ናቸው!

በየትኛውም የዓለም ክፍል የተካሄዱ የለውጥ ንቅናቄዎች በብዙ ተግዳሮቶች የተፈተኑ ናቸው። ለውጥ በራሱ በአሮጌ፤ በዕለት ተዕለት የማኅበረሰብ መስተጋብር ውስጥ የባሕል ያህል ስርጸት ባገኘ አስተሳሰብ እና እሱን በሚጻረር አዲስ/ተራማጅ አስተሳሰብ መካከል የሚደረግ የማይቀር ትግል ነው። ይህም በመሆኑ ለተቃርኖ ሕግ ተጋላጭ እና ተገዥ ነው።

በለውጥ ሂደት ወስጥ የሚፈጠሩ ተቃርኖዎች ሊያስከፍሉ የሚችሉትም ዋጋ እንደየማኅበረሰቡ የንቃተ ሕሊና ደረጃ የሚሰላ ቢሆንም፤ ይብዛም ይነስም በለውጥ ሂደት ውስጥ የሚያልፍ ማኅበረሰብ ሊከፍለው የሚገባ ዋጋ ስለመኖሩ ግን ለጥያቄ የሚቀርብ አይደለም ።

ይህንን ተጨባጭ እውነታ ካለመረዳትና የለውጥ ፈተናዎችን አቅልሎ የማየት፤ የለውጥ ሂደትን አልጋ በአልጋ አድርጎ የመመልከት የተዛባ እሳቤዎች ይስተዋላሉ። ይህም በለውጥ ፈላጊው ማኅበረሰብ ውስጥ መዘናጋትን ከመፍጠር ባለፈ፤ በለውጡ ያለውን ተስፋ ፈጥኖ እንዲደበዝዝ ሊያደርገው እንደሚችል ይታመናል።

ከዚህም ባለፈ የለውጡ ባለቤት የሆነው ሕዝብ ራሱን አግባብ ባለው መልኩ የለውጥ ኃይል አድርጎ እንዳያሰልፍ፤ ለውጡን የሚያጋጥሙት ፈተናዎችም ሆነ ቡድን ወይም ግለሰብ አድርጎ እንዲያስብ ያደርገዋል፤ በዚህም በአሮጌው አስተሳሰብ ተጠልፎ ወደ ቀደመው የቁዘማው ሕይወት መመለሱ የማይቀርበት ሁኔታ ይፈጠራል።

በርግጥ አሁን ያለንበት ዘመን ከቀደሙት ዘመናት ለውጥንና የለውጥ አስተሳሰቦችን በተሻለ መንገድ ለለውጡ ኃይሉ /ለማኅበረሰቡ በማድረስ ተናቦ ውጤታማ መሆን የሚያስችሉ ሰፋፊ አማራጮችን የያዘ ነው፤ አማራጮችን በጥንቃቄ በመጠቀም ፈጥኖ መንቀሳቀስ ካልተቻለ ግን የተገላቢጦሽ የስጋት ምንጭ መሆኑ የማይቀር ነው።

በእኛም ሃገር የሕዝባችንን የለውጥ መሻት ተከትሎ የለውጥ ኃይሉ ሥልጣን ከያዘበት ማግስት ጀምሮ፤ እንደሀገር አላራምድ ያሉንን፤ በየዘመኑ ብዙ ዋጋ ያስከፈሉንን ያረጁ አስተሳሰቦችን ከታሪክ በመማርና በሰከነ መንፈስ፤ በዕውቀት፣ በጥበብ፣ ጊዜንና ሁኔታዎችን ታሳቢ ባደረገ ስሌት በአዲስ ተራማጅ አስተሳሰብ ለመቀየር ሰፋፊ ጥረቶች አድርጓል፤ ዛሬም እያደረገ ነው።

ከቀደመው የለውጥ ታሪኮቻችን ልንማር እንደምንችለው፤ ለውጥ ስሜታዊነት በሚፈጥረው ሞቅታ፤ በለውጥ ወቅት የሚፈጠሩ ተቃርኖዎችን በኃይል ለመፍታት በመሞከርም ሆነ ከፍ ብለው በሚሰሙ የፕሮፖጋንዳ ድምጻች ስኬታማ መሆን አይችልም። ከዚህም የለውጥ ኃይሉ ብዙ ተምሯል።

በተለይ እኛ ይዘናቸው የመጣናቸው የተዛነፉ ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ አስተሳሰቦች፤ እንዲሁም በይደር ያስቀመጥናቸው ችግሮቻችን፣ ለውጡ እንደሃገር ከፈጠረው መነቃቃት ጋር ተያይዞ ከመጣው የውጭ ተጽዕኖ ጋር ተዳምረው ለውጡን በተረጋጋ እና በሰከነ መንፈስ መምራት የግድ አድርጎታል ።

አሁን ላይ የለውጡን ገፊ ምክንያቶች በአግባቡ ባለመረዳት የተፈጠረው ለውጡን አቅልሎ የማየት ሁኔታ፤ የለውጡን ሂደት አልጋ በአልጋ አድርጎ የመመልከት፤ መንግሥት ለለውጡ ስኬት ዋነኛ አቅም ለሆነው መዋቅራዊ ለውጥ ለሰጠው ትኩረትና እየተመዘገበ ላለው ውጤት ተገቢውን ዋጋ የመንፈግ ስጋት ፈጥሯል።

ከዚህም ባለፈ ከተዛቡ ታሪኮች ላይ የሚነሱ የጥፋት ትርክቶች የብሔርና የኃይማኖት ቀለም እየያዙ የመምጣታቸው እውነታ ፤ በሕዝቦች መካከል ለዘመናት ሰፍኖ የቆየውን ተቻችሎ በአንድ ሃገረ-መንግሥት ጥላ ስር በልበ ሙሉነት የመኖርን ትልቁን ብሔራዊ እሴታችንን በብዙ መልኩ እየተፈታተነ ይገኛል።

ይህም ሕዝቡን/የለውጥ ኃይሉን ለአሉባልታ እና ከአሉባልታ ለሚፈጠሩ የጥፋት ትርክቶች ተጋላጭ አድርጎታል፤ በለውጡ ላይ ያለውን እምነት በመሸርሸር፤ ትናንቶችን ናፋቂ እንዲሆን፤ ከነገ ብሩህ ተስፋዎቹ እንዲፋታ እየፈጠሩት ያለው ግራ መጋባት፤ በለውጡ ሂደት ላይም እያስከተሉ ያለው ተጽዕኖ በቀላሉ የሚታይ አይደለም።

የለውጥ ኃይሉ ችግሩን ለመፍታት የሄደበት መንገድ፤ ትልቁን የለውጥ ግብ ታሳቢ ያደረገ፤ በሰፊ ትዕግስት እና ሆደ ሰፊነት ላይ የተመረኮዘ መሆኑ፤ ችግሮቹ እንደ ሕዝብ ሊያስከፍሉን ይችሉ የነበረውን ከፍ ያለ ዋጋ ትርጉም ባለው መልኩ ቀንሶታል ፤ አዲስ የችግር አፈታት ተሞክሮ ጅማሬም ሆኗል።

ይህንን በየትኛውም የለውጥ ሂደት ሊያጋጥም የሚችልን ፈተና ተሻሮ ለመሄድ የመንግሥት አካሄድ እንዳለ ሆኖ፤ በሃገራዊ ለውጡና በለውጡ ገፊ ምክንያቶች ዙሪያ ችግሮቻችን በአዋጅና በመመሪያ የምንሻገራቸው ሳይሆኑ መሠረታዊ የአስተሳሰብ ለውጥ የሚፈልጉ ስለመሆናቸውም ተገቢውን ሕዝባዊ ግንዛቤ መፍጠር ያስፈልጋል።

የሚፈለገውን የአስተሳሰብ ለውጥ ለማምጣት በቅድሚያ በሀሳብ የበላይነት ማመንና ለዚህ የሚሆን በጎ ሕሊና እና ቅን ልቦናን መሠረት ያደረገ ዝግጁነት ይፈልጋል። ከራስ ጋር በብዙ ታግሎ ራስን አሸንፎ መውጣትንም ከሁሉም በላይ ይጠይቃል!

አብዛኞቹ ችግሮቻችን ብዙ ትናንቶቻችንን በልተው በይደር ሲንከባለሉ ዛሬ ላይ የደረሱ፤ በተረጋጋ መንፈስና በሰከነ አዕምሮ ቁጭ ብለን ተነጋግረን የምንፈታቸው፤ ከትናንቶች ይልቅ ነገዎች ላይ ባለን ብሩህ ተስፋ በቀላሉ ልንሻገራቸው የምንችላቸው መሆናቸውንም በሕዝቡ ውስጥ ማስረጽን ይጠይቃል!

**አዲስ ዘመን**

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## የአማርኛ ቋንቋ የባሕር ማዶ ጉዞ

ክብረመንግሥት

የሀገሪቱን ሕገመንግሥት (አንቀፅ 86) ስንመለከትና የኢትዮጵያን የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ ሰነድ ስናገላብጠው፤ ኢትዮጵያ ከዓለም ሀገራት ጋር ሊኖራት ስለሚገባት ግንኙነት እንዲሁም የኢትዮጵያን የውጭ ግንኙነት መርሕና ሌሎች ዲፕሎማሲያዊ ጉዳዮች ምን ይመስላሉ? የሚሉትን ዐብይ የትኩረት አቅጣጫዎችን በግልፅ ያመላክታል።

እነኝህ ከፍተኛ የሕግ ማዕቀፎች ኢትዮጵያ በርካታ ፖለቲካል ኢኮኖሚ ትርፎችን እንድታገኝ ረድተዋታል። በቅርቡ እየሆነ ያለውን ብቻ ብናነሳ የኢትዮጵያ የዲፕሎማሲያዊ ግንኙነቶች በእጅጉ እየተሻሻሉ ስለመሆናቸው ብዙ መረጃዎችን አንስቶ መነጋገር ይቻላል። ከነዚህ ውስጥ ለዛሬ አማርኛ ቋንቋን በተለያዩ ሀገሮች በትምህርት ደረጃ መሰጠት የተጀመረበትን እውነታ ለመቃኘት ልሞክር ።

እንደሚታወቀው ቋንቋ በውስጡ ሰፊ ነገር የያዘ ነው። የተናጋሪውን ሕዝብ ባህል፣ ዕውቀት፣ አስተሳሰብ... ወዘተ ይይዛል ። ከዚህ የተነሳም፣ የአንድን ሕዝብ ቋንቋ ማጥናት ለአጥኚው የሚሰጠው ጠቀሜታ ብዙ ነው። በሀገር ደረጃ ሲሆን ደግሞ በሀገራቱ ሕዝቦች መካከል ያለውን ግንኙነት የበለጠ ለማሳደግ የሚኖረው ፋይዳ ከፍ ያለ ነው።

ከዚህ ተጨባጭ እውነታ አንጻር የሩሲያና የቻይና መንግሥታት የአማርኛ ቋንቋ በዝቅተኛ ደረጃ ለሚገኙ ተማሪዎቻቸው እንደ አንድ ትምህርት ለመስጠት እየሄዱበት ያለው መንገድ የሚበረታታና የሀገራቱን ሕዝቦች ግንኙነት ማሳደር የሚያስችል መልካም ዕድል ነው። በሀገራቱ መካከል ያለው ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት እያደረገ ስለመሆኑም ማሳያ ነው ።

ለዚህም ነው በቻይና ቤጂንግ የውጭ ጥናት ዩኒቨርሲቲ ለቻይናውያን ተማሪዎች የተዘጋጁ መጽሐፍ ምረቃ ላይ የተገኙት ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ አቶ ደመቀ መኮንን፤ የመጻፉ ምረቃ የኢትዮጵያ እና የቻይና ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ወደ ተሻለ ደረጃ ማደጉን የሚያሳይ እንደሆነ ያመላከቱት ።

የኢትዮጵያ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ከቻይና የምርምር ተቋማት ጋር የዕውቀት ልውውጥ ማድረጋቸው ትልቅ ጠቀሜታ እንዳለው፣ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲና በቤጂንግ የውጭ ጥናቶች ዩኒቨርሲቲ መካከል ያለው የአማርኛ ቋንቋ ትብብርም የሕዝብ ለሕዝብ ትስስሩን የበለጠ ያጠናክረዋል ሲሉም መናገራቸው ።

በርግጥ የኢትዮ-ቻይና ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት የረጅም ዘመን ታሪክ ያለው፣ በየወቅቱም ከፍ ያለ እመርታ እያሳየ መምጣቱ የሚታወቅ ነው። የቻይና መንግሥት በኢትዮጵያ የሚገኙ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማትን በሰው ኃይል፣ በትምህርት መርጃ መሣሪያዎች፣ ቤተ ሙከራ በማደራጀትና ያሉትን በማስፋፋት፣ በቴክኖሎጂ ሽግግር፣ በእውቀት እና ምርምር ዘርፍ ከፍተኛ ድጋፍ እያደረገ ነው። ብዛት ላላቸው ኢትዮጵያውያን የትምህርት ዕድል በመስጠትም ተጠቃሽ ነው። ይህ ደግሞ ከቴክኖሎጂና ከእውቀት ሽግግር ባለፈ የባሕል ልውውጥ ከማድረግ አንጻር የማይተካ ሚና እንዳለው ይታመናል ።

የሀገራት ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት እያደገ መሄድ፤ የሀገራቱን ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ፍላጎትን በማሳለጥ ወዳጅነትንም ያጠነክራል። መቀራረብን፣ መተዋወቅንና መፈላለግን ይፈጥራል። ለዚህም ይመስላል ትናንሾቹ የቻይና ሕጻናት አማርኛ ቋንቋን እየለመዱ እንዲመጡ የቻይና መንግሥት መሠረት የሚጥል ተግባር እያከናወነ የሚገኘው ።

ቻይናውያን የአማርኛ ቋንቋን የመልመዳቸው እውነታ እንደሀገር በርካታ ጥቅሞችን ይዞ ይመጣል። ከሁሉም በላይ ቻይናውያን ስለኛ ትናንቶች እና ዛሬዎች የዳበረ እውቀት እንዲኖራቸው ያስችላል። ለቴክኖሎጂና እውቀት ሽግግር የተሻለ ዕድል ይፈጥራል። ይህ ደግሞ ለጀመርነው ሀገራዊ እድገት ተጨማሪ አቅም መፍጠር የሚያስችል ነው።

በሩሲያ በኩል የሚታየውም ከዚህ የተለየ አይደለም። እንደ ቻይና ሁሉ ሩሲያም በተለያዩ ጊዜያት ከኢትዮጵያ ጎን በመቆም የኢትዮጵያ ሁነኛ አጋር መሆኗን አሳይታለች፤ እያሳየችም ነው። በተለያዩ ጊዜያት እንደ ሀገር ፈተና ውስጥ በወደቅንበት ሰዓት ሩሲያ ከኢትዮጵያ ጎን ነበረች። ጉዳያችን ቋንቋ ላይ በመሆኑ ሌላውን በሌላ የአጀንዳ ጽሑፍ ልመለስበት እችላለሁ ።

በቅርቡ በወጣው መረጃ እንደተመላከተው፤ በሞስኮ የሚገኙ የተወሰኑ ትምህርት ቤቶች ከመስከረም ጀምሮ አማርኛ ቋንቋ ማስተማር ሊጀምሩ ነው። በርግጥ ቀደም ባለው ጊዜ በሩሲያ በአማርኛ ቋንቋ እስከ ዶክትሬት የደረሰ ትምህርት ይሰጥ እንደነበር የሚታወቅ ነው ።

የእስያ እና አፍሪካ ጥናት ኢንስቲትዩት ዳይሬክተር አሌክሲ ማስሎቭ ከፈረንጆቹ መስከረም 2023 ጀምሮ ቢያንስ አራት የሞስኮ ትምህርት ቤቶች ለሕጻናት የአማርኛ እና የስዋሂሊ ቋንቋ ማስተማር እንደሚጀምሩ ይፋ አድርገዋል። የሩባ ቋንቋን የሚያስተምሩበትን ዕድልም እየተመቻቸ መሆኑ ተነግሯል።

ውሳኔው ከሁሉም በላይ አፍሪካ አንድ ትልቅ አህጉር ብቻ ሳትሆን የተለያዩ ቋንቋ፣ ባሕል፣ ሃይማኖት እና ኅብረ ብሔራዊ ማንነቶች ያሉባት አህጉር መሆኗን ለአዲሱ ትውልድ ለማሳወቅ የሚያስችል ነው።

አዲሱ ትውልድ ኢትዮጵያ ሆነች በአህጉሪቱ የረጅም ሀገረመንግሥትና የቀደመ ሥልጣኔ ባለቤት መሆኗን፤ ከምንጩ አንብቦ እንዲያውቅና ቀጣይ የሀገራቱ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ከቀደሙት ዘመናት በተሻለ መልኩ ስኬታማ እንዲሆን ያስችላል። ሰላም!

> **የሀገራት ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት እያደገ መሄድ፤ የሀገራቱን ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ፍላጎትን በማሳለጥ ወዳጅነትንም ያጠነክራል። መቀራረብን፣ መተዋወቅንና መፈላለግን ይፈጥራል። ለዚህም ይመስላል ትናንሾቹ የቻይና ሕጻናት አማርኛ ቋንቋን እየለመዱ እንዲመጡ የቻይና መንግሥት መሠረት የሚጥል ተግባር እያከናወነ የሚገኘው**

ማህበራዊ

# እንዲህም ይኖራል

ሕይወት ፈርጀ ብዙ ገጽታዎች አሏት፤ መውጣት እንዳለ ሁሉ መውረድም ይኖራል። ከመውረድ ውስጥም በትጋት መውጣት ይቻላል። አግኝቶ ማጣት እንዳለ ሁሉ አጥቶም ይገኛል። ይህ የሕይወት እውነታ ነው፤ በጥቂቶች የህይወት መውጣትና መውረዶች ውስጥ ብዙዎች ይማራሉ። የህይወትን ፈተናዎችም ያውቃሉ። በከፍታ ውስጥ የሚገኙት ‹‹እንዲህም ይኖራል እንዴ?›› ብለው ራሳቸውን ይጠይቃሉ። ስተቸገሩት ያዝናሉ፤ ካላቸው ቀንሰው የሌሎችን ችግር ይካፈላሉ፤ በተጨማሪም ችግር ብልሃትን ያስተምራል እንዲሉ ከችግር ጋር ተላምዶ ከመኖር ይልቅ ለመፍትሄ የሚታትሩትንም ያበረታታሉ። በመሆኑም ‹‹እንዲህም ይኖራል›› ብለን በከፈትነው አምዳችን ህይወትን በየፈርጁ ታስተውሉበት፣^አስተውላችሁም ትማሩበት ዘንድ ጋበዝናችሁ። ስአስተያየቶቻችሁ፤ ስመሰል ታሪኮች ጥቆማችሁ እንዲሁም ለድጋፋችሁ የዝግጅት ክፍላችን አድራሻ ትጠቀሙ ዘንድ ጋበዝናችሁ።

## ቀን ለማውጣት - ቀን ሲጨልም

ሰላማዊት ውቤ

የህፃን ልጇም ሆነ የእሷ ልብስ ሁሌም የፀዳ ነው። እናትና ልጅ በመልክ ብስል ይሉት ቀይ ናቸው። ሁለቱንም አስተውሎ ላያቸው የፊታቸው ገጽታ በሰም እንደተቀባ ወለል ያንፀባርቃል፡፡ ውብ መልክና ቁመና ይዘው ካልታሰበ ቦታ መገኘታቸው ሁሉንም ያስደነግጣል፡፡ ሁለመናቸው አበባ ቢመስልም የዕጣ ፋንታ ነገር ከማይሆን ቦታ ጥሏቸዋል፡፡

ቅዳሜና እሁድ ሙሉ ቀን፤ ከሰኞ እስከ ዓርብ ደግሞ ከዘጠኝና ከአስር ሰዓት በኋላ አራት ኪሎ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት አጥር ስር በአሳዛኝ ሁኔታ ተኝተው ሲለምኑ ማየት በእጅጉ ያሳዝናል፡፡

ብዙ ጊዜ ህፃን ልጇ የትምህርት ቤት ዩኒፎርሙን እንደለበሰ ጋቢ ተከናንባ መሬት በምትተኛው እናቱ ላይ ጋደም እንዳለ እንቅልፍ ወስዶት ሲታይ ይበልጥ የአላፊ አግዳሚውን አንጀት ይበላል፡፡ በዚህ ሁኔታ ያያቸው ማንም መንገደኛ ስለነሱ ምንም ሳይነግረው የቻለውን እየመፀወተ ያልፋል፡፡ እነሱን የሚያዩ አብዛኞች በሀዘኔታ ከንፈራቸውን እየመጠጡ፣ ራሳቸውን እየነቀነቁ ያልፋሉ። ሁኔታቸውን ልብ ብሎ ላጤነ የእናትና ልጁ ገጽታ ከማሳዘን አልፎ የማማሩን እውነት ይረዳል፡፡ ይህኔ ‹‹መልክ ገንዘብ አይሆን አይበላ›› ማለቱ አይቀርም፡፡

እርግጥ ነው እናትና ልጁ ውብ ናቸው፡፡ ልብሳቸውም ለልመና የወጣ ሰው አይነት አይደለም። ፅአዳና ንጹህ ነው፡፡ እናም ‹‹ለምን ጎዳና ላይ ወጥተው ልመናን መረጡ ? የሚለው የበርካታ ሰዎች ጥያቄ



በአሰሪዋ ተደፍራ የበሽታ ቁራኛ ለመሆንና ጎዳና ለመውደቅ የተገደደችው ወጣት የሚደግፋት ወገን ትሻለች፣

እንደሚሆን አያጠራጥርም፡፡

መቼም አንዲት እናት ፈጣሪ ጤና ከሰጣት ልጇን ሰርታ ማሳደግ ምርጫዋ ይሆናል፡፡ አካሏ ጎድሎ መስራት የሚያስችላት ጤናማ ሁኔታ ላይ ካልሆነች ግን ለልጇ ስትል የማትከፍለው መስዋዕትነት አይኖርም፡፡ የዚች ወጣት እናትም ሁኔታ ይህንኑ እውነታ ያሳያል። ጤናዋ በፍፁም ሰርቶ ልጅ ማሳደግና ማስተማር የሚያስችላት አይነት አይደለም፡፡

ይህች እናት ድህነት ከሴትነት ተዳምሮ ጫናው በርትቶባታል፡፡ የዕለት ጉርስ የሚሆን ቁራሽ ማግኘት አልቻለችም፡፡ ይህ እንዳለ ሆኖ የዕድሜ አለመብሰል ሲታከልበት የሕይወት አቅጣጫዋን አስቶ ከህይወት ፈተና ጥሏታል፡፡

ከሃያ ዓመቷ ወጣት ፍሬህይወት አድማሱ /ለዚህ ፅሁፍ ሲባል ስሟ የተቀየረ/ ጋር የተገጣጠመውም ዕጣ ፈንታ እንዲህ ያለው እንደሆነ እራሷ ባለ ታሪኳ በምሬት ትናገራለች፡፡ ወጣት ፍሬህይወት ውልደትና ዕድገቷ በደቡብ ጎንደር ደብረ ታቦር ከተማ ‹‹አጅባር›› ከተሰኘ አካባቢ ነው፡፡ ለቤተሰቦቿ አምስተኛና ብቸኛዋ ሴት ልጅ ስትሆን አራት ታላላቅ ወንድሞች አሏት፡፡

ስለ አባቷ ማንነትና ታሪክ የምታውቀውም ሆነ ከእናቷ የሰማችው ባይኖርም እናቷ የሚላስ የሚቀመስ የሌላቸው ምስኪን ደሀ መሆናቸውን ትናገራች፡፡ እናት አምስት ቤተሰብ ቀርቶ ራሳቸውንም የሚያኖር አንዳች ገቢ የሌላቸው እንደሆኑ ስታወሳ እንባዋን ማዘዝ መቆጣጠር ይሳናታል፡፡

ወንድሞቿ እና እሷ ብዙ የሚባል የዕድሜ ልዩነት የላቸውም፡፡ ምን አልባት እናት በላይ በላዩ ሳይወልዷቸው አልቀሩም፡፡ ይህ አይነቱ እውነት ረዳትና አጋዥ እንዳይኖራቸው አድርጓል፡፡ ወይዘሮዋ ልጆቻቸውን ሲያሳድጉ በተፈለጉበት ስፍራ ሁሉ ጉልበት ከፍለው፣ በየሰው ቤት ሰርተው ነው፡፡

እናት ሌት ተቀን በሥራ ይባዝናሉ፡፡ የጉልበት ስራ የሚባል አይቀራቸውም፡፡ እንዲሁም በስራው አምሽተው ሲገቡ ለልጆቻቸው ራት፣ ቁርስና ምሳ ማዘጋጀት ግድ ይላቸዋል፡፡ ሲነጋ ደግሞ ማልደው ወደተለመደው ውሏቸው ይበራሉ፡፡

ወደ ገጽ 17 ዞሯል

## ከአማኑኤል የአእምሮ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ጋር በመተባበር በየሳምንቱ የሚታተም

# ትኩረት የሚሹ የወጣቶች የባህሪ እና አዕምሮ ጤና ችግሮች

ጥናቶች እንደሚያመላክቱት ከዛሬ አስርት አመታት በፊት በዓለም ላይ ካሉት ህፃናትና ወጣቶች ውስጥ እስከ 20 በመቶ የሚሆኑ ልዩ ልዩ የባህሪ ችግሮች ያላቸው ሲሆኑ ከዚህ ውስጥ ከ3 እስከ 4 በመቶ የሚሆኑ ህክምና የሚያስፈልጋቸው ናቸው፡፡ በህፃናትና ወጣቶች ላይ ከአስር መሪ የጤና ቀውስ ከሚያስከትሉት ምክንያቶች አምስቱ የባህሪይ እና የአእምሮ ጤና ችግሮች መሆናቸውን ጥናቶች ያረጋግጣሉ፡፡ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት የተለየ ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገባ ዋና ዋና የወጣቶች የባህሪና ጤና ችግሮች ናቸው።

### 1 ከፍተኛ ጭንቀት

ህፃናትና ወጣቶችን ከሚያጠቁ የአእምሮ ችግሮች አንዱ ከፍተኛ ጭንቀት ነው፡፡ በዚህ ችግር የሚሰቃዩ ወጣቶች ከፍተኛ ምክንያት አልባ ፍርሃት፤ የልብ ምት መዛባት፤ መበርገግ፤ አእምሮን ማሰባሰብ አለመቻል በዚህም ምክንያት ትምህርትን በተገቢው ለመከታተል አለመቻል፤ መነጫነጭ፤ በተደጋጋሚና በቀጣይነት ለረጅም ጊዜ ሊታይባቸው እንደሚችል በጥናቱ ተዳሷል፡፡

### 2 ድብርት

ይህ የአእምሮ ጤና ችግር ብዙ ጊዜ በተለይ በህፃናት ላይ ሲከሰት አሳዳጊዎች ወይም መምህራን በቀላሉ ሳይገነዘቡት ለከፋ ሁኔታ የሚዳርግ ነው። ይህም የሚሆነው የህፃናቱ ወይም የወጣቶቹ ባህሪ ዝምተኛ ሲሆን ተቀባይነት ያለው ሆኖ ስለሚገኝ ነው። በአውደ ጥናቱ እንደቀረበው በተለይ አንድ ወጣት ቀድሞ ከነበረው ባህሪ እጅግ በተለየ ሁኔታ የእንቅልፍ፤ የመሳቅ፤ የመጫወት፤ ወዘተ ባልተለመደ ሁኔታ ቀንሰው ከሆነ ለድብርት ተጋልጦ ስለሚሆን በሚገባ ቀረብ ብሎ ማስተዋል ተገቢ እንደሆነ ያሳያል፡፡

ድብርት ሃዘንተኛ መሆንን፤ ቁጡና ነጭናጫነትን፤ ተስፋ መቁረጥን፤ የበደለኛነት ስሜትን፤ ስለራስ ያለ ግምት ዝቅተኛነትን፤ በወጣቱ ላይ ያስከትላል፡፡ ይህ ስሜት እየጨመረ እና እየበረታ ሲሄድ ወጣቱ ከችግሩ ለመላቀቅ ወደ ሱስ አምጭ ንጥረ ነገሮች አለበለዚያም ራስን ለማጥፋት እስከ ማሰብ እንዲደርሱ ያደርጋቸዋል፡፡

### 3 የባህሪይ ቀውስ

ይህ ችግር በህፃናትና በወጣቶች ላይ የሚታይ ፀረማህበረሰብ የሆነ አቋምና ድርጊት የሚንፀባረቅበት ሁኔታ እንደሆነም ነው ጥናቱ የሚያሳየው፡፡ በዚህም ምክንያት ወጣቱ ትምህርቱን ለመከታተልም ሆነ የመሰል ወጣቶች እንዲሁም የህብረተሰቡን ህግጋትና ባህል በሚገባ መከተል አለመቻል ብቻ ሳይሆን አፍራሽ ድርጊቶች የሚፈፀምበት ነው፡፡ ተቃርኖን የሚያጎላ ባህሪ ከማሳየት እስከ ጉልህ የጠባይ ቀውሶች ሊከሰቱ ይችላሉ። ምልክቶቹም ከፍተኛ እልህ፤ አልታዘዝ ባይነት፤ ሌሎችን ተገቢ ባልሆነ ሁኔታ መውቀስ፤ በቀላሉ ማኩረፍ፤ ቁጠኛ እና በቀለኛ ከመሆን አንስቶ እስከ አብዝቶ ደጋግሞ መዋሸት፤ ጠብ አጫሪ መሆን፤ ለእንስሳትም ሆነ ለሰዎች ርህራሄ አልባ መሆን፤ ስርቆት፤ አጥፊነት የወሲብ ጥቃት መፈፀም ወዘተ.... ሊጠቀሱ የሚችሉ መሆናቸውም ተካትቷል፡፡ በአጠቃላይ በባህሪ ቀውስ ውስጥ ያሉ ወጣቶች የቤተሰብ የትምህርት ቤትና የማህበረሰብን ደንብ ባለማክበር ከአካባቢ ጋር ከመጋጨት ባሻገር ህግን በመጣስ በተደጋጋሚ በህግ ጥበቃና ቁጥጥር እስከ መሆን ይደርሳሉ፡፡

### 4 ትምህርት የመከታተል ችግር

ወጣቶች ትምህርታቸውን መከታተል ሲያቅታቸው ወላጆች ለጭንቀት ይዳረጋሉ፡፡ ተማሪዎች በትምህርታቸው ከሚደከሙባቸው ምክንያቶች አንዱ የመከታተል ችግር መከሰት ነው፡፡ እንደ ጥናቱ ምልከታ በተለይ ምንም አይነት የአእምሮ ዝግመትም ሆነ የአእምሮ መቃወስ እንዲሁም የጠባይ መቃወስ በሌለበት ሁኔታ ከሆነ የመከታተል ችግር ሊሆን ስለሚችል ወላጆችም ሆኑ መምህራን ልዩ ትኩረት ሊሰጡት እንደሚገባ ያትታል፡፡

### 5 የወጣቶች ሱስ አምጪ ነገሮችን ተጠቃሚነት

ህፃናት ወደ ወጣትነት እድሜ ሲገቡ ቀስበቀስ ከአሳዳጊዎች ቁጥጥር በመውጣት ነፃነታቸውን ስራ ላይ ማዋል ይጀምራሉ፡፡ በዚህ ጊዜ ከህፃንነታቸው ጀምሮ ሌሎች ሲያደርጉት ያዩትን እነሱም ለመሞከር ይወስናሉ። ጎጅ የሆኑትም ድርጊቶች የሙከራው መነሻ ይሆናሉ፡፡ ከዚህም ውስጥ ሱስ አምጭ ጎጅ ነገሮች ማለትም ሲጋራ፤ ጫት፤ አልኮል መጠጦች፤ የሚሸተቱና በተለያየ መንገድ የሚወሰዱ እፆችና መድሃኒቶች ይገኙበታል፡፡ ለአንዳንድ ወጣቶች የሚወስዱት እፅ ለአእምሮ አለመረጋጋታቸው እንደ መፍትሄ የሚወሰዱ እርምጃዎች ሲሆኑ ሌሎቹ ደግሞ ከወላጆቻቸው የተማሩት አለበለዚያም ራሳቸውን ከመሰል ወጣቶችና አዋቂዎች ተርታ የሚያሰልፉበት መንገድ አድርገው ስለሚያስቡ ነው፡፡

በወጣቶች የሚከሰት የሱስ አምጭ ነገሮች ተጠቃሚነት ለተለያዩ ከፍተኛ አደጋዎች ያጋልጣል፡፡ የተለያዩ አካላዊ አደጋዎች/ወንጀሎች ያልተፈለገ እርግዝና፤ ኤች አይ ቪ ኤድስን ጨምሮ የተለያዩ በወሲብ የሚተላለፉ በሽታዎች እና ለራስ ማጥፋት ድርጊት እንደሚያጋልጡ አለማቀፍ ጥናቶች ያስገነዝባሉ፡፡

### 6 በወጣትነት የሚከሰት የራስ ማጥፋት ድርጊት

ራስ ማጥፋት የወጣቶችን ህይወት በማሳጠር በዓለም በሶስተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡ አብዛኞቹ ህይወታቸውን የሚያጠፉ ወጣቶች በተለያየ የአእምሮ ጤና ቀውስ ውስጥ ይገኛሉ፡፡ በዓለም በየዓመቱ ቢያንስ አራት ሚሊዮን ወጣቶች ራስ የማጥፋት ሙከራ ያደርጋሉ፡፡ ከዚህ ውስጥ ቢያንስ 100 ሺህ የሚሆኑት በተያያዘ ድርጊት ይሞታሉ፡፡ በምዕራቡ ዓለም ራስን ማጥፋት ከድብርትና ሌሎች የአእምሮና የባህሪ ችግሮች ጋር የተያያዘ ሲሆን በማደግ ላይ ባሉ አገሮች ደግሞ ከላይ በተጠቀሰው በተጨማሪ ከማህበራዊና ፖለቲካዊ አለመረጋጋት እንዲሁም ከድህነትና ከሃይማኖት ጋር በአብዛኛው እንደሚያያዝ ጥናቶች ያመለክታሉ፡፡

ወጣቱ ራሱን ለመጉዳት አደጋ ላይ እንደሚሆን ጠቋሚ ምልክቶች መካከልም፤ የአመጋገብና እንቅልፍ ሥርዓት መዛባት፤ ቤተሰብ፤ ጓደኞችና የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ መገለል፤ ከቤት መጥፋት ያልተለመደ ዐመፀኛ ጠባይ፤ የአልኮልና ሱስ አምጭ ነገሮች ተጠቂ መሆን፤ ባልተለመደ ሁኔታ ራስን መጣል ስልቹነት፤ አእምሮን ማሰባሰብ አለመቻል እንዲሁም የተለያዩ ምክንያት የለሽ አካላዊ ችግሮች ለምሳሌ ሆድ ህመም፤ ራስ ህመም፤ ድካምና ለምንም ነገር ስሜት አልባ መሆን፤ ለአብነት የተጠቀሱ ከፍተኛ የአዕምሮና የባህሪ ችግሮች ናቸው፡፡

ከመከላከልና ህክምናው ውስጥም ህፃናት ገና ከመወለዳቸው በፊት ጀምሮ ወላጆች እርግዝናውን በማቀድ ከዚያም ለፅንሱ ተገቢውን እንክብካቤ ማለትም የእናቲቱን አካላዊና አዕምሯዊ ጤና የተሟላ ማድረግ። በወሊድ ወቅት ተያያዥ ችግሮች እንዳይከሰቱ ጥንቃቄ ማድረግ፤ ለህፃኑ የተሟላ የአካልና የአእምሮ ጤና ከፍተኛ አወንታዊ አስተዋፅኦ አለው፡፡ በህፃንነት የሚደረግ የተሟላ እንክብካቤ ወደ ወጣትነት የሚደረገው ሽግግር የተስተካከለ እንዲሆን ያደርጋል፡፡ የተስተካከለ አመጋገብ የተረጋጋና የተሟላ ቤተሰብና አካባቢ ከተለያዩ ወረርሽኝና ቅፅበታዊ በሽታዎች መጠበቅ፤ በአካል በተለይም በራስ ቅል ከሚደርሱ አደጋዎች መጠበቅ፤ እንዲሁም አወንታዊ የጤና አስተዋፅኦ ሲኖረው በየወቅቱ ቤተሰብና ማህበረሰብ የወጣቱን የተናጠልና የድምር ፍላጎት በሚገባ በመመርመር ከጎጅ.ልማዳዊ ድርጊቶች በማራቅ ጠቃሚ፣ ባህላዊና ዘመናዊ እሴቶችን በማዳበር ተገቢውን እንክብካቤ ማድረግ ይጠበቃል።

# ቀን ስማውጣት...

ከ ገጽ 16 የዞረ

ፍሬህይወት እድሜዋ ከፍ እያለ ሲመጣ የእናቷን ድካም ተረድታ ለማገዝ ሞከራለች፡፡ ትምህርቷን ትታ እናቷ ለመደገፍ ጥራለች፡፡ ‹‹እናቴ ልብስ ስታጥብ አብሪያት አጥብ ነበር፡፡ እንጀራ ስትጋገርም እየጋገርኩ ድካሟን ላቀልላት እጥራለሁ›› ትላለች ወጣት ፍሬህይወት እናቷን ለመርዳት የነበራትን ጥረት ስታስታውስ፡፡

ይህ የኑሮ ልምድ ግን እንደነበረው አልቀጠለም፡፡ አዲስ አበባ ሀብታም የሚባሉ ዘመዶች ባሏት አንዲት ጓደኛዋ ሰበብ የህይወት አቅጣጫዋ ሊቀየር ግድ ሆነ። ባልንጀራዋ ጠፍተው ወደ አዲስ አበባ ቢሄዱ በተሻለ ሥራ እናቷን እንደምትለውጥ ስትነግራት ፍሬህይወት አላንገራገረችም። ሀሳቧን በሙሉ ዕምነት ተቀብላ ለመንገዷ ጓዟን ሸከፈች፡፡

ፍሬ ህይወት እናቷን ከድህነት የማውጣት ቢቻላትም ታላላቅ ወንድሞቿን የማስተማር ህልም አላት፡፡ ይህን ዕቅድ በልቧ ሰንቃለች፡፡ አሁን ሀሳቧ ዕውን እንዲሆን ከጓኛዋ ጋር ጉዞ ጀምራለች፡፡ የትራንስፖርት ችላ ካገሯ ያወጣቻት አብሮ አደጓ አዲስ አበባ ሲደርሱ ካሰበችው ደርሳ ከደላላ አገናኘቻት፡፡ ደላላው ሰው ቤት በሰራተኝነት ሲያስቀጥራት አልዘገየም፡፡

የተቀጠረችበት ቦታ ካዛንቺስ አካባቢ ከሚገኝ መኖሪያ ነበር፡፡ ቤቱ ፎቅ እንደነበር ትዝ ይላታል፡፡ ከዛሬ ስምንት ዓመት በፊት በዚህ ቤት በሰራተኝነት ስትቀጠር የአስራ ሁለት ዓመት ታዳጊ ነበረች፡፡ ቀጣሪዎቿ ባልና ሚስት ሁለቱም ስራ ውለው ማታ ወደቤታቸው ይመለሳሉ። ሦስት ወንዶችና አንዲት ሴት ልጅ አለቻቸው፡፡ ከወንዶቹ ልጆች ትልቁ ባገኘው አጋጣሚ ሁሉ አይኑን ጣል አድርጎ ያያታል። ሁሌ ቢያተኩርባትም እሷ ቀና ብላም አታየውም።

አጋጣሚ ቀና ካለች ግን ዓይኑን ሳይሰብር እንደሚያያት ታዝባለች፡፡ በወቅቱ ልጅነት ፤ እፍረትና ድንጋጤ ተደራርበውባት ነበርና ምክንያቱን ለመጠየቅ አልደፈረችም። ብዙን ጊዜ የልጁን ዕይታ አንገቷን ደፍታ፣ በፍርሃት ታሳልፈዋለች። ልጁ ግን በዚህ ብቻ አላቆመም። ወላጆቹ ሥራ ሲሄዱና እህት ወንድሞቹ ሳይኖሩ አጋጣሚውን ይጠቀማል፡፡ ምግብ የምታበስልበት ማዕድ ቤት ድረስ እየመጣ ያያታል፡፡

ሁኔታው ሁልጊዜ ግራ ያጋባታል፡፡ ይህ ሁሉ ሲሆን ከልጁ ጋር አንዳች ዓይነት ንግግር አልነበራቸው፡፡ ‹‹ምን ፈልገህ ነው እኔ ዘንድ የምትመጣው?›› ብላም ጠይቃው አታውቅም። በዚህ ሁኔታ ዓመታት አለፉ፡፡ ከእሱ በቀር የቤቱ ብቸኛዋ ሴት ልጅና ሁለቱ ወንዶች እንዲሁም ወላጆቻቸው በብዙ ነገር ቁጥብ ነበሩ፡፡ ከእርሷ ጋር ቀርቶ እርስ በእርሳቸውም ሲጫወቱ አይታይም፡፡

ፍሬህይወት አብዛኛውን ጊዜ ልብስ ካጠበች፤ ቤት ካፀዳችና ምግብ ካበሰለች በኋላ ከማዕድ ቤት አትወጣም። እንደ አብዛኞቹ የቤት ሰራተኞች ከአሰሪዎቻቸው ጋር እየተሳሳቁ ቴሌቪዥን ማየት ቀርቶ ያበሰለችውን ምግብ ደፍራ አታቀርብም፡፡ ቤተሰቡ የሚመገብ፣ የሚስተናገደው በሴቷ ልጅ አማካኝነት ነበር፡፡

ቡናም ቢሆን ተቀምጣ አታፈላም፡፡ ከሰል አቀጣጥላ ካቀራረበች በኋላ እናትዬዋ ያፈላሉ፡፡ እሷ በየምትጠራው የተበላበትና የተጠጣበትን እቃ ለማንሳትና ለማጠብ ነው። በዚህ ሁኔታ ከቤተሰቡ ጋር አንድ ዓመት ከሦስት ወር አሳለፈች፡፡ አሰሪዎቿ ግን የወር ደሞዝ ከፍለዋት አያውቁም። እሷም ብትሆን ፍፁም ጠይቃቸው አታውቅም።

ከቀናት በአንዱ ሁሌም በአትኩሮት የሚያያት ትልቁ ልጅ በቤቱ ማንም ያለመኖሩን ያረጋግጣል፡፡ እንደ ልማዱ ወደ ማዕድ ቤት ይመጣና ጥቂት ሲመለከታት ይቆያል፡፡ ምግብ እየሰራች፣ በስራ እየተጣደፈች ነው። ሳታየው ከኋላዋ ይደርስና እንዳትጮህ ያፍናታል። አንገቷን አንቆም አስገድዶ ይደፍራታል። ጎረምሳው ያሻውን ከፈፀመ በኋላ ከወደቀችበት ጥሏት ከቤት ወጥቶ ይሄዳል፡፡

ደፋሪዋ ድርጊቱን ፈፅሞ ጥሏት ሲሄድ የተናገረውን አትረሳም። ድርጊቱን ለወላጆቹም ሆነ ለእህት ወንድሞቹ ትንፍሽ ብትል እንደሚገላት ዝቶባታል፡፡ ጆሮዋ ይህን ቃል ስቃይ በተሞላበት ህመም ውስጥ ሆና አድምጧል። ኃይል የተሞላበት የጎረምሳ ጉልበቱ አቅሟን አዳክሞ፣ ያልፀና ሰውነቷን ጎድቶ ነበርና ከወደቀችበት ልትነሳ ብትሞክርም አልቻለችም፡፡

ከወደቀችበት ሳትነሳ ለአራት ሰዓታት ከመሬት ወድቃ ቆየች። ልብሷ በደም ተነክሮ በወደቀችበት እንቅልፍ ወሰዳት። ስትነቃ ግን ነገሩ ህልም ነው የመሰላት። የተፈጠረውን ነገር ማመን አቃታት። ትንሽ አሰበች፡፡ አሰሪዎቿና ልጆቹ የመምጫቸው ሰዓት መቃረቡ ትውስ አላት፡፡ እነርሱ ሳይደርሱ እንደምን ራሷን አጠንክራ መነሳት አለባት፡፡ ጥርሷን ነክሳ ተነሳች ገላዋን ታጠበች። ልብሷን አጸዳች።

ህመሙ ቢፀናባትም አመመኝ ብላ አልተኛችም ምንም እንዳልተፈጠረ ራሷን አረጋግታ የተለመደ ሥራዋን ቀጠለች። ድርጊቱ ተሸፋፍኖ ለአራት ወራት ዘለቀ። ውሎ አድሮ ግን ሆዷ እየገፋ፣ ሰውነቷ ይለወጥ ያዘ፡፡ አሰሪዋ የሰጠቻት ሰፋፊና ረጃጅም ቀሚስም ሆዷን መደበቅ አቃታው፡፡ አምስተኛ ወር ሲቃረብ የሆዷ መጠን እየጨመረ መጣ፡፡

ደግነቱ አብዛኛውን ጊዜ አሰሪዎቿ ቤት ሲኖሩ እሷ ከማዕድ ቤት አለመውጣቷ የሆዷን መግፋት ለመደበቅ ጠቅሟታል፡፡ ከዚህ በፊት እንዲህ ዓይነት ነገር አይታ ስለማታውቅ እርግዝናው ውፍረት መስሏት ነበር፡፡ በሂደት ግን ስሜቱም ድካሙም እየተጫጫናት ጭራሽ አላሰራት አለ፡፡ ፍሬህይወት ግራ አጋቢውን ጉዳይ ማወቅ ፈልጋለች። ደርሶ የሚረብሽ የሚያስጨንቃትን ስሜት እያሳሰባት ነው፡፡ አንድቀን አሰሪዎቿ ሥራ ሲሄዱ ጠብቃ በአቅራቢያው አለ ሲባል ከሰማችው ጤና ጣቢያ አቀናች፡፡ የአምስት ወር ተኩል ነፍሰ ጡር መሆኗ ተነገራት፡፡

‹‹የአሰሪዎቼ ጎረምሳ ልጅ ከደፈረኝ በኋላ ወደ ማዕድ ቤት ሊመጣ ቀርቶ የት እንደገባ አይቼውም አላውቅም›› የምትለው ፍሬህይወት፤ የማርገዟን እውነት ከጤና ጣቢያው እንደሰማች ብርክና ድንጋጤ ያዛት፡፡ ተመልሳ አሰሪዎቿ ቤት ለመግባት ፈራች። ልብሷን ለመውሰድ እንኳን ሳትደፍር እንደወጣች ቀረች፡፡

የት እንደምትሄድ ባታውቅም ቀኑን ሙሉ እያለቀሰች ስትጓዝ ውላ አመሻሹን ሽሮ ሜዳ አካባቢ ራሷን አገኘችው። ሁኔታዋን የተመለከቱ አንዲት ሴት አዝነው ቤታቸው አሳደሯት፡፡ የተወሰነ ቀንም ከእሳቸው ጋር ቆየች። ሴትዬዋ ደሃ ናቸው፡፡ እሷን ተንከባክበው ማኖር ማሳደር አይችሉም፡፡ ቀኗ እስኪደርስ ድረስ ሰርታ የዕለት ጉርሷን እንድትችል መከሯት፡፡ ጎንበስ ቀና እያለች ልብስ ማጠብ የጉልበት ሥራ በመስራት ያዘች፡፡ ሁለት ወራት በዚህ መልክ አለፉ፡፡

‹‹ከጉልበተኛው ጎረምሳ የተረገዘው ልጅ እንደምንም ዘጠኝ ወር ሞልቶት ተወለደ›› ትላለች ወጣት ፍሬህይወት በትካዜ ግዜውን እያስታወሰች፡፡ ሆኖም ልጁን የወለደችው እንዲህ በቀላሉ አልነበረም፡፡ የወለደችው ሽሮ ሜዳ አካባቢ በሚገኘው ቅዱስ ጴጥሮስ ሆስፒታል ሲሆን ለሰባት ጊዜ ቀዶ ህክምና እንደተደረገላት ታስረዳለች፡፡

በወቅቱ የአራስ ወግ አላየችም ‹‹እንኳን ማርያም ማረችሽ ››አልተባለችም፡፡ ጠያቂ ወዳጅ ዘመድ አጥታ ለሶስት ወራት በሆስፒታሉ ተኝታ በበረታ ስቃይና ህመም ማሳለፏን አትረሳም፡፡

ፍሬህይወት የታዳጊነት ጉልበቷ ሳይጠና ተደፍሮ ማርገዝ ዛሬን ስቃይ ውስጥ እንደከተታት አሁን ያለችበትን ሁኔታ ያሳያል፡፡ ከመውለዷ ባለፈ ሃያ ዓመታት በበሽታ ውስጥ ሆና ጎንበስ ቀና ብላ እንዳትሰራ ሆናለች። ‹‹ሆዴ ሰባት ጊዜ እዚህም እዛም እየተቀደደ በመሄዱ ጎንበስ ቀና ብዬ ሥራ መሥራት አልችልም። ከባድ ዕቃ ማንሳትም አይታሰብም። መቀመጥ እንኳን አይሆንልኝም፡፡ አብዛኛውን ጊዜ ተኝቼ የማሳልፈውም ለዚህ ነው›› ትላለች መልከኛዋ፣ ዓይነግቡዋ የልጅ እናት ወጣት ፍሬህይወት፡፡

ባትድንም ከሆስፒታል በቃሽ ተብላ ስትወጣ ምርጫዋ ህፃን ልጇን ይዛ በረንዳ መውደቅ ነበረ፡፡ ልጇ ሁለት ዓመት እስኪሞላው ከአንዱ በረንዳ አንዱ በረንዳ እየተዘዋወረች አሳደገችው፡፡ በዚህ መሃል ሽሮ ሜዳ አካባቢ የምትኖር አንዲት ወጣት ሴት ተዋወቀች፡፡ ጓኛም ሆኑ፡፡ ወጣቷ ራርታ አስጠግታት ልጇን ለማሳደግና ትምህርት ቤት ለማስገባት ችላለች፡፡

ሆኖም መሥራት ባለመቻሏ ላስጠጋቻት ወጣት ሴት ለምና ያገኘችውን ሳንቲም ስትሰጣት እንደነበር ትናገራለች። ‹‹ይህቺ ሴት ካስጠጋችኝ በኋላ ልጄን ትምህርት ቤት በማስገባቴ አሁን ኬ ጂ ሁለት ደርሶልኛል፡፡ ምግብም እዛው ትምህርት ቤት ስለሚመገብ ሃሳብ አይገባኝም፡፡ ዩኒፎርምም ያለበሰው ትምህርት ቤቱ ነው፡፡ በመጪው ነሐሴ ወር ስድስት ዓመቱን ይይዝልኛል›› ትላለች፡፡

በደባልነት አብራት እንድትኖር በመፍቀድ አስጠግታት የነበረችው ወጣት ቤቷ በመፍረሱ ፍሬህይወት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ማደሪያ በማጣት ከህፃን ልጇ ጋር ጎዳና ላይ ለመውጣት ተገድዳለች።

‹‹ልጄን በአባቴ ስም ነው የማስጠራው›› የምትለው ወጣት ፍሬህይወት፤ የደፈራትን ወጣት ፈልጋ አባትህ ይሄ ነው ለማለት እንደማትፈልግና ልፈልግ ብትልም ቦታውን ማስታወስ እንደተሳናት ታስረዳለች፡፡ በጊዜው እውቀቱም ስላልነበራት ለመክሰስ እንዳልቻለች ትግልፃላች፡፡ ስለዚህም ስቃዩዋን ይዛ የተፈጠረውን ነገር በውስጧ ይዛ እህህህ! ብላ ትኖራለች፡፡

‹‹ልጄ ትምህርቱን ሳያቋርጥ እንዲማርልኝ እፈልጋለሁ። መጠለያ ባገኝም ደስ ይለኛል›› የምትለው ወጣት ፍሬህይወት፤ አግዙኝ የሚል ጥሪ ታስተላልፋለች፡፡ እኛም ይህን ፅሁፍ የተመለከቱ ሁሉ ወጣት ፍሬህይወትን ለመርዳት ምላሻቸው ፈጣን እንደሚሆን እንገምታለን፡፡ በየሰዉ ቤት ተቀጥረው ሲሰሩ በአሰሪ ልጆች፤ አባወራዎችና በተለያዩ የቤተሰብ አባላት በመደፈራቸው ዕጣ ፈንታቸው እንደ ወጣት ፍሬህይወት የሆኑ ወጣቶች በርካታ ናቸውና ጩኸታቸው ሊሰማ፣ እምባቸው ሊታበስና ከልመና የሚወጡበት መንገድ ሊመቻችላቸው ይገባል፡፡

## ከግብርና ሚኒስቴር ጋር በመተባበር በየአሥራ አምስት ቀኑ የሚታተም

# የስንዴ ልማት ስኬት በሩዝ ይደገማል

በዮሃንስ ደመቀ

በአስር ዓመቱ አገራዊ የልማት እቅድ የግብርናው ዘርፍ ዕድገት በሚፈለገው ደረጃ ፈጣን እንዲሆንና ግብርና እንዲዘምን ብሎም ለአጠቃላይ ኢኮኖሚው የመዋቅራዊ ሽግግር የተሻለ አስተዋጽኦ እንዲያበረክት ይጠበቃል፡፡ ለዚህ ደግሞ የመስኖ ልማት በተገቢው መጠን ማስፋፋትና በቴክኖሎጂ የታገዘ ማድረግ፣ የተቀናጀ የግብርና መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ሥርዓት ማስፈን፣ ቀጣይነት ያለው ቴክኖሎጂ ማመንጨት፣ ብዜትና ስርፀት ሥርዓት ማዳበር፣ የግብርና ፋይናንስ እንዲሁም ኢንሹራንስ እና ኢንቨስትመንት በበቂ ሁኔታ ማሳደግ፣ የግብርና ግብይት ሥርዓት ዘመናዊ፣ ፍትሐዊና ሕጋዊ ሆኖ እንዲገነባ ማድረግ እንዲሁም በግብርና መስክ የግሉን ዘርፍ ተሳትፎ የሚያበረታታ ሥርዓት መፍጠር ዋነኛው ተግባር ነው፡፡

የአገራችን የግብርና ምርት በዋናነት በዝናብ ላይ የተመሠረተ በመሆኑ ለዝቅተኛ ምርታማነት የተጋለጠ ነው። ከዚህም በተጨማሪ የምርት መጠን ከዝናብ መጠን መዋዠቅና ከሚከሰቱ የድርቅ አደጋዎች ጋር ተያይዞ ከፍተኛ ውጣ ውረዶች ይታዩበታል። ይህ አካሄድ የሚጠበቀውን የግብርና ሽግግር ለማረጋገጥ በቂ ስላልሆነ ለመስኖ ልማት ትኩረት በመስጠትና የመስኖ አቅምን በማጎልበት የግብርናን ዘርፍ ከዝናብ ጥገኝነት የማላቀቅ ስራዎች ባለፉት ጥቂት ዓመታት በትኩረት ተጀምረዋል፡፡ ለዚህም ለግብርና ሥራ የሚያገለግሉ አነስተኛ፣ መካከለኛና ትላልቅ የመስኖ ልማቶች በመንግሥት፣ በልማት አጋሮች፣ በግሉ ዘርፍ እንዲሁም በማህበረሰቡ ትብብር እየተገነቡ ይገኛሉ። እነዚህን የመስኖ መሠረተ ልማቶች ተጠቅሞ በዓመት ውስጥ ያሉንን የምርት ወቅቶች ከፍ በማድረግ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ ከሚደረገው ርብርብ ባለፈ ለኢንዱስትሪና ለወጪ ንግድ በቂ ምርት ከማቅረብ አኳያ ከፍተኛ አስተዋጽዖ እንዲኖረው እየተሠራ ነው።

ባለፉት ጥቂት ዓመታት ተግባራዊ ከተደረጉ የመስኖ ልማት ሥራዎች መካከል ደግሞ የመስኖ ስንዴ ልማት ፕሮግራም አንዱና ትልቁን ድርሻ የሚይዝ ነው፡፡ ፕሮግራሙ ከጥቂት ዓመታት በፊት በጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ኢኒሼቲቭ የተጀመረ ሲሆን በዋናነትም ግብርናውን ከዝናብ ጥገኝነት አሠራር ወደ ተቀናጀ የዝናብና መስኖ ግብርና ሥርዓት በመቀየርና ድህነትን በመቀነስ የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ እንዲያስችል ነው፡፡ አገራዊ የስንዴ ፍላጎት ክፍተትን ለመሙላት በዝናብ የሚመረተው የስንዴ ምርታማነትን ከማሳደግ ጎን ለጎን የበጋ መስኖ ስንዴ ልማት በ2011 ዓ.ም ተጀመረ፡፡

ኢትዮጵያ ከፍተኛ የስንዴ ምርትን ከሚያመርቱ ከሰሃራ በታች ካሉ አገሮች መካከል አንዷ ስትሆን የአመራረት መሰረቱም በዋናነት በዝናብ ላይ የተመሠረተ ግብርና ነው፡፡ በአገሪቱ የስንዴ ምርት በስፋት የሚመረተው በደጋማውና ከፍተኛ ቦታ ላይ ባሉ የአርሲ፣ ባሌ፣ ሸዋ፣ ጎንደር፣ ትግራይ፣ ጎጃም፣ ኢሉአባቦር፣ ምዕራብ ሐረርጌና ሲዳማ አካባቢዎች ነው። ይሁን እንጅ በቅርብ ዓመታት የተጀመረው የመስኖ ስንዴ ልማት ፕሮግራም የስንዴ ልማት ቦታዎችንና አገራዊ ምርታማነትን ማሳደግ እንዲቻል በዝናብ ብቻ ከማምረት በተጨማሪ በመስኖ አማካኝነት የስንዴ ሰብል በደጋማው ብሎም በቆላማና ሞቃታማ አካባቢዎችም እየተመረተ ይገኛል፡፡

የመስኖ ስንዴ ልማት ስራው ውጤታማ እንዲሆን የመስኖ ውሃና ግብዓት አቅርቦት፣ የምርምር ድጋፍና ኤክስቴንሽን አገልግሎት እንዲሁም የምርት ገበያ ትስስር ዋና የትግበራው ምሰሶዎች በማድረግ እየተሠራ ይገኛል።

መንግሥት በመስኖ መሰረተ ልማት ላይ ከፍተኛ መዋለ-ነዋይ እያፈሰሰ ሲሆን በተለይም ስንዴ በዋናነት በሚመረትባቸው የደጋማ አካባቢዎች ሰፊ ሥራ እየተሠራ ይገኛል፡፡ የመስኖ ስንዴ ልማት በኦሮሚያና አፋር ክልሎች ውጤታማነቱ መረጋገጡን ተከትሎ በአማራ፣ ደቡብና ሶማሌ ክልሎች የልማት ሥራው ተስፋፍቶ ይገኛል፡፡




ዘመናትን ሲባክኑ በኖሩ የበጋ ወቅቶች እንድንቆጭ ያደረገን የመስኖ ልማት

የመስኖ ስንዴ ልማት በ2011 ዓ.ም በሶስት ሺ 502 ሄክታር የተጀመረ ሲሆን በ2014 ዓ.ም 450 ሺ ሄክታር በማልማት አገራችን 23 ሚሊየን ኩንታል የመስኖ ስንዴ የማምረት አቅም ላይ እንድትደርስ ማድረግ ተችሏል። በ2015 ዓ.ም ከአንድ ነጥብ ሶስት ሚሊዮን ሄክታር 52 ሚሊዮን ኩንታል ከመስኖ ስንዴ ምርት ለማግኘት ግብ ተጥሎ እየተሠራ ነው። በ2015 ዓ.ም የበጋ መስኖ ስንዴ ፕሮግራም የተነሳበት ዓላማ ከውጭ የሚገባን ስንዴ በአገር ውስጥ ምርት መተካት፣ የሥራ እድል መፍጠርና በቂ ምርት ለኢንዱስትሪው ከማቅረብ ባለፈ የወጪ ንግድ ገቢ ማሳደግን እንደ አንድ ተጨማሪ ዓላማ በማንገብ እየተሠራ ይገኛል፡፡

አገራችን ከስንዴ በተጨማሪ ለበርካታ የሰብል አይነቶች ምቹ የሆነ ስነ-ምህዳር ያላት ስትሆን ከእነዚህ ሰብሎች መካከል አንዱ ሩዝ ነው፡፡ የሩዝ ሰብል በተለያዩ የአገሪቱ አካባቢዎች ዝናብን መሰረት በማድረግ እየተመረተ ሲሆን ምርትና ምርታማነቱን ለማሳደግ ሰፊ ርብርብ እየተደረገ ነው፡፡ ሩዝ በቀጣይ 10 ዓመታት በልዩ ትኩረት ከሚተገበሩ አስሩ አገራዊ የግብርና ፕሮግራሞች መካከል አንዱ ነው፡፡ ከመስኖ ስንዴ ልማት ፕሮግራም የተገኘውን ተጨባጭ ለውጥና ውጤታማነቱን መሰረት በማድረግ እንዲሁም ልምዶችንና ተሞክሮዎችን በመቀመር በቀጣይ በሩዝ ምርትና ምርታማነት ላይ ለውጥ ለማምጣት እቅድ ተይዞ እየተሰራ ይገኛል፡፡

በመጨረሻም የሩዝ ልማትን እንደ ስንዴው ልማት ስኬታማ ለማድረግ ሁሉም ባለድርሻ አካላት የየራሳቸውን አስተዋፅዖ በማበርከት የሚጠበቅባቸውን እንዲወጡ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ያሳስባል፡፡

# ስፖርት



# በዓለም ሻምፒዮና ኢትዮጵያን የሚወክሉ የማራቶን አትሌቶች ታውቀዋል

ብርሃን ፈይሳ

ኢትዮጵያ እና ማራቶን ከግሪካዊው ወታደር ፊሊፒደስ በተሻለ ቁርኝት አላቸው ቢባል ማጋነን አይሆንም። በዚህ ርቀት ኢትዮጵያ ከኦሊምፒክ እና ዓለም ሻምፒዮና መድረኮች ጋር የተዋወቀችበት ድልንም መቀዳጀት የጀመረችበት ዘመን ሩቅ ነው። ለዘመናት በማራቶን ስኬት ተጠቃሽ ከሆኑ ሃገራት ቀዳሚዋ ስለመሆኗም በየሳምንቱ መጨረሻ በሚካሄዱ የጎዳና ውድድሮች የሚመዘገቡ ውጤቶች ማሳያ ናቸው።

ኢትዮጵያ በዓለም ሻምፒዮና መድረኮች እአአ በ1983 በአትሌት ከበደ ባልቻ በተገኘው የብር ሜዳሊያ የውጤት ጅማሬዋን ያደረገች ሲሆን ለበርካታ ዓመታት ከውጤት ርቃ ነበር። እአአ 2009 የበርሊን ሻምፒዮና አንስቶ ግን የሜዳሊያ ሰንጠረዥ ውስጥ ያልገባችበት ጊዜ የለም። ባለፉት ሁለት ሻምፒዮናዎች ደግሞ የወርቅና የብር ሜዳሊያዎችን በማግኘት የርቀቱን የበላይነት መቆናጠጥ ችላለች።

በአሜሪካዋ ኦሪገን ከዓመት በፊት በተካሄደው የዓለም አትሌቲክስ ሻምፒዮና የማራቶን ውድድር ኢትዮጵያ በሁለቱም ጾታዎች ድሉን በመጠቅለል የረጅም ርቀት ፈርጦች ሃገር መሆኗን ማስመስከሯ የሚታወስ ነው። በወንዶች በኩል አትሌት ታምራት ቶላ ሌላኛውን የሃገሩን ልጅ ሞስነት ገረመውን አስከትሎ በአሸናፊነት ነበር ውድድሩን ያጠናቀቀው። ታምራት የገባበት 2:05:36 የሆነ ሰዓትም የውድድሩ ክብረወሰን ነበር። በሴቶች በኩልም በተመሳሳይ ጀግናዋ አትሌት ጎተይቶም ገብረስላሴ አስደናቂ በሆነ ብቃት የወርቅ ሜዳሊያውን ለሃገሯ አስመዝግባለች። አትሌቷ ርቀቱን ያጠናቀቀችበት 2:18:11 የሆነ ሰዓትም በሴቶች የውድድሩ ክብረወሰን ነው።

በመሆኑም ሁለቱ ባለ ድል አትሌቶች ከሁለት ወራት በኋላ በሚካሄደው 19ኛው የዓለም አትሌቲክስ ሻምፒዮና









ኢትዮጵያ የዓለም ሻምፒዮና ጠንካራ የማራቶን ቡድንን ይፋ አድርጋለች፣

በቀጥታ ተሳታፊ ይሆናሉ። ይኸውም ኢትዮጵያ በዚህ ውድድር ላይ በቀዳሚነት ተጠባቂ ሃገር ያደርጋታል። የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽንም ሃገራቸውን በሻምፒዮናው የሚወክሉ የማራቶን አትሌቶችን አሳውቋል። ፌዴሬሽኑ በድረ ገጹ ይፋ ባደረገው የዕጩ አትሌቶች ዝርዝር መሠረትም በቀጥታ ተሳታፊ ከሆኑት አትሌቶች ውጪ በሁለቱም ጾታዎች አምስት አምስት አትሌቶችን አቅርቧል። አሰልጣኝ ገመዱ ደደፎ እና ሃጂ አዲሎ ደግሞ ቡድኑን በአሰልጣኝነት ለመምራት ተመራጭ ሆነዋል። ይህንን ተከትሎም ፌዴሬሽኑ ቅሬታ ያላቸው አካላት እስከ ሰኔ 6 ቀን 2015ዓ.ም በኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ተሳትፎና ውድድር ክፍል ተገኝተው እንዲያቀርቡ አሳስቧል።

የቀረቡት ዕጩዎችም በወንዶች በኩል ያለፈው ዓመት የአምስተርዳም ማራቶን አሸናፊው አትሌት ፀጋዬ ጌታቸው አንዱ ነው። አትሌቱ በወቅቱ ርቀቱን የሸፈነው 2:04:48 በሆነ ሰዓት ሲሆን፤ በተያዘው ዓመት የቶኪዮ ማራቶንን በሦስተኝነት ነበር ያጠናቀቀው። አትሌቱ ያስመዘገበው 2:05:25 የሆነ ሰዓትም ለሻምፒዮናው በእጩነት እንዲመረጥ አድርጎታል። ከወራት በፊት በተካሄደው የቶኪዮ ማራቶን አሸናፊ የነበረው አትሌት ጫሉ ዴሶም የቡድኑ አባል ሊሆን ችሏል። ቶኪዮን 2:05:22 በሆነ ሰዓት የሮጠው አትሌቱ፣ ያለፈው ዓመት የፓሪስ ኦሊምፒክ አሸናፊ ነበር። በዓመቱ የሲድኒ ኦሊምፒክ 3ኛ ደረጃን ሲይዝ በቫሌንሺያ ማራቶን ደግሞ 6ኛ ነበር።

የለንደን ማራቶንን አራተኛ ሆኖ ያጠናቀቀው አትሌት ልዑል ገብረሥላሴም ከእጩዎቹ መካከል አንዱ ሲሆን፤ ያስመዘገበው ሰዓትም 2:05:45 ነው። አትሌቱ ባለፈው ዓመት የለንደን እና የሮተርዳም ማራቶኖች ተሳትፎውንም በሁለተኛነት ነበር የፈጸመው። 2:06:38 በሆነ ሰዓት የለንደን ማራቶን በመሮጥ 5ኛ ደረጃን የያዘው አትሌት ሰይፉ ቱራም ከዕጩዎቹ መካከል ተካቷል። በቺካጎ እና ፓሪስ ማራቶኖች ሁለተኛ ደረጃን ይዞ ያጠናቀቀው ይህ አትሌት በኦሪጎኑ የዓለም ቻምፒዮና 6ኛ ደረጃን ነበር የያዘው። ማራቶንን ቅርብ ጊዜ የተቀላቀለው ሌላኛው አትሌት መሐመድ ኢሳም በቡድኑ ተካቷል።

ያለፈው ዓመት በአምስተርዳም ማራቶን 5ኛ የነበረው አትሌቱ፤ ከወራት በፊት በተካፈለበት የቶኪዮ ማራቶን 2:05:22 በሆነ ሰዓት 2ኛ ደረጃን ለመያዝ ችሏል።

በሴቶቹ በኩል ያለፈው ዓመት የቫሌንሺያ ማራቶን አሸናፊዋ አማኔ በሪሶ ለቡድኑ በዕጩነት ከቀረቡ አትሌቶች አንዷ መሆን ችላለች። አትሌቷ በወቅቱ ያስመዘገበችው 2:14:58 የሆነ ሰዓት ነው። ማራቶንን በቅርቡ የተቀላቀለችውና ተስፋ ሰጪ ጅማሬ ላይ የምትገኘው አትሌት ፀሐይ ገመቹ ደግሞ 2:16:56 የሆነ ሰዓት አላት። ያለፈው ዓመት አምስተርዳም ላይ 3ኛ የሆነችው ፀሐይ፤ በዘንድሮው የቶኪዮ ማራቶን ሁለተኛ በመሆን የገባችበት ሰዓት የግሏ ፈጣን ነው። ሌላኛዋ ከምትታወቅበት ግማሽ ወደ ሙሉ ማራቶን የተሸጋገረችው አትሌት ያለምዘርፍ የኋላውም ከእጩዎቹ መካከል ተገኝታለች። የማራቶን ጅማሬዋን በለንደን በማድረግ ያለፈው ዓመት አሸናፊ ስትሆን በዘንድሮው ውድድር ደግሞ 5ኛ ደረጃን ነበር የያዘችው። በርቀቱ ያላት ፈጣን ሰዓትም 2:17:26 ነው።

የዘንድሮውን እና ያለፈውን ዓመት የለንደን ማራቶን 2ኛ እና 3ኛ ደረጃ የያዘችው አትሌት መገርቱ ዓለሙም ከእጩዎቹ መካከል አንዷ ናት። አትሌቷ በርቀቱ 2:18:32 የሆነ ሰዓትም አላት። ወርቅነሽ ኢዴሳ ደግሞ የቶኪዮ ማራቶንን 2:20:13 በሆነ ሰዓት 4ኛ ሆና ያጠናቀቀች እንዲሁም በዕጩነት የቀረበች አትሌት ናት።

ጤና ሚኒስቴር - ኢትዮጵያ
MINISTRY OF HEALTH-ETHIOPIA

## ከጤና ሚኒስቴር ጋር በመተባበር በየአሥራ አምስት ቀኑ የሚታተም

# በኦሮሚያ ክልል የተከሰተውን የኮሌራ በሽታ ለመከላከል የተደረጉ ጥረቶች እና ለውጦች

በ2014 ነሐሴ ወር አጋማሽ አካባቢ በኦሮሚያ ክልል ባሌ ዞን የኮሌራ በሽታ መከሰቱ ከታወቀ ጊዜ ጀምሮ የክልሉ ጤና ቢሮ ስርጭቱ እንዳይስፋፋ ብርቱ ጥረቶችን አድርጓል። በሽታውን በፍጥነት ለመቆጣጠር ይረዳው ዘንድ ስድስት ምሰሶዎችን/ፒላሮችን በመለየት ወደሥራ እንደገባ የክልሉ ምክትል ጤና ቢሮ ኃላፊ ዶክተር ተስፋዬ ከበበው ያስረዳሉ።

እንደክልሉ ምክትል ጤና ቢሮ ኃላፊ ማብራሪያ በሽታውን ለመቆጣጠር ከሚያስችሉ ምሰሶዎች የመጀመሪያው የቅንጅት ሥራ ነው። እንደእርሳቸው አባባል የኮሌራ ወረርሽኝን በአንድ አካል ብቻ መቆጣጠር አዳጋች ነው። ስለሆነም የሌሎች ተቋማትን ርዳታ ማስተባበር ያስፈልጋል። ስለዚህ የጤና፣ የውሃ ልማት፣ የኮሙኒኬሽን፣ የፋይናንስ፣ የአስተዳደር እና ሌሎች ተቋማት የየራሳቸውን ሚና እንዲወጡ ማድረግ የመጀመሪያው ተግባር ነበር። ለተቋማቱ ስለኮሌራ ወረርሽኝ መረጃ መስጠትና በሽታውን ለመቆጣጠር ምን ምን ሥራዎች መሠራት እንዳለባቸው እንዲሁም እያንዳንዱ ተቋም ምን አይነት አስተዋፅዖ እና ርብርብ ማድረግ እንደሚገባቸው ቅንጅታዊ አሠራር ተፈጥሯል።

ሁለተኛው ምሰሶ የሚባለው የቅኝት ሥራ ነው። በቅኝት ሥራው መጀመሪያ በሽታው ምን እንደሆነ የሚገልጹ ምልክቶች ሲታዩ ማኅበረሰቡ ለጤና ባለሙያዎች እንዲያሳውቅ የሚያስችል አሠራር ተዘርግቷል። በሰዎች ላይ የሚታዩ የበሽታ ምልክቶችን መነሻ በማድረግ በሽታው መኖሩን እና አለመኖሩን በላብራቶሪ የማረጋገጥ ሥራ ይሠራል።

ሦስተኛው እና አራተኛው ኬዝ ማኔጅመንት እና የግብዓት አቅርቦት የሚባሉት ናቸው። ለምሳሌ በአንድ አካባቢ ኮሌራ አለ ተብሎ ከታወቀ



ዶክተር ተስፋዬ ከበበው የኦሮሚያ ክልል ምክትል ጤና ቢሮ ኃላፊ

ታማሚዎቹ ከሌሎች ታካሚዎች ጋር እንደማንኛውም በሽታ በአንድ ቦታ ሆነው ሕክምናቸውን መከታተል ስለማይችሉ ተለይተው እንዲታከሙ ይደረጋል። ስለሆነም የኮሌራ ሕክምና ማዕከል ተብለው ቦታዎች ይለያሉ። ይህም በሦስት ደረጃዎች ይከፈላል። አንዱ የመጀመሪያ ርዳታ የሚደረግበት ማለትም በጎጥ በቀበሌ ደረጃ ኮሌራ ኮርነር ተብሎ ትንሽ ሰዎች የሚታከሙበትን እና በሽታው እንደተከሰተ ከመስፋፋቱ በፊት በጥቂት ሰዎች ላይ ልየታና እክማ ማድረግን የሚመለከት ነው። ሌላኛው ኮሌራ ኮርነር ተብሎ የሚታወጀው በዩኒሴፍ እና በሀገር ውስጥ የጤና ተቋማት ታማሚዎች በተለየ ቦታ ሆነው ሕክምና የሚያደርጉበት ትልቅ የሕክምና ማዕከል ማዘጋጀት ነው።

ከዚሁ ጋር የማይለየው የሕክምና ግብዓት አቅርቦት ሦስተኛው ደረጃ ነው። እንደ የዓለም የጤና ድርጅት፣ ዩኒሴፍ ፣ ኅብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት፣ ጤና ሚኒስቴር፣ የክልል ጤና ቢሮና ሌሎች አጋር የጤና ተቋማት የአልጋ፣ የመድኃኒት በአጠቃላይ ከበሽታው ጋር በተያያዘ አስፈላጊውን ግብዓት የሚያቀርቡበት እና ርብርብ የሚያደርጉበት ተግባር ነው።

አምስተኛው ምሰሶ የኮሌራ ክትባት መስጠት ነው፤ ይህም በተለያየ ደረጃ ተከናውኗል። ለመጀመሪያ ጊዜ ባሌ አካባቢ በሽታው እንደተከሰተ የተሰጠ ሲሆን አሁን ደግሞ ለሁለተኛ ጊዜ በርከት ያለ መጠን ያለው ክትባት ሌሎች አምስት ዞኖችን በማካተት ተሰጥቷል።

የመጨረሻው ምሰሶ በሽታው ምን ያህል በሰው ላይ ጉዳት ሊያደርስ እንደሚችል ኅብረተሰቡ በሚገባ መረጃ እንዲኖረውና እያንዳንዱ ሰው ምን አይነት ጥንቃቄ ማድረግ እንዳለበት፣ በሽታውን ለመቆጣጠር ምን አይነት አስተዋፅዖ ማበርከት እንዳለበት ለማስገንዘብ፤ ኮሚቴዎችን ማቋቋምና ሚዲያዎች በጉዳዩ ዙሪያ ግንዛቤ እንዲያስጨብጡ የማድረግ ሥራ ተሠርቷል። ይህ በመደረጉ ስርጭቱ እንዳይስፋፋና የከፋ ጉዳት እንዳይስከትል ማድረግ መቻሉን ዶክተር ተስፋዬ አስረድተዋል።

ስለሆነም ቀደም ብሎ በሽታው በተከሰተባቸው ምሥራቅ ባሌና ባሌ ዞን፣ ምዕራብ አርሲ ፣ምሥራቅ ቦረና እና ጉጂ አካባቢ ወረርሽኙን ወደ መቆጣጠር እየተደረሰ ነው ያሉት ዶክተር ተስፋዬ ምዕራብ ጉጂ ቦረና እና ምሥራቅ ሸዋ አካባቢ አዳዲስ ምልክቶች እየታዩ እንደሆነ ጠቅሰዋል። ስድስቱን ምሰሶዎች ተጠቅሞ ወረርሽኙን የመቆጣጠሩ ሥራ አሁንም እንደቀጠለ ነው ያሉት ዶክተር ተስፋዬ ኮሌራን ሙሉ ለሙሉ መቆጣጠር ተችሏል የሚባለው ግን በሽታው አለ በተባለበት ቦታ ለአርባ ተከታታይ ቀናት ምልክቱ በአንድም ሰው ላይ ሳይታይ ሲቀር እንደሆነ ተናግረዋል። ከዚህ አንጻር ወረርሽኙ መጀመሪያ በተከሰተባቸው አካባቢዎች መቆጣጠር የተቻለ ቢሆንም በአጎራባች አካባቢዎች አዳዲስ ምልክቶች በመታየታቸው ሙሉ ለሙሉ በቁጥጥር ሥር ውሏል ማለት አይቻልም ብለዋል።

ኮሌራ የሚተላለፍበት መንገድ የግለሰብ፣ የማኅበረሰብና የአካባቢ ንጽሕና ሲጓደል እንደሆነ የጠቀሱት የክልሉ ምክትል የጤና ቢሮ ኃላፊ በዓይነምድር፣ በተበከለ ምግብ ወይም ውሃ አማካኝነት ሊከሰትና ሊተላለፍ ይችላል ብለዋል። ስለዚህ የግል የቤተሰብና የአካባቢ ንጽሕናን በመጠበቅ ኮሌራን መከላከል ይቻላል። ኅብረተሰቡ ሜዳ ላይ የመጸዳዳት መጥፎ ባሕልን አስወግዶ ሽንት ቤት ቆፍሮ የመጠቀም ልምድ ቢያሳድግ በሽታውን ለመቆጣጠር የሚደረገውን ጥረት በእጅጉ እንደሚያግዝና የሰዎችን በበሽታው የመያዝ ስጋት እንደሚቀንስ ተናግረዋል። የበሽታውን ስርጭት ለመቆጣጠር ለምግብነት የሚውሉ አትክልቶችን በሚገባ አጥቦ መመገብና እንደሥጋ የመሳሰሉትን አብስሎ መመገብ እንደሚመከር ገልጸዋል። የኮሌራ በሽታ ምልክቶች ከታዩም ማለትም አጣዳፊ ተቅማጥና ትውከት ኖሮ ትኩሳትና ሕመም ከሌለው የኮሌራ ምልክት ሊሆን ስለሚችል እንዲህ አይነት ምልክት ሲያጋጥም ሕመሙ የተከሰተበት ሰው በፍጥነት በአቅራቢያ ወደሚገኝ ጤና ተቋም ሄዶ እንዲታከምና ሌሎች ሰዎችም ከንክኪ እንዲታቀቡ ዶክተር ተስፋዬ መልዕክት አስተላልፈዋል።